**16/2/2013 ዓ.ም**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን፣

ዛሬ ጥቅምት **16** ኪዳነ ምህረት ናት ክብር፣ምስጋና፣ስግደት ለሷ ይገባል፣

ይህንን መልዕክት የመፃፍ ፍላጐት አልነበረኝም ነገር ግን እንድፅፍ የሚያነሳሱ ብዙ ጥያቄዎች በውስጤ ይነሳሉ እነዚህን ጥያቄዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ይወያይበት ዘንድ ለመፃፍ በእግዚያብሄር ፈቃድ ብዕሬን አንስቼ አለሁ አሜን ።

ይህቺ አጭር ፅህፍ እወነቱን መረዳት ለሚፈልጉና መፍትሄ ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን የመወያያ ርዕስ እንዲሆን በማሰብ እንጂ ለኢትዮጵያውያን መፍትሄ እራሳቸው ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን አምናለሁ።

ይህ ፅሁፍ የደረሳችሁ እውነትን መጋፈጥ ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን እንዲደርስ አድርጉ።በፅሁፌ ብዙም ትንታኔ አልሰጠሁም የአንድ ቀን ፅህፍ ነው ። ለእናንተ ለውይይት ክፍት አድርጌዋለሁ።የእናት ሀገራችን  ችግር የረጅም ጊዜ ቢሆንም እኔ ግን አሁን በአለው ስርአት ላይ ትኩረት አድርጌ አለሁ።እናንተም የአለፋትን ስርአት በራሳችሁ መነፅር ከእውነት ጋር ፈትሹ።

ኢትዮጵያ(ጰ) ነኝ!

With FSHSM and HA !

# አብይ አህመድ የምን እንቁላል ነው?

# አብይ አህመድ ማን የጣለው እንቁላል ነው ?

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ለ **27** አመታት ተጨቁኼ አለሁ፣ተሰድጄ አለሁ፣ታስሬ አለሁ፣ተርቤ አለሁ፣ወዘተ እያላችሁ በልጆችህና ይወክሉኛን

የምትላቸው ሙህራን እና አክትቪስት እየመረጥህ፣ እየደገፍክና ልጆችህን እየሰዋህ ስትታገል ቆይተሃል ሆኖም ሚያዝያ **2010** ዓ.ም**!"**

1. ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው!
2. ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ!
3. ግንቡን አናፍርሰዋለን/ ድልድዩን እንገነባወለን! ምን አፍርሶ ምን ምን እንደገነባ ስለማላውቅ ነው
4. አዲሱን ወይን በአዲስ አቅማዳ!
5. መደመር!
6. ፍቅርና ይቅርታ!
7. እንቁላል ከውስጥ ሲሰበር ህይወት ነው! ......የመሳሰሉትን መፎክሮች ይዞ መሪ መጣልህ ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የንጉስን አቀባበልህን ራስህ ታውቀዋለህ እኔ አልነግርህም ነገርግን ጥያቄ አለኝ፣ ድጋፍህና አቀባበልህ፣

1. የታገልክለት መሪ መጥቶልህ ነው?

2. ልጅህን የሰዋህለት መሪ መጥቶልህ ነው?

3. ቁምጣ አድርገህ ጫካ የገባህለት(ግንቦት 7 የአሁኑ ኢዜማ፣ኢሳቶች ሁላችሁም ባትሆኑም) መሪ መጥቶላችሁ ነው ?

4. ብዙ የታገልክለት ትግል ፍሬ አፍርቶ ነው?

5. የጣልከው እንቁላል ሰብሮ ወጥቶ ነው?

6. የተረኝነት ስሜት ተሰምቶህ ነው? ወይስ እየተበቀልክ ነው? (ህወሓትን)............Face the ugly truth!

ለማንኛውም መልሳችሁን ተወያዩበት የእኔ የዛሬው ርዕሴ ግን፣

## አብይ አህመድ ማን የጣለው እንቁላል ነው?

በመጀመሪያ ስለእንቁላል ትንሽ ልበላችሁ እንቁላል ከውጭ ሲሰበርም ህይወት ነው ዋናው ቁም ነገሩ የምን እንቁላል ነው መሆን አለበት ፣ማን የጣለው ነው?

ለምሳሌ የዶሮ እንቁላል ከውጭ ሰብረህ ነው፣ ምግብ አድርገህ የምትበላው ስለዚህ ለአንተ ህይወትህ ነው፣ ካልገባችሁ ሚስቶቻችሁን፣ እናቶችህንና እህቶቻችሁን ጠይቁ ለማንኛውም ገብቶሃል።

ሌላው የዶሮ እንቁላል በኢንኩቤተርም ይሁን እናቲቱ ማለትም ዶሮዋ ታቅፋው ቀኑን መድረሱን ስታውቅ ወይም ቀኑን ቆጥረህ ከውጭ ብትሰብረው ለዶሮው ህይወት ነው።

ይህ ለሰው ልጅም ይሰራል በተፈጥሮ ምጥ መውለድ ፣ኢንዱውስ ማድረግ፣አሲስት ማድረግና ቀዶ ጥገና እነዚህ መንገዶች ከጽንሱና ከእናቲቱ ሁኔታ በተፈጥሮ ሲጀምር፣ ሌላው በመድሃኒቶች ምጥ ማስጀመር ነው፣ሌላው የውስጡን በውጭ መርዳት ነው፣ሌላው ቀዶ ጥገና ነው።

ማዳን ሲኖርብህ ደግሞ ቀደህ ትሰፋለህ (ከስር ነቀል ፖለቲካ ለውጥ ጋር አንድ ነው ማዳን ካለብህ ህገመንግስቱን ቀደህ ትፅፋለህ አንተ ፈፃሚ ነህ የኢትዮጵ ህዝብ ሊፈርምልህ ይገባል።ዝም ብሎ ቀዶ ጥገናም የለም ጉዳዩን አሳምነህ ነው።) **the people must be autonomous**. ስለዚህ ህይወት በብዙ መንገድ አለ።

በዚህ መሰረት የሌሎችን እንቁላል በዚሁ ተረዱት ለምሳሌ የእባብ ዕንቁላል አትበላውም ከውጭም ቢሰበር ያው እባብ ነው አይበላም የተወገዘ ነው፣ ከውስጥም ቢሰበር ያው እባብ ነው። የእንቁላል ጥናት አደረግሁባቸው። በወሬ  ወደ ነፈሰበት አትንፈሱ ነው ዋናው ቁምነገር።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ዝም ብለህ አታጨብጭብ ትግልህ ማፍራቱንና የጣልከው እንቁላል መሆኑንና ፀሎትህ መድረሱን እርግጠኛ ሁን በቃላት አትሸወድ።የጣልከው እንቁላል እንኳን ቢሆን ተረጋግተህ እይ ቢቀይሩብህስ፣ደመነፍሳዊ ድጋፍ አቁም።ተግባርን ጠብቅ።ፖለቲካው እንዴት እየተገነባ እንደሆነ ማወቅ ያስፍልጋል ሀሰተኛው መሲህ(666) የሚያሳስተን እንደዚህ ነው የምትመረምርበት ግዜ ሳይሰጥ ካስጨበጨበህ አበቃ ንሰሃ የሚሰጥህ ላታገኝ ትችላለህ።

ለውድፊቱ ነው አሁን ግን ቶሎ ንሰሃ ግባ።ለሊት ስልጣን ይዞ ጠዋት sound track ከለቀቀልህ ሲዘጋጅ ኖሮ የመጣልህና የራሱን ሐዋሪያትና ወንጌል ይዞልህ እንደመጣ መገመት ነበረብህ።ባለትንቢት ነኝ ሊል እንደሚችል መገመት ያስፈልጋል።ባለትንቢተኛ ነው ብለህ ካመንህ ደግሞ ትንቢቱ ከማን ነው ብለህ መመርመር ያስፈልጋል።

እኔ የማዝነው **27** ዓመት ታገልኩልህ በሚሉህ ተደማሪዎች ነው፣ጫካ ገባንልህ ባሉህ ተደማሪዎች ነው።ለራሳቸው ነው የታገሉት ለሆዳቸው፣ለክብርና ስልጣን ፍለጋ።

ምክንያቱም ችግራችን ሲስተም፣ህገ መንግስቱ፣የተቋም ግንባታና የመሳሰሉት ሆነው ሳለ የሚያሰራህ ሲሰተም ሳታገኝ ካልጣልከው እንቁላል ጋር የተደመርከው ለምንድን ነው? ጠላትህ ማን ነበር? መለስ ዜናዊ ፣በረከት ስምኦን ፣ታደሰ ጥንቅሽ፣ ህወሃት.........ወዘተ

ስለዚህ አብይ አህመድ ማን የጣለው እንቁላል እንደሆነ ማወቅ ነበረብህ የአብይ አህመድ እንቁላል ለመሆን ከመቸኮል። ያው ሲፈልግ ይፈለፍልሃል ወይም ይበለሃል ህይወት ትሆነዋለህ። ለማንኛውም አብይ አህመድን ማን የጣለው እንቁላል ነው?

1.መለስ ዜናዊ

2.በረከት ስምኦን

3.ህወሃት በጋራ

4.አባ ዱላ ገመዳ

5.ለማ መገርሳ

6.ህወሃት በጋራ በነገራችን ላይ ህወሃት ማለት አልወድም ኢ.ህአዴግ የጣለው እንቁላል

7.ፒኮክ የጣለችው እንቁላል ወይስ

**8.** የእባብ እንቁላል

9. እናቱ በትንቢት የጣለችው እንቁላል

10. የኢትዮጵያ ህዝብ የጣለው እንቁላል

በነገራችን ላይ የፒኮኩ ኃውልት ማስመለኪያ ነው። ንጉሱ አለባበሱን በሂደት እንደ ፒኮክ ለማድረገረ ይሞክራል ጠብቁ። የቤተ መንግስት በር ጠባቂ ነች the gate keeper.

በተለያዩ ሀገራት በህንድ፣በግብፅና የመሳሰሉት ሀገራት በተለያየ መንግድ የፒኮክ ሀውልት በማስራት በቤተ መንግስታቸው በር ያስቀምጣሉ ርኩስ መንፈስ በሃውልቱ በማሳደር የፒኮኳን ባህሪ እንዲያላብሳቸው ግብር እየገበሩ መንበራቸወ ያስጠብቃሉ እንደፈለጉ እየፈነጩ ህዝቡን አንገት በማስደፋት ተደማሪ እያደረጉ ገዝተውታል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ማንም መንግስት እየመጣ የእምነቱን ሐውልት የሚገነባብህ አትሁን ሊያስገዛህ ነው በሰይጣን።

መጀመሪያ መሪህን እወቅ ከማን እንደሆነ ከእግዚያብሄር ወይስ ከሰይጣን ምክንቱም ሰይጣናዊ መንግስቶች እንደነበሩ አትዘንጋ እንደ ዲዮቅልጥያኖስ፣ናቡከደነፆረ ወዘተ የነሱ ሃውልቶችት የማን ነበር፣ መልሱን ለእናንተ።

በነገራችን ላይ አብይ አህመድ በፒኮክ ፋንታ አንበሳ ቢያስገነባ ደስ የሚላችሁ ብዙ ኦርቶዶክስ አላችሁ ችግሩ ግን መሪው ከመንፈስ ቅዱስ ካልሆነና አንበሳው መስቀል ካልያዘ ያው ሽህ አንበሶ ነው።

በእግዚያብሄር ትዕዛዝ  ከሆነ ግን ችግር የለውም ሊቀ ነብያት ሙሴም በንሃስ የእባብ ሀውልት ስርቷል።

ጨዋታው ማን አዘዘህ ነወ? ሌላወ መታወቅ ያለበት ፓርክ እየተባለ በሚገነባው የሚቀመጡ የተለያየ ፍልፍስፍ የተሰጣቸው ምልክት ማጤን ይገባችኃል።

ለምሳሌ የሉሲፈር ሁሉን የሚያይ አይን በኢትዮጵያውያን ቡናማ አይን መጥቶልሃል። ፓርኩ ላይ ያለውን የእንቁላል ፍልፍስፍና፣የሚደንሰውን ውሃ እንቅስቃሴ ጭምር መርምር፣ሁሉንም አርክቴክቸራል ዲዛይን መርመር።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ይህን የምልህ ለምን እደሆነ ታወቃለህ አለምን እየመራት ያለው **Brand and symbol** ነው።ርኩስ መንፈስ የሚገዛን **Brand and symbol** ላይ በማደር ነው።ታውቃለህ ሁሉንም  ችግሩን እንዳትናገር ትታፈናለህ። በርኩስ መንፈስ አቤት አቤት ትላለህ።

ለምሳሌ የሰንደቃላማችንን ፔንታግራም (ባለ ቀንዳሙ ፍየል፣ ባፎሜት ነው ) በብዙ ብራንዶች ተዋርሰነዋል። በእግር ኳስ፣**music Idol** ወዘተ፣ሄክሳግራም፣ትርያንግል ፣ፒራሚድ ወዘተ መርምሩ ንቁ።በነገራችን ላይ የሶስት ማዕዘን ደራሲ ለምን ርዕሱን መረጥከው፣ዐይኑንስ ማን ነው?

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ሌላው ምሳሌ ንቅሳት ነው እባብ ስትነቀስ የእባብ መንፈስና ባህሪ በውስጥህ ታሳድራለህ። ስለዚህ ንቅሳቶቻችሁን መርመሩ ከውጭ የመጣ ትርጉሙን የማታውቀውን ዝም ብለህ አትነቀስ።

በኃይማኖትህም መፈቀዱን አረጋግጥ ምክንያቱም መስቀል ነው፣ የተነቀሰኩት ሳይሆን ቀለሙ የተቀመመበትም ይወሰወነዋል።**the Ink matters.** መነቀሻ መሳሪያውም።

ሌላው መታወቅ ያለበት የሠይጣን መንግስት ስልጣን ከያዘ መንበር ጠባቂ አጋንንትና እነሱ ጋር ግንኙት ያላቸው ባለ አውሊያዎች፣ባለዛሮች፣ጠንቋይ፣የረከሰ ደብተራ፣ቃልቻ፣ዲያቆን፣የረከሰ መርጌታ፣ሸህ፣ባለውቃቢዎች የመሳሰሉት መኖራቸውን መታወቅ አለበት፣ እነዚህ የኢትዮጵያ ሰክሬት ሶሳይቲዎች ናቸው። ከውጭ ጋር ግኑኝነትም አላቸው ስለዚህ የዘመኑን አስነጋሺዎች በያለት አሸንፈን የእግዚያብሄር መንግስት እንዲመጣ መፀለይ አለብን።

ሌሎቹን እናንተ ኢትዮጵያውያን ተወያዩበት የእኔ ፅህፍ ሀይላትነው። ይህንን ፅሁፍ ለዘመድኩን በቀለ ነጭ ነጩን ፣ ለ ኢትዮ **360** ፣ለቴዲ ርዕዮት እና እነሱን_ለመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን ለውይይት ለኢትዮጵያ ህዘብ እንዲያቀርቡት በትህትና እጠይቃቃለሁ።

ይህ ፅህፍ የደረሳችሁ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲደርስ አድርጉ።ወደ ሌላ ወሰድኳችሁ ወደ ርዕሴ ልመለስ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ምንም የተቋም ልዩነት በሌለበት፣የህገመንግስት፣የአገዛዝ ስርአት ለውጥ በሌለበት የኢህአዴግ እንቁላል ከውስጥ ሰብሮ ሲወጣ ወላጆቹን ኃጢያተናኛ አድርጎ እራሱን ያፀደቀ መሪ ነው እያስተዳደረን ያለው።

ምክንቱም የማን ልጅ ሆኖ ነው ራሱን ባለወጠበት አገሪቱን አራት(the big four) ሆነው ሲያስተዳድሩ የነበሩት ሌሎቹን ክልሎች አናሳ አድረጎ ኢህዴግ ለ ለ 27 አመት ሲመራ የነበረው ተጠያቂው አራቱም ድርጅት እንጂ ደመቀ መኮን፣ገዱ አንዳርጋቸው ነፃ ሆኖ በረከት ስምኦን የሚታስርባት አገር አይደለችም፣ ፍትህ እኩል ነው። ደመቀ መኮንን የበረከት እንቁላል ነው።

ስለዚህ ሁሉም የህወሐት እንቁላል ናቸው ደም አለባቸው እራስን ለማንፃት ወላጃቸውን የቀን ጅብ በማለት የኢትዮጵያን ህዘብ confussed and conviced በማድረግ ህዝቡን አስጨብጭበውት የቀንም የማታ ጅብ ሆነው አረፉት።

ያለ ምክንያት ደጋፊ ተደማሪ መሆን ወይም ፍርፋሪ መቅመስ ፍትህን ያዛባል። ስለዚህ እውነትን እንመርምር።

ለምሳሌ በአሁኑ ሰዓት ብልፅግና የሚባል ፓሪቲ አገሪቱን እየመራ ነው። ደመቀ መኮንን ወይም ገዱ አንዳርጋቸው እንቁላሉን ሰብረው ጠቅላይ ሚኒስተር ቢሆን እና ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈፀሙትን <u>የዘር ማጥፋት ወንጀሎች</u> ተጠያቂው የኦሮሚያ ብልፅግና ነው ቢሉ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆ ብለህ ካጨበጨብክ ድምርህ ዜሮ ነው።በተጨማሪም ለአብይ አህመድ፣ለሽመልስ አብዲሳ የእስር ደብዳቤ ቢያወጣ የየኢትዮጵያን፣የኦሮሞን ህዝብ መናቅ ነው።

ይህ ነው የትግራይ ህዝብ ችግር አብረህ ስትበላ ኖርህ፣በቤታቸው አሳድገውህ፣እንቁላላቸው ሆነህ የቀን ጅብ አልካቸው አየህ ስም መጥራት አለብህ ደብረ ጽዮን የቀን ጅብ ማለት አለብ (ይቅርታ ደብረ ጽዮን ምሳሌ ነው።)

ይህ ጅምላ ስድብ የፖለቲካ ፍጆታ ነው።ተደማሪዎች ሆይ አያችሁ እውነቱን ስትስቱ እኔ ፖለቲከኛ አይደለሁም የማንም ፓርቲ ደጋፊ አይደለሁም።**I am a disciple of the truth.**

ስለዚህ የቀን ጅቦቹ ወላጅ አላቸው ቤተሰብ አላቸው ጅብም ብትሆን ለናትህ ልጅ ነህ። ስትናገር መጠንቀቅ አለብ የህወሃት ህዝብ እና የትግራይ ህዝብ አንድ አይደሉም የምትሉት እንዴት አወቃችሁ ጥናት አድርገሃል ወይስ እኔ አውቅልሃለሁ የሚል አባዜ ነው።

ቢያንስ ከደርግ ጋር በተደረገው ትግል ልጃቸውን የገበሩለት ነው።አየህ እነሱ እራሳቸው ህወሐት እና የትግራ ህዝብ አንድ አይደለም ሊሉ ይገባል።አብይ ለኦሮሞ ህዝብ ያልሆነ፣ለአማራው ያልሆነ፣ለአፋር ህዝብ ያልሆነ በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያልሆነ ለትግራይ ህዝብ አይሆንም።

ህወሃትን የቀን ጅብ ስትል ሙሴን፣ኃየሎም አርአያን አስብ፣ማርታን አስብ ለትግራይ ህዝብ ታግለው ፣ለኢትዮጵያ ህዝብም ታግለው ትግራይም ኢትዮጵያም ሆነው አልፈዋል።ታሪክ ለመስራት ብለህ ታሪክ ሰሪዎችን አትንካ የትግሉ ሂደት ተገቢ ነወ ወይስ ስህተት እሱን ማጥናት አለብህ።

እያልኩህ ያለሁት አንተ ለኦሮሞ ህዝብ ማንም አይደለህም ማለት ነው። ምክንያቱም ኦህዴግና የኦረሞ ህዝብ አንድ አልነበረም። ስለዚህ የኦረሞን ህዝብ ከድተኃል።

ብአዴን፣ደህዴንም ሁላችሁም ህዝባችሁን ከድታችኃል። ህወሃት ለወላጆቹ ታማኝ ነው።የቀን ጅብ ብትሉትም።

ለእናንተ ለተደማሪዎች ህዝብ ስም ያወጣላችሁ። ምክንያቱ እየኖርክ ያለኸው የብሄር ፖለቲካ ነው።የብሄር ፖለቲካ እየኖርክ ህወሀትና የትግራይ ህዝብ አንድ አይደለም ማለት አትችልም የሚቃወሙትም ትግራውያን ቢኖሩም ።ሌላው ህወሀት የሚለው ስም ለትግራይ ህዝብ ብራንድ ነው ።እየተገዙበት ያለው ስርአት እንጂ ትግራቸው ሊሆን የሚችለው ስሙ አይደለም ።

ህወሐት ወደ ትግራይ ብልፅግና ተቀይሮ ቢሆን ለትግራይ ምን ጥቅም ነበረው? ደብረ ጽዮንን በአረጋዊ በርሄ በመተካት የመደመርን ወንጌል ማስፋፋት እንጂ ሌላ ምንም ጠብ አይልም ።ችግራችን ስምና መሪ ማን ሆነ አይደለም ።አገር የምተመራበት፣መሪ ሲያጠፉ ለፍርድ የሚያቀርብ ስርአት ያስፈልጋል ።

ዲያስቦራው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ለምሳሌ ኔሽን የገነቡ አገሮችን ተመልከቱ፣ተጠያቂ የሚያደርጉ ስርአቶችን ገንብተዋል ።ስለዚህ ሀሳቦች ናቸው ለምርጫ የሚቀርቡት የተሻለውን ህዝብ ይመርጣል ። ሲያጠፉም ተጠያቂም ነው ። ስለዚህ የኢትዮጵያወን ችግር ያለፉት መሪዎች ያልሰሩትን የቤት ስራ አሁንም አለመሰራቱ ነው ። የእኔ ጥቄ ብቻ አይደለም የነ ልደቱም ነው ። ይሰሙ ።

የአሜሪካውያን አያቶቻቸው ዩኤስኤን ገንብተውላቸወል ። አዲሱ ትውልዳቸው የተሻለ የህዝብ አስተዳደር ይዞ በምርጫ ተወዳድር በዲሞክራሲ ይመራል ።

የእኛ አያቶች ያወረሱን <u>ኢትዮጵያን</u> እንጂ <u>ኢትዮጵያዊነትን</u> አይደለም ።ምክንቱን የኦነግን፣የጃዋር፣ወዘተ ጥያቄ ሳትመልስ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ።ጥያቄአቸውን ስላልመለስክ በሚያደርጉት ትግል ለጥያቄአቸው መልስ ለማግኘት ለሚጠፋት ነፍሶች እጅህ አለበት ።በተዘዋዋሪ መንገድ የአማራውን ደም የምታስፈስሱት እናንተው ሚኒሊካውያን ናችሁ ።መጀመሪያ የሚኒልክን ንፅህንና አረጋግጥልን ።ስለዚህ ኢትዮጵያውያን መገንባት ያስፈልጋል ።ሊዘህ እኮ ነው እያንዳዱን ኦረሞን ብትፍቁት ኦነግ ነው የምትሉት ።ችግሩን ታውቀዋለህ ማለት ነው ።

የዜግነት ፖለቲካ የምታራምዱ እንደ ethio 360 ዎች ትግላችሁ ደስ ይላል ። ነገር ግን ለምሳሌ ከናንተ አንዱ የኢትዮጵያ መሪ ቢሆን ኢትዮጵያን መምራት በጣም ይቸገራል ።

ኤርምያስ ለገሰን የአሜሪካ ፕሬዝዳንነት ብታደርጉት ለመምራት ለእሱ በጣም ቀላል ነው ። ለምን የሚለውን መልሱን ኤርምያስን ጠይቁት ። እውቀት አይደለም ችግራችን ጥናት ይደረግበት ችግራችን ።

እያልኩህ ያለሁት መጀመሪያ Build the nation and the system that govern us.ከዚያ በኃላ መደመር፣ውህድ ማንነት፣የዜግነት ፖለቲካ ....እያልክ መወዳደር ትችላለህ ።

አወ ውህድ ማንነት ነው ያለን ከሃማኖት እስከ ቢሄር ይህ ስለገባህ መደመር ሳይሆን የሚያወጣን ውህድ ማንነት ነው ብለህ ውህድ ኢትዮጵያ ብለህ ብትመጣ ያው መደመር ኢትዮጵያ ነው ።

ከእከከልኝ ልከክልህ ፖለቲካ ውጣ በአሁኑ ዘመን ማንም ኢትዮጵያዊ የሆነ አርትቲስት፣ፖለቲከኛ፣አክትቪስት፣፣፣የለም ።

ስለኢትዮጵያ የሚያወራና የሚዘፍን ግን ሞልቷል ።

ለምሳሌ ቴዲ አፍሮ የኢትዮጵያውያን ጀግና አይደለም ፣ምክንቱም በስንቱ የኦሮሞ ህዝብ ልብ ውስጥ ገብቷል ።ይህን የሆነው ለፖለቲካችን መልስ ስላልሰጠን ነው ። <u>ጀግናየ የምትለውን የምተሰዋው እራስህ አነተ ነህ</u> ።

ጥቁር ሰወን ስለዘፈነ ለፖለቲካ ፍጆታ እየተጠቀምክበት ለመሰዋት ታዘጋጀው አለህ ።የቄሮን አመለካከት ሳትመልስ ቄሮ ያወገዘውን ማድነቅ ቄሮን ኢትዮጵያዊ አይደለህም ማለት ነው ።

ቄሮም ችግርህን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ሲገባህ በስምህ የፈሰሱ ደሞችን አለብህ ። ሻሸመኔ፣ቡራዮ፣ሀረር በመላው የኦሮሚያ አከባቢዎች ለአፈሰስከው ታሪክ ሀውልት የሰው ልጅ በጭንቅላቱ ገንብቷል ።ሲመቸን አንድ ቀን እኛም ሀውልት እናቆማለን ። ስለዚህ በዳይም ተበዳይም ነህ የሚስታርቀን ያስፈልገናል ።

ከዚህ በኃላ አደራ ጥያቄህን በሰላማዊ ትግል አድርግ የሚመራንና ሲመሩን የነበሩት እንጂ ችግራችን ብሄራችን አይደለም ።ሌላው ቁስላችን ሳይታከም የሰውን ቁስል መንካት መናቅ ነውና ተጠንቀቁ ።ሁላችንም ይቅርታ መጠየቅ ያስፈልጋል ።

ቴዲ አፍሮ እያልኩህ ያለሁት መልሱ ያስተሰርያል ነው ።እጅ የሚቀሰረው ብዙ ነው፣ ማን ነው የሚያዋጣን፣ማነው ትክክል፣አንዱ በአንዱ ላይ እጁን እየቀሰረ ነው ።

ይህ ከገባህ ጥቁር ሰው የሚለው ስራህ እጅ መቀሰር ማለት ነው ። አምነህበት ከሆነ መብትህ ነው ። ኢትዮጵያዊ መሆን ከፈለክ ጥያቄዎቻቸውን አብረህ መልስ፣መልስ ካጣህ ይቅርታ ጠይቅ ።

ቴዲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ከመድረክ ስራዎችህ የእኔ የምንግዜም ምርጥ የምትለው የትኛውን ግዜ  ነው**?**

እያልኩህ ያለሁት በስራዎችህ ስንት ፐርሰንት የኦረሞ ብሄር ደጋፊዎችህ ተገኝተዋል**?** ለአንተና ለደጋፊዎችህ ላይገባችሁ ይችላል።  ሁልህም ራስህን ፈትሽ ኦሮሚያ ተግንጥላብሃለች።

So what ever your stage performance is. With out you I am in pain you must say.

አንተ የ 110 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ነህ።ትግልህን ጀምር የራስህን ደጋፊ ብቻ ይዘህ አትጓዝ።ተሰሚነትህን ተጠቅመህ ችግሮችን ለመፍታት ታገል። ጥቁር ሰው ላይ oromo beats መጠቀምህ ለምን ይመስልሃል? አንተ ውስጥ Oromo beats አለ።ደጋፊዎችህ እንደሚጫጩ  አውቃለሁ።የሰራሃቸውን ስራዎች ገምግም የአንተኑን አስተሳሰብ ነው እያስረዳውህ ያሁት።

ስራዎችህ ኢትዮጵያዊ ናቸው ሀሳብህን ግን ጎራ ተለይቶበታል።ስለዚህ እነዚህ ጎራዎችን ለማቀራረብ ትልቅ ስራ አለብህ አደራ።ችግሮች ከተፈቱ you will be 11o millions' people Man

በነገራችን ላይ ቁሮ ከዚህ በኃላ የቴዲ አፍሮ ጠባቂ ነህ ። መጥፎ ታሪክ፣አይቀጥልም በህይወት እያለ ይቅርታ ሊጠይቅህ ወይም ይቅርታ ልጠይቀው ይገባል ።

<u>ይህንን ስታደርግ ብቻ ነው የአጫሉን ሁንዴሳን ትግል የምታሳካው ከዚህ ውጭ ተሸንፈሃል</u> ።

ሌላው በ **you tube** ለህጻናት መልዕክት የምታስተላልፉ፣ የኦነግን ባንድራ የሚይዙና አነግን፣ህወሃትና ባንድራውን የሚዙትን እንዲጠሉ እያደረኩ ነው የማሳድጋቸው ትላለህ ፡፡ሌላ ኩላሊት የሚወጣ ትውልድ እየገነባህ ነው ፡፡የአንተ ልጇ ወደፊት ህወሃት በበማለት ኩላሊት ይበላል ፡፡ ነጩን ስታወራ ይህንንም ጨምርበት ፡፡

ሌላው ትንቢት እያልክ የምታወራውን፣ ትንቢተኞቹ አባቶቼ ለምትላቸው ጥያቄ አለኝ ፡፡ እግዝያብሄር ተገልፆላቸው ይህንን የሰቆቃ ትንቢት ሲገልፅላቸው ለምን አላማለዱንም? አባታችን ኖህን አስብ ለምን በግልፅ ወጥተው ንስሀ ግቡ አላሉንም፣መርከቡን ለምን አልሰሩንም፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣

አባታችን አብረሃም እግዝብሄር ሰዶምና ጎሞራን ሊያጠፋ ሲል የአብረሃም ምልጃ አስታውስ ፡፡ወይስ ሁላችንም ጠፍተናል ፡፡

ከዚህ ውጭ እጅህን እየቀሰርክብኝ ነው ፡፡ በግልፅ ይቅርታ ጠይቅ ፡፡ሁላችንም በድለናን፣ተበድለናል ፡፡

አቶ የሺዋስ አንተ ራስህ በድለሀኸኛል ፡፡በዳይና ተበዳ አጣን ማለትህ አንደ ምሳሌ ነው ፡፡ይቅርታውን ጀምር ፡፡

በጣም የማዝነው ለኢትዮጵጵ በፊሰሱ ደሞች ነው ፡፡ የውጭ ባርነትን ድል አድርገን የውስጥ ባሪያ በመሆናችን ፡፡ወንድምህን እየገደልክ ግብፅ ልትመጣ ነው ስትባል ሆ ፡፡እስኪ ለፍቅር ሆ እንበል ያን ግዜ ግብፅ ዜሮ ናት ፡፡ለምን እንደምትደፍረን ሊገባችሁ ይገባል ፡፡

የወልደያና የአከባቢው ህዝብ ሆይ መንገድ ዘግተህ ነበር፡፡ ታሪክ ፅፈሃል ነገ ትጠየቅበት አለህ በሰማይም በምድርም፡፡ አሁንም የኢኮኖሚክ ሰንክሽንና ጦርነት የምታወሩ እንደ አኖሌ አይነት ሐውልት እየገነባችሁ ነውና ተጠንቀኩ፡፡ ጦርነትም ከጀመርክም ከፅዮን ማርያም ጋር ነው ፡፡

ስለዚህ በጀታቸውን እንዳትነካ፣ኢኮኖሚካል ሰንክሽን አያዋጣም፡፡ እንኳን ምርጫ መገንጠል መብታቸው ነው፡፡አደራ የትግራይ ህዝብ ሆይ መገንጠል አይታሰብም፡፡

የኢትዮጵያ 7 ኛው ንጉስ ኤርትራ ለምን እደተገነጠለች ታውቃለህ? ኦነግ ኦሮሚያን ለመገንጠን ለምን እንደፈለገ ታውቃለሁ? በሰው ጭንቅላት ላይ የታነፁ የጥላቻ ሀውልቶች ናቸው።እነሱ በጊዜው ቢታከሙ ኑሮ ኤርትራ የኢትዮጵያ ነበረች ።አነግ የሚባልም ፓርቲም አይኖርም ነበር።

ስለዚህ አገር ገንጣዩ አንተ፣ተደማሪዎችህና አላዋቂ ፖለቲከኞችህ ናቸው።መለስ ዜናዊ ኤርትራን አስገነጠለ አትበል ለምን፣እንዴት ብለህ ጠይቅ።

የኢሣያስ አፈወርቅንና የኤርትራን ህዝብ ፍላጎትን ማወቅም አለብህ አትፍረድ።ለኦነግ ለምን አልሰራም ጥናት አደርግ።**YOU MUST UNDERSTAND JUNGLE SURVIVAL AT WAR**,

ትንሽ ሃሰብ ልስጥህ ሻቢያ የራሱ አላማ ነበረው፣ህውሃትም እንደዛው።የውጊያ ቀጠናቸው የተለያየ ነው።ደርግ ህወሀትን ሲያዳክመው ሰርቫይቭ የሚያድርገው ከሻቢያ ጋር በመመሸግ ነበር ሻቢያም እንደዛው ስለዚህ አንዱ ለአንዱ አላማ ታግሏ.።

ህወሀት ራሱን update ሲያደርግ ሻቢያ አልቻለም። ስለዚህ ችግራችን background ነው። መሰረቱን አክም። Heal the source.ብሄር ብሄረሰቦችን ህመማቸውን አክምና ኢትዮጵያዊ መሆኑን፣ኢትዮጵያነት ሱስ መሆኑን ተናገር።

ምክንቱም ለ 27 ዓመት የተመራነው በብሄር ፖለቲካ ነው፣የ 27 ዓመትችግራቸወን ሳትመልስ አዲስ ወይን በአዲስ አቅማዳ አትበል።የከረመ ወይንና የከረመ ፍቅር የሚወድ አለና ነው።

ወይኑንም አቅማዳውን የመቀየር መብቱ የኢትዮጵያውያን እንጂ የአንተ መብት አይደለም።ማን የጠመቀውን ወይን ነው የምታወራው። ህዝብ ነው የራሱን ወይን መጥመቅ የሚገባወ። አየህ አንተ የጠመከወን አዲስ ወይን በአሮጌ አቅማዳ ሞላኸው በቃ ፈነዳ። ጄኖሳይድ ተፈፀመ። ማን ነው አሮጌ አቅማዳ ህዝቡ/መሪዎች። ህዝብ አሮጌም አዲስም አቅማዳ አይደለም።

ምክንያቱም ህዝቡ ወይኑን ጠምቆ ስለማያውቅ አቅማደ አላዘጋጀም።ምንም እንኳን ባለአቅማዳ ቢኖሩም።ስለዚህ ባለወይኑም አንተ፣ባለአቅማዳውም አንተ። ቀዳማዊት አይጥም ወይንሽ ተፋነው፣ትንሽ ቀመስነው አቃረን አስመለሰን። ካልተሸክምክ ብለሽ ደም በዛብሽ።

ህዝብ ሆይ መሪ፣ ንጉስና መንግስት የምትፈጥረው አንተ ነህ።ወይኑን ጠማቂው አንተ፣አቅማዳ አዘጋጁም አንተ፣ኢንጅነሩም አንተ እንደ አባይ፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣

<u>ከዚህ ውጭ አብሮ መኖሩን ለኛ ካላለልን የቴዲ አፍሮን ጋብዝሀአለሁ።</u>

ንጉስ ሆይ በነገራችን ላይ ትመቸኝ አለህ ሃሃሃሃ አንተ እኮ መፈንቅለ መንግስትን በቸሻፕ ያከሸፍክ  ጀግና መሪ ነህ።መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ የሞከሩ፣የተሞከረባቸው ዜጎች በአሉበት ሀገር ዲሞክራሲያዊ መንግሰት አገኘን ብለው ካለምንም መሳሪያ ሙብታቸውን ሊጠይቁህ ቢመጡ መፈንቅለ መንግስት ብለህ የት አደረስካቸው ፍትህ  ለመከላከያ የመንግስት ሎሌ ለሆነው።በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ................ምን አለ ወደ ገደል ከምትመራን ሳሩን ከገደሉ አውጥተህ ብትሰጠን።የሴራ ፖለቲከኛ ነህ።

ደም አየፈሰሰ የመንግስትን ትዕዛዝ የምትጠብቅ ወታደርና ፖሊስ።ምን ይደረግ በአድርግ አታድርግ ተተብትበሃል።.

**Don’t be Yes sir only soldier and police.** ለማንኛውም መፈንቅለ መንግስት እንዴት እንደሚደረግና እንደሚከሸፍ መንጌን ጠይቀው።በተጨማሪ ከወታደሮች ጅርባ ማን ነበር። ህወሃት እንዳትል አንተ።

ትንሽ ስለብሄር ፌደራሊዝም እናውራ የብሄር ፌደራሊዝምን <u>የተከበረው የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስተር</u> በኢትዮጵያ ሲመሰርት ፍጽም ስህተት አልነበረም። ምክንያቱም  ለኢትዮጵ ብሎ ወይም ለአህዳዊ ስርአት ሊታገል ጫካ የገባ የለም። አህዳዊ ስርአትን ለመታገል እንጂ።

ለምሳሌ ህወሀት፣ኢህዴን ራሱን ቀይሮ ብአዴን የሆነው፣አነግ፣ደህዴን አ.አ ቢመሰረትም ወዘተ የታገሉት ለትግራይ ህዝብ፣ለአማራ ህዝብ፣ለኦረሞ ህዝብ በአጠቃላይ ትግሉ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ትግል ሆነ ፣መነሻው ህወሃት ቢሆንም ትግሉን ተቀላቅለዋል።ደርግን ድል አደረጉት በዚህ መሰረት ትግሉ የብሄር እኩልነት ለማስፈን እንጂ ድል የመቱትን ስርአት ለመመስረት አይደለም።

እዚህ ላይ ስራ ጥናት መስራት ያስፈልጋል የትኛው መንግስት ልክ ነው። ደርግ ወይስ የታገሉት አካላት ፣የተጨቆነ ብሄር ነበር? ወይስ ለስልጣን ፍላጎት ነው? ህወሃት የተመሰረተው፣ሌሎቹ ብሄሮች ጭቆና አልደረሰባቸውም ፣የተጨቆኑት በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ናቸው ነገር ግን ማን እንደ ኢትዮጵያ ታገለላቸው፣አይ ደርግ ጥሩ ነበር የታገሉት ውጊያ የጀመሩት እነሱ ናቸው የሚሉትን ጥያቄዎችን መመለስ ያስፈልጋል።

ለማንኛውም ብሄርተኛው ቡድን ድል አድርጎ ስልጣን ያዘ ብሄር ብሄረሰቦችን መሰረት ያደረገ ፌደራሊዝምን መሰረተ።በደመነ ነፍስ ከመቃወም መለስ ዜናዊን ከታገለለት፣ጫካ ከገባለት አንፃር ትክክል ነው።

የመለስ ቴክኒካል/ታክቲካል ችግር ግን የኢትዮጵያ ብሄሮች በዳይና ተበዳይ በግልፅ እርቅ ሳይፈፅሙ እኔ አውቅልሃለሁ በሚል አባዜ በራሱ መወሰኑ ነው።ምክንያቱም የረጅም ግዜ ቁርሾ አለ።

ብሄሮች የሆነ ችግር በተፈጠረ ግዜ በብሄር ጎዳ እንደሚደበቁ ግልፅ ነው። ዘመድ ከዘመዱ ብሎ የተረተ ህዝብ ነው። ፈልገት ነው የምትሉ ኃይሎችም አላችሁ።ጥናት ይፈልጋል ለምን እንደፈለገው።

ሌላው ምንም እንኳን ብሄራዊ እርቅ ተደርጎ ቢሆኑም የህዝቡ ንቃተ ህሊና ይወስናል ብሄርን የተረዳበት።ምን መሰለህ መለስ ስለብሄር ያለው ግንዛቤና አንተ የተረዳህበት ይወስነዋል።

ስለዚህ በሁሉም መንገድ መሪውና ህዝቡ የተረዱበት መንገደ አንድ ካልሆነ የብሄር ፖለቲካ ለእኔ አደጋ ነው። ህዝብህን ማወቅ አለብህ።ተስማምተህ ትኖርና ልክ እንደ አሁኑ ዘመን ህወሃትን የቀን ጅብ ስትል ከትግራይ ህዝብ መለየት ይከብድሃል።

ለማንኛውም ህዝብ ከተግባባ ብሄር መሰረት አድርገህ ኢትዮጵያን መመስረት ትችላለሁ፣ኢትዮጵያዊነት እያለ ብሄር ለምኔ ይቻላል፣ ኢትዮጵያ ቅደሚ ብለህ ብሄርን ማክበር ትችላለህ ዋናወ ቁም ነገር ቅድሚያ ለህዘብና ህዝብ አገልጋይ መሆን ያስፈልጋል።

መንግስትና የፖለቲካ ፓርቲዎች የብዝሃኑን ሃሰብ ትታችሁ ለራሳችሁ ሃሳብ የምትታገሉት ለምንድን ነው።ለሃሳብህ ደጋፊ ይኖርሃል የሶሻል ሚዲያ ግሩፕና ቤተሰብ ።

እሰኪ ሁላችሁም  የፖለቲካ አክቲቪስቶችና ፓርቲዎች ከ **110** ሚሊዮን በላይ ህዝብ ባለበት አገር ምን ያህል ደጋፊ አላችሁ። **110** ትተን ሶሻል ሚዲያ ከሚጠቀመው ህዝብ ምን ያህል ይከተላችኃል ።

እኩል ቅርጫ እንኳን ቢሆን ብቻህን መንግስት መሆን አትችልም።

ሁላችሁም ተነጋገራችሁ ብትታረቁ  እና ህዝቡን ብታስታርቁት ኢትዮጵያን ትመሰርታለህ።ከ **110** ሚሊዮን በላይ በጋራ ደጋፊ ይኖራችኃል። ከዚያ በኃላ በሃሳብ የተመሰረተ ፌደራሊዝም ይኖርሃል ወይም የተስማማችሁበት።

በአንድ ላይ ሁኑና አስታርቁን **110** ሚሊዮኑን የእናንተ፣የሁላችሁም አድርጉት፣ተቋም መስርታችሁ ወደ ሃሳባችሁ ፖለቲካ መግባት ትችላላችሁ።ኪዚህ ውጭ የሶሻል ሚዲያ ፌደራሊስቶች ናችሁ። ተቋም ቢኖር እኮ አብይ አህመድ ፍርድ ቤት ቀርበ ነበር።

ከዚህ በኃላ መለስ ዜናዊን የሚወቅስ ኢትዮጵያዊ የግል ችግር አለበት። ምክንያቱም አንተ ማን ነህ**?** ራስህን መርምር።ምንም ኃጥያት ያልሰራ የብልፅግና አመራር መለስ ዜናዊን  በድንጋይ ይውገረው።

ምክንቱም መንግስት ምስረታ፣ስልጣን እንደ ዱላ ቅብብል ነው። ማን ያቀበለህን አገር እየመራህ ነው። ለአንተ ገፅታ ግንባታ የተቀበልከውን ዱላ ይዘህ ሩጫውን ሳትጨርስ ቀድሞ የነበረውን መሪ እየወቀስክ የምትኖረው።

- እንደ ቦልት ሁን የተሰጠህን ዱላ ይዘህ አሸንፍ ዱላውን ያቀብለህ ስህተት ቢኖርበትም።
- ሩጫውን አቋርጠህ  የኃላወን አትተች።የኃላው ከሌለ የለም የፊቱ እስከ ስህተቱ።

ቢያንስ አባይን የደፈረ  መሪ ነው የምትመፃደቅበትን፣አባይ ብሄራዊ ክብርህ ከሆነ መለስ ዜናዊ ብሄራዊ ጀግና ነው።ከዚህ ውጭ ማን ነህ አንተ፣ፍላጎትህ ምንድን ነው። የኃላውን እንዲጠላ አድርገህ መደነቅ የፈለክ።

ለፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ መልዕክት አለኝ።ለምን ኤርትራን ለመገንጠል እንደፈለጉ ይገባኛል ። በጭንቅላታችሁ የተገነባው ነው።የመገፋት ስሜት እንደነበረ ይሰማኛል።ጥያቄአችሁ እስካልተመለሰ ድረስ ለኤርትራ ያደረጉትን ትግልና የነፃነት ድል አከበራለሁ።ነገር

ግን  ከአብይ አህመድ ጋር አይተባበሩ። ለልደቱ አያሌው መታሰር እጅዎ አለበት እየተባለ ነው ። ስለዚህ ባስቸኳይ አስፈቱልን።ሌላ ጥላቻ አይዝሩ። የውስጥ አገዛዝወን በተመለከተ የሚመሩት ህዝብ አለ እነሱ ናቸው ባለመብቶቹ።

ሌላው ጥያቂየ ከኢትዮጵ መንግስታት ኤርትራንና ኤርትራውያንን የሚወድ  እንደ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርም ያለ መሪ አላውቅም መቃብሬ ኤርትራ/አስመራ ላይ ናት ነው። እያለ ሲታገል ከአገር የወጣው።የነበረውን ግፍና በደል አውቃለሁ ምክንያቱ የእናንተም ምርጫ ጦርነት ነበር የሁለታችሁም ችግር ግን የኤርትራ ፍቅር ነው።

ስለዚህ እውነተኛ ፍቅር ከፈለጉ መንጌን ይቅርር በሉት ና የኤርትራ ህዝብ ሆይ ይቅርታ ይደረግለትና መቃብሩን፣ሞቱን የተመኘላትን ኤርትራን፣አስመራን ይጎብኝ። እውነተኛ ፍቅርና ይቅርታ ከፈለጉ ይህ ነው።

ከዚያ ውጭ አብይ ጋር እየተቃቀፉክ ትግራይን መክዳት ልጅህን እንደከዳህ ቁጠረው።የነበሩትን ሴራ ስበሯቸው። ለአብይ የኖቤል ሽልማት ማሟያ ነው የሆንከው።ህይወት አጭር ናት።አንድ ብንሆን ብለህ አስበህ ታውቃለሁ፣አስብበት ዋናው ፍቅር እንጂ መሪ መሆን አይደለም። ጅቡቲም የኢትዮጵ ነበርች ልውቀስ ካልክ ብዙ አለ ዋናው ይቅርታ ነው። እግዚያብሄር አንድ ያድርገን።።።

ከፈለግህ  የኢትዮጵያ ህዝብ የመንም የኛ ነበር። እያልክ ቀጥል ይህን ማሰብ የምትችለው ከዘር ፖለቲካ ስትወጣ ነው።

የኢትዮጵያ ህዘብ ሆይ ያሳለፍናቸው መንግስታት በሙሉና ያሉትም  መሪዎቻችን ጭምር ፅድቅና ኃጥያት አለባቸው።እኛም እንደዛው።

በሁሉም መንግስታዊ ስርአት የተበደልን ህዝቦች አለን ምክንያቱም በህዝብ ስም የራሳቸውን አላማ/እውቀታቸውን ነው የሚጭኑብን። እውቀትህን ለራስህ መጀመሪያ ከህዝብ ጀምር።

ከ **110** ሚሊየን በላይ ህዝብ በሚኖርባት ሀገር ከ **110** ሚሊየን በላይ ሃሳብና ጥያቄዎች አሉ። እነሱን መመለስ እንጂ የሚያዋጣው መደመርና መደመር ብቻ ነው አትበል። እንዴት አወቅህ። ምክንያቱንም ለሀገራችን ችግር ከ **110** ሚለየን በላይ መፍትሄዎች ፈልግ።ከዚህ ውጭ ሁላችሁም **small peer group** ናችሁ።አራት ሃሳቦች መርጣችሁ **3** ቱን ጠማማ አድርገህን አሸናፊውን ንጋት አልክ ቀሽም። ጋኖች በሌሉበት ሆኖ ነው።ለማንኛውም የኢትዮጵያ ጋኖችን ፍታ አባ።

ሌላው ልንገነዘብ የሚገባን የራሳቸውን አላማ ይዘው የሚመጡ መሪዎች ከራሳቸው አላማ አንፃር ልክ ናቸው።የህዝብ አላማ ስለማይኖራቸው አላማቸውን ሊያሳኩ የሚጓዙበት መንገድ ነው ስህተት የሚሆነው። ከራሱ አላማ አንፃር አዶልፍ ሂትለርም ትክክል ነው ችግሩ የተጓዘበት መንገድ ደገግሞ ደም ነው። ስለዚህ የራስህ ጀግና አትሁን።

ሁላችሁም ህዝብን የወከላችሁ ፓርቲዎች፣አክቲቪስት፣ባለሞያዎች ከ **110** ሚሊየን በላይ ጥያቄ አለኝ። መልሱልኝ።ከዚህ ውጭ አውሮፓና አሜሪካ መራሽ እውቀትህን ለራስህ። ከ **110** ሚሊየን በላይ ህዝብ ሳትይዝ ኢትዮጵያ አትበል።

እባካችሁ መጀመሪያ ተቋም ገንቡልን። እኛን የሚመራን የተገነባ ተቋም ነው። ማለትም ሁሉም የኢትዮጵያን ህዝብን ያሳተፈና ያመነበት ተቋም ገንቡልን። አብይ እኮ እየገነባ ነው የምትሉ ተደማሪዎች አትጠፉም። ተቋም የሚገነባው እኮ  ቅራኔ ተፈቶ፣ከእርቅ በኃላ ነው። የሚገነባውም አብይ ብቻ አይደለም ሁሉንም ማሰተፍ አለበት።

ምክንቱም ጃዋርም፣በቀለ ገርባም፣ልደቱ አያሌውም ፣እስክንድር ነጋም፣በረከት ስምኦንም፣ታደሰ ጥንቅሹም፣ክንፈ ዳኘም፣ህወሀትም፣ድሃውም የየጎዳና ተዳዳሪውም ሁሉም ህዝብ ያስፈልጋል። አሲስት መደረግም ያስፈልጋል በውጭ ኃይልም **with caution. This is called assisted delivery,**

የታሰሩትም ኢትዮጵያዊ ናቸው። የታሰሩትም በመንግሰት እጅ ወይም ሴራ እንጂ በተቋም ስላልሆነ ፖለቲካዊ እስር እንጂ ፍትህ አይደለም።

አሳሪም ታሰሪም አንድ ናቸው ደመቀና በረከት አንድ ነበሩ።ያው የዝሆኖች ፅብ ሆኖ ነው። ያሸነፈ ያስርሃል፣ሊገልህም ይችላል። ስም ይሰጥሃል ስሙ እኮ የሁለቱም ነው። ሁሉም ዘርፈዋል።ሙሰኞች ናቸው።ለአማራ ህዝብ <u>በረከት ስምኦን</u> ከደመቀ መኮንን በላይ ጅግና ነው።ወደኃላ ተመለስሰህ የብአዴን ትግል ተመልከት።የበላውን እያበላ ያሳደገው ደመቀና ገዱ በሴራ ለአብይ ሲሸጧቸው ዝም አልክ።ራሳችሁን መርምር። ትግላቸው ትክክል/ስህተት ጥናት አድርግ።

እንዲገባችሁ እሲኪ <u>የእዮብ መኮንን የአየሸውን አይቻለሁ</u> የሚለውን ዘፈን ተጋበዙ።ሃሳቡን እንጂ ርዕሱን እርግጠኛ አይደለሁም ይቅርታ።በረከትና ታደሰ ጥንቅሹ ያዩትን፣የቀመሱትን ደመቀ መኮንንና ደጉ አይተዋል፣በቃ ቀምሰዋል።

ስለዚህ ኃጢያተኛ ከሆኑ ሁሉም አንድ ናቸው።ማንም ማንንም በድንጋይ መውግር አይችልም በእግዚያብሄር አይን ሰዎች ሃጢያተኛ ያሉት፣እንዲወገር የፈረዱበት፣ያወገዙት ትንሳኤውን ቀድሞ ሊያይ እንደሚችል ማን አወቀ።

በዚህ መሰረት ህወሃት ሌላ አንፀባሪቂ ታሪክ ሰርተዋል። ጌታቸው አሰፋና አብይ አንድ ናቸው። ጌች ያየውን፣የቀመሰወን አቅምሶታል።ትግራ/መቀሌ ሳይቀር ወስዶ አመቻችቶታል።ስለዚህ ጌታቸው አሰፋን ለማን አሳልፈው ይስጡ። ወንጀል አያበረታተሁ አይደለም ለማን ልስጠው ፣ፈራጁ ማን ነው።

የተበደለው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ። የበደለህን ማን ነው፣ የሚቀጣልህ አብይ፣ደመቀ፣ብልጽግ፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣

ለምሳሌ አባት በዳይ ልጅ አለው።እንዲቀጣና እዲታረም አጥብቆ ይፈልጋል።እንዴት እንደሚቀጣው እያሰበ ባለበት ሰአት በደል አብሮት ሲሰራ የነበረ ሰይጣን መጣና እስር ቤት ጣለለት አባት መደመር፣መደመር እያለ ወጣ ፣፣፣፣፣፣፣፣፣አዝናለሁ።

የኢትዮጵ ህዝብ ልጅህን በማን እንዳስፈረድህበት እይ።አባትም ልጅም አንድ ሲሆኑ።

የትግራይ ህዝብ ጌታቸው አሰፋ ወንጀለኛ እንኳን ቢሆን ለሰይጣን አልሰጠኸውም ራሴ ነኝ የምቀጣወ ብለኃል።**Double pride, there is time for Hatrick.////////////////////////////**

መደመር ለኢትዮጵያ ምን ይዞ መጣ።እኔ በኢትዮጵያ የመንግስታት ታሪክ የአንዱም ስርአት ደጋፊ አይደለሁም። ምክንቱም የበዳይና ተበዳይ ስርአት ነው። በሁሉም ስርአት ደም ፈሰዋል። ማለትም አሸናፊና ተሸናፊ አለው። **It is win loss way**።

የአሸናፊው ወገን የሆንክ የራስህን ስታደንቅ። ስታሸንፍ ያፈሰስከው የማን ደም ይመስልሃል።አደዋ ላይ ከፈሰሰው ደም በላይ በእርስበርስ ጦርነት የፈሰሰው ደም ይበልጣል።

ስለዚህ የፈሰሱ ደሞች እየጮሁ ነው ፡፡ እኛ ግን ሌላ ደም እናፋስሳለን፡፡ቃየሎች ነን በአቤሎች ደም የምንቀልድ የአቤል ደም እየጮኸብህ፣የሴትንም ደም እያፈሰስን፣ ባይነገስስ ቢቀር፡፡ ደም መፍሱሱን አቁሙልን መጀመሪያ፡፡ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከተመሰረተች ጀምሮ  በግፍ የፈሰሱ ደሞች እየጮሁብን ነው፡፡ጆሮአችሁ አይሰማም እንዴ እኔ ግን ታምሜ አለሁ፡፡

ፌደራሊዝም ፣አህዳዊ ፣ውህድ፣መደመር፣፣፣፣ወዘተ ትለኛለህ የወገኖቼ ደም እየጮኸብኝ፡፡

አህዳዊ አገር እንጂ፣አህዳዊ አትዮጵያ እንጂ፣ አህዳዊ አስተሳሰብ ወይም አህዳዊ የሚል ፓለቲካ አንፈልግም፡፡

አብይ አህዳዊ መንግስት ነው የሚሉት እኮ ልክ ናቸው፡፡ መደመርና ብልፅግና የሚል አህዳዊ አስተሳሰብ ይዞ ነው የመጣለው፡፡ የእኔ ሃሳብ ብቻ ነው የሚያዋጣው የሚል ፓለቲካ ይዘህ ስትመጣ ሁልህም አህዳዊ ነህ፡፡የቱንም ያህል ደጋፊ ቢኖርህ፡፡ሁላችሁም የራሳችሁን ትታችሁ እርቅ አምጡልን፡፡ ሚዲያዎች ራሳችሁ እርቅ አድርጉና እውነትን ተናገሩ፡፡

ከዚህ ውጭ ውሸት የምትናገር ማንም ሁን <u>የእውነት መላእክ አፍንጫህ ላይ ነው፡፡</u> እሱ ዳውን፣ዳውን እያለህ ነው፡፡

ውሸት በተናገርክ ቁጥር ቅዱስ መልአከ ሞት ሊወስድህ እንደመጣ አስብ፡፡ ውሸት ወደዘርህ እየዞረ ነው፡፡ መርገምቱ ለልጅጅህ ነው፡፡

ዛሬ የዋሸኸን ነገ እውነት  ይታገልሃል፡፡

በዚህ ፁህፍ ውስጥ ስማችሁን የጠቀስኩት ምሳሌ እንጂ ሁላችንም አንድ አይነት ከለር መሆናችን እወቁ፡፡

በሌላ መልኩ ከእስማኤልና ከይስሀቅ ነኝ አስተሳሰብ እንውጣ፡፡ ሁለቱም የአብረሃም ልጆች ናቸው፡፡አባታቸው በእግዚያብሄር የተመረጠ፡፡

እስማኤል ምን አጠፋ ለእኔ ቅዱስ ልጅ ነው ወንድሙን የሚወድ፣አባቱን የሚወድ ቃል እግዚያብሄር የገባለት፡፡

ለአዳም የገባለትን ቃልኪዳን ደግሞ በይስሃቅ ፈፀመ፡፡ ቃልኪዳኑ ደግሞ ድንግል ናት፡፡እስማኤል ደንግልን እኮ አልከዳም የዳነው በእሷ ነው፡፡እኛ ነን የእነሱ ልጆች  የተከፋፈልነው፡፡

አስራሁለቱ የእስረኤልን ልጆች ሁሉም ሐጥያት ነበረባቸው።ሌላውን ተውት ወንደማቸው ዮሴፍን ሸጠውታል።

ድንግል ማርያም ብቻ ናት እንጂ በነፍስም በስጋ ብፅእት፣የዘር ሀጥያት ያልተተላለፈባት የለም።ቃልኪዳኑን የፈፀመባት፣ ሁሉም የአዳም ሀጥያት ነበረበት።

ስለዚህ የዳዊት ነኝ የጎልያድ ልጅ አትበል። ዳዊትም ሐጥያተኛ ልጅ፣ፃድቃንም ልጅ ነበረው።ጎልያድም ፃድቃን ልጅ ሊኖረው ይችላል።ምክንያቱም ሀጥያተኛው አዳም በነፍስም ፣በስጋ ብፅእት የሆነች የአምላክ እናት ልጅ እንዳለችው።

ከዘር ውጡ።ከሃማኖት፣ከፖለቲካ ዘርም።ሁሉም የሆነው በቸርነቱ ነው። የሰለሞን ዘር ነኝ ለማለት አትሯሯጥ።

ሰለሞንን ሆነህ ተነገኝ።

እስላሞችም እንደዛው የእስላም ክፍሎችን ታውቁት አላችሁ። የአሊ ነኝ ፣የመሃመድ ወዘተ............

ራስህን እየከፈልክ የኢብራሂምን ደም አታፍስ።

ከገባችሁ የክርስትያኖ፣የመሲ ነኝ እንደሚባለው በሃይማኖትም ተከፋፍለናን።የአንዱን እውነት ሌላው እየከዳ።

**Think twice** ለምን እነደሚባል ታውቃለህ**?** ከአንደበትህ መጥፎ እንዳይወጣ ነው።ምክንያቱም ፓራዳይዝ ታመልጥህ አለችና።

ትንሽ ስለ ኢኮኖሚ እናውራ መንግስት ምስረታ ዱላ ቅብብል ነው። ትንሽ ወደኃላ ብንመለስ ስርአታችን ፊውዳሊዝም ንጉሳዊ፣ሶሻሊዝም፣አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ፣መደመር ብቻ ነው የሚያዋጣን ብልፅግ ወዘተን ይመስላሉ።

ሁሉም የራሳቸው አንድምታ አላቸው።ትንታኔውን ለባለሞያዎች/ለእውቀቱ ባለቤቶች ትቸዋለሁ።

እኔ ስለ ሶሻሊዝም ትንሽ ማለት እፈልጋለሁ ኃጥያቱ እንዳለ ሆኖ  ለእኔ ሶሻሊዝም ለካፒታሊዝ ትራንዝሽን/መሸጋገሪ  ነው፣ ወደ ካፒታሊዝም ስርአት።

ሶሻሊዝም ሀገርህን የምትወድበት፣ህዝብህን የምትወድበት፣የአገርን ሀብት እኩል የምትወርስበት/የምትጋራበት ወዘተ ነው።ነገር ግን በኛ አገር የሆነውን ለእናንተ ትቸዋለሁ። ሀብትን እኩል ለማሰራጨት የሀብት ወሰን መኖሩ አግባብ ነው ችግሩ ግን አፈፃፀሙ ነው የደርግ ካድሪዎች የራሳቸው የሀብት ማከማቻ አደረጉት ፊውዳሎ ሶሻሊስት አደረጉት። በአግባቡ  ቢሰራበት ግን የተመጣጠነ ሀብት ሁሉም ህዝብ ይዞ ወደ ካፒታሊዝም መሻገር ይቻል ነበር።

ግንቦት **20/1983** ዓ**.**ም ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ ህዝቡን ኢኮኖሚ ሁኔታ ሳያጠኑ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ባልተሰራበት አገር ምንም ጥናት ሳይሰራ ሶሻሊዝም ላይ ትልቅ ሰርተው ወደ ካፒታሊዝም የተሻገሩ ሀገሮችን ተሞክሮ ኮርጆ የካፒታሊዝም ስረአትን አወጀ። ፊውዳሎ ካፒታሊዝምን መስርቶት ቁጭ አለ።ለዚህ ነው የንጉሳዊው/የፊውዳሉ ቤተሰብ ርዝራዝ ናችሁ የምትባሉት። ኢህአዴግ የሀብት ሩጫውን ሲስጀምር ደሓውን አብሮ ማስጀመር ነበረበት ነው፣ እያለኩ ያለሁት ባለሃብቶችን እየተቃወምኩ አይደለም።አንዳዶቹ በኃይሌ ገ/ስላሴ ፍጥነት ማራቶን ሲሮጥ ሌላው ውድድሩን/ሩጫውን አልጀመረም። ስለዚህ ብዙ ነገራችን እንደገና መገንባት ያለበት ይመስለኛል። ተወያዩበት በጣም። ብዙ ደሞች በከንቱ የፈሰሱባት አገር ነው ያለን። የደም ትግል ይብቃ። አንፈልግም በቃ ከጫካ ውጣ። ዶሞች እየጮሁ ነው።ብዙ ጫካዎች እንዳሉ አትዘንጋ፣የአመለካከትት ጫካም አለ፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣

**so there is no absolute truth in poltics,we must compromise.**

ለአፃፃፍ ስልቴ ይቅርታ፣፣፣

የኢትዮጵያ 7 ኛው ንጉስ በሁለት አመት የስልጣን ዘመንህ  የሚከተሉት ሀውለቶች ተሰርተውልሃል ሀውልቱን ያቆምኩት እኔ ነኝ ማነህ ብለህ አጠይቅ አፍንጫህ ላይ ነኝ። እውነት ነኝ። **call me** **<u>ጰ- truth.</u>**

**1.** የቀን ጅብ ብለህ ተሳድበሃል የመጀመሪያው ሀውልት

**2.** ሻሸመኔ ሰው ዘቅዝቀህ ስቅለሃል

**3.** ቡራዮ ደም ስታፈስ ግብር ይመስላል ለአቀባበል ይመስላል የተቀበልካቸውን ታውቃለሁ

**4.** ኢንጅነር ስመኘውን ስትገድል( አባይ የስመኘው ደም ነው፣ግድቡን የሞላው ውኃ የስመኘው ደም ነው።ፍትህ፣ፍትህ፣ፍትህ )

**5.** ጄኔራል ሳእረ መኮነን ፣ብርጋዴል ጀነራል ገዛሂ አበራን ስትገድል

**5.** የአማራ አመራሮችን ስትገድል

**6.** የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምዕመናን ስትገድል

**7.** የአማራ ሴት ተማሪዎችን ስታግት ፍትህ ፣ፍትህ፣ፍትህ ያሉበትን ሁኔታ በአስቸኳ አሳውቅ፣ሴራውንም አሳውቅ

**8.** ጋንቤላ አማራዎችን ስታስጨፈጭፍ

**9.** አጫሉን ሁንዴሳን ስታስገድል

**10.** ኩላሊት አውጥተህ ስትበላ ሀውልት ተገንብቶልሃል

**11.** የኢትዮጵያን ገበሬ አንበጣ ወሮት፣ጎርፍ እየወሰደው ፓርክ ስታስመርቅ፣ብሽክሊሊት ስትነዳደ(በሽቦ መኪና የወጣልህ መስሎኝ ነበር)

**12.** የጉራን ፈርዳን ህዝብ ስታስጨፈጭፍ ተገንብቶልሃል

**13.** በመላው ኢትዮጵያ የፈሰሱትን ደሞች እና ግፎች መታሰቢ ሀውልት በሰማይ ተሰርቶልሃል።በምድርም ተሰርቶልሃል።በእያንዳዱ ኢትዮጵያ ልብ ውስጥ ስንት ሀውልት እንደተሰራልህ ህዝብ ይቁጠረው።

**14.** የወጣት ዮሐንስ መርዕድ አባትንና የመሱሉትን መታሰቢያ ሀውልት ገንብቼአለሁ። አባቱን መልስለት። በይቅርታ ምህረት ካላገኘህ ምግብህ፣መጠጥህ፣ኑሮህ የሰው ስጋ፣ደም፣እንባ መሆኑን አትዘንጋ። ጨው ጨው ይላል ማለትህ አይቀርም። እንባው ይፈረደህ ወርደህ በእያነዳዱ ቤት ይቅርታ ጠይቅ ከዚህ ውጭ ለልጆችህና ለልጅ ልጆችህ በምድርም፣በሰማይም ደም አውርሰሃል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ እውነተኛ አባት፣እናት ሁኗቸው። አባትህ ነኝ በሉት።

ተደማሪዎች ሆይ እሱ ምን ያድርግ ትላላችሁ መልሱ He is the server.It is all abou server-client model.There is no peer to peer aspect In Ethiopian history .ካለ ተወያዩበት።ጄኖሳይድ እንዳይፈፅም መከላከል ይቻል ነበር።ደም እንደይፈስ ማድረግ ይቻል ነበር።

ስለዚህ ለኢትዮጵያውያን የሚያስፍልገው የግፍ ሀውልቶችን፣የጥላቻ ሀውልቶችን ማፍረስ መቻል ነው።እንዴት መልሱ ያለው በኢትዮጵያውን እጅ ነው።

የተሳሳቱን ሃውልቶች በውይይት እና የእውነት ሀውልቶችን በይቅርታ። መሪ ብቻ አይደለም ይቅርታ መጠየቅ ያለበት በዳይና ተበዳይ ነው። የገነባነውን የምታፈርሰው ቀጥታ ወርደህ እንጂ it is not by confussion.

ስለዚህ ሁሉም እምነቶችና ሃሳቦች ለውይይት ቀርበው፣ህዝብ ተሳትፎባቸው ነው እንጂ <u>ይቅርታ</u> ደጋፊዎችህን እየሰበሰብክ ይቅርታ ብትል እኔ አባቴ፣እናቴ፣እህቴ፣ወንድሜ፣ልጄና በአጠቃላይ ወገኖቼ በግፍ የሞቱብኝ ይቅር አላልኩህም።

ሀውልታቸውን ሰርቼ አለሁ።እባካችሁ ተደማሪዎች እውነትን ፈልጉ ፍርፋሪ አትልመዱ፣በፍርፋሪና በተጽኖ አትውደቁ።

ምክንያቱም አንቱ የተባላችሁት አርቲስት የኢትዮጵያን ህዝብ ደም እየፈሰሰ ፓርክ ተሰራ ብላችሁ ኮንሰርት ታዘጋጃላችሁ፣እንጦጦን እየጎበኘህ በአለም ካየኋቸው ከ 1 እስከ 3 ነው ትላለህ ፣ውይ ደስ ሲል ልጆቼን አሜሪካ፣ አውሮፓ ነበር

የማዝናናው አሁን ግን ማዝናኛ አገኝሁ ትላለህ የድሀ ልጅ ኩላሊቱ ወጥቶ እየተበላ ከዚህ ይጠብቀን።where is the love? where is the truth?

አድናቂ ብቻ አትሁን ልትዘፍነው ይገባል።ፍቅር ፍቅር፣ለፖለቲካ ሰላም ሰላም ብሎ ከመዝፈን ፍቅር የታለ፣ሰላም የት አለ ብለሽ ዝፈኚ።ተደማሪ. Where is the peace? ኦ ፊውቸር ነው። ፊውቸር ፊልም ትወጃለሽ አይደል። ነብይ ደስ ይልሻል ማለት ነወ ባለትንቢተኛው።**your sum gets zero, you must charge it.**

የኢትዮጵያ 7 ኛው ንጉስ መንግስትዎ በደም የተጨማለቀ ነው ስለዚህ እውነቱን የሚናገሩትን ልደቱ አያሌውን ፣እስክንድር ነጋን እና ባልደረቦቻቸውን ፍታ ጥያቄአቸውን መመለስ ሲያቅትህ ነው ያሰርካቸው ለእኛ የሚያስፈልገወ ሀሳባችን ተወክሎ በውይይት ተወክለን ወደ አንድ መምጣት ካለብን እንመጣለን።

ለኢትዮጵያ መፍትሄው አንተ ፅፈህ የመጣኸው መደመር እና ብልጽግና ፓርቲ አይደለም።በነገራችን ላይ መደመር ቃሉ ላላ ሲል አንተነህ ደማሪው ማለትም፣

1, By confused and conviced

2. By obligation*(obligation by love and focre) ሌሎች አማራጭ መንገዶችም አሉ ለእናንተ ትቸዋለሁ።

መደመር ሲጠብቅ ተደማሪው እራስህ ነህ።ስትደመር ግን አምነህበት፣ለጥቅም፣ተገደህም፣ወዘተ ሊሆን ይችላል።

መደመር ራስ ወደዳድነት የወለደው ፍልስፍና ነው።ወዴት እንደመር**?** የራስህን አመለካከት ይዘህ **42** አመት በሰባራ መርፌ የጠቀምከውን አመለካከት ይዘህ ለኢትዮጵያ የሚያዋጣው መደመርና መደበር ብቻ ነው ትላለህ።

መደመር አምባገነንነት የወለደው አስተሳሰብ ነው። እያል ያለኸው ገብቶሃል ወደኔ አመለካከት መደመር አለባችሁ ነው።ከገባህ መደመር ያለብህ አንተ ነህ። አብይ አህመድ መደመር አለብህ ወደ **110** ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ አስተሳሰብ።

መደመር ትርፍ ፈላጊ ፖለቲካ ነው።ማሳያው ኢሳያስ አፈወርቅ፣የአፈወርቂ ተደማሪነት።የኖቤል ሽልማት አመጣ።

የኢትዮጵ ህዝብ ሆይ አፈወርቂ እንደሚደመር ግልጽ ነበር፣ ግልፅ ነበር ምክንያቱም ዋናው የአፈወርቂ ፀብ ከህወሀት ጋር ነው።የቀን ጅብ ስትለው ህወሃትን፣ አፈወርቂ ዋው አሉ።የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው  አሉና ተደመሩ።ኢትዮጵያውያን በሬ ሆይ አጫወቱን።ከገባችሁ የሚያብለጨልጩ ፓርኮችም የበሬ ሆይ ውጤት ነው።እነሱን እያየን ወደ ገደል።

ኢሳቶች የበሬ ሆይ ውጤቶች ናቸው።ሲሳይ አጌና፣መሳይና ከመደመር በኃላ የመጡት ተደማሪ ኢሳቶች ሲናገሩ የበሉት ሳር ይታያል።ገለባ፣አሬሙቻ ፣፣፣፣፣ወዘተ የበላም አለ።

ህወሀትን መውጋት 60 ፐርሰነት ኢትዮጵያን ያድናል ትላለሁ።መሳይ ሳይሆን አስመሳይ ነህ።ሰይጣን መሳይ ነህ።ሊገባችሁ የሚገባው አባታችሁን እወቁ።ጦርነት በማንኛው ፓርቲ ካወጅህ አገሬ የምትላትን እያፈረስክ ነው።በቃ ህወሃት አልደመርም አለ።

ማብራሪያ ስጠኝ፣መልስ  ስጠኝ፣አሳምነኝ የአንተን አሸናፊ ሀሳብ።የጦርነት አዋጅ ከምታውጅ ለምን ልታሳምናቸው አትሞክርም።

- በህወሀት የተለያየ አዋጅ የምታውጁ ተጠንቀቁ።
- መደመርና ብልፅግና አልተመቻቸውም።
- አዋጅህን፣በጀት መዝጋትን ትተህ በሃሳብ አሸንፍ። አፄ በጉልበቱ አትሁን። ንጋትን መረጥኩ አላልክም እንዴ?
- አሰናቀን ደግፈህ አዋጅ ታውጃለህ ፖለቲካ አልገባህም ወይም ትንታኔ አትችልም ሁልግዜም ዘረኛ ነህ።
- የበላኸው ሳር እንጂ የሚያሳስብህ ህዝብ አይደለም።
- ኢትዮጵያዊ ከሆንክ ህወሀትን፣አነግ፣ወላይታ፣ሁሉም ብሄሮች የሚሉትን ስማ።
- ተደማሪዎቹ ብቻ ሳይሆን ያልተደ መርነውም ኢትዮጵያዊ ነን።
- ሓጥያቱ ሁላችንም ግንባር ላይ ተፅፋል። የዚችን ሴት ሀጥያት ቢያውቅ እንዳለው ይሆንብሃል።

በነገራችን ላይ ርዕዮት የኢትዮ **360** ዋን አመሰግንሽአለሁ።የመጀመሪያዋ ናት በግልፅ ፕሮቴስት ስታደርግ ከኢሳቶች በዘመነ Honey Moon።ልታብረታታ ይገባል።ethio 360 ዎች ሳሩን ባለመብላታችሁ አመሰግናለሁ።እየሩሳሌምንም ጀግና ናት።አሰናቀ ተመችቶኛል።ለእናንተ ያለኝ አሳብ፣

አስናቀ VS ህወሃት.የሚል ጥናት አድረጉና እወነትን ተጋፈጡ።እውነተኛ ትንታኔና መፍትሄ ማቅረብ አለባችሁ።

አንድ እውነት ልንገራችሁ የሚኒሊክ የአገዛዝ ስርአት በአጠቃለይ ፊውዳሊዝም ነበረ።ማለት ቢሆንም አለም ያለፈበት ታሪክ ነው ስለዚህ አይገርምም።

በስረአቱ ደግሞ መሬት ከበርቴና ጭሰኛ የነበረበት ነው።ስለዚህ የአገዛዝ ስርአቱ ጨቋኝ ነበር።የመሬት ከበርቴ ልጅ ከሆንክ አይገባህም፣ተደማሪ ጭሰኛም ከሆንክ አይገባህም።ሰለዚህ የሚኒልክ ስርአት ለአማራውም፣ለአሮሞውም፣ለሁሉም ኢትዮጵያዊ አስገባሪ ነበረ።

በውድም በግድም፣ እንቢ ስትል ምን እንደሚመጣብህ ማወቅ አለብህ። ሚኒልክ በተፈጥሮው ጥሩ ሰው ሊሆን ይችላል።ስርአቱ ግን በዳይ ነበር።ለዚህ ነው ተቋም ግንባታ የሚያስፈልገው።አዎ የአደዋ ጀግና ነው።ግን የአማራ ጭሰኞች እንባም አለበት፣ ይፍረድ።

- ሃሰብ ነው እየሰጠውህ ያለሁት ተወያዩበት።
- የኦሮረሞ የመሬት ከበርቴ ልጅም ከሆንክም አይገባህም።

ሰለሞናዊው ስረወ መንግስት ከእግዝያብሄር የተሰጠ ነው ብለን የምንደግፍም አለን። በግልፅ እግዝያብሄር ቅዱስ ዳዊትን ቀብቶታል ህዝቡን ነፃ እንዲያወጣ።

ወደልጁም ተላልፏል ነገር ግን ህዝብን ጭሰኛ አላደረገም።እምነቱን በጦርነት አላስፋፋም  ጥላቱን ግን በእምነቱ በወንጭፍ ጥሏል።የዳዊት እራሱን በዘይት የቀባ አምላከ እስራኤል ያስበን።

የእኛ ሰለሞናዊ ታድያ የተቀቡ እንደሆኑ ነው የሚያምኑት። ታዲያ ወንጭፉን ለምን ለህዘቡ፣በርግጥ ለጣልያንም ተጠቅሞታል ክብር ይሰማኛል።

እያልኩህ ያለሁት ከራስህ ምሽግ ውጣ ዳዊትም ጎልያድም የአብርሃም ልጆቸች ናቸው።ስለዚህ የሚኒልክ ልጅ መሆንህ ዳዊት ወይም ሰለሞን አያደርግህም። ከቻልክ እረኛው ዳዊት ሁን እንጂ የዳዊት ዘር ነኝ አትበል።

የዳዊት ልጆች ናቸው ጌታችን መድሃኒታችን ክርስቶስን የሰቀሉት።

እኔ የሴም፣የያፌት፣የካም ልጅ ነኝ እያልክ የተከፋፈልክ።አባታችን ኖህን የረሳህ።እኔ የያዕቆብ ነኝ፣ወይስ ኤሳው ራስህን የተከፋፈልክ። የይስሀቅ ናቸው ሁለቱም።

እግዘያብሄር ያዕቆብን መረጠ እንጂ ኤሳው እኮ የአባቱን ትእዛዝ አክብሮ ዱር አደን ገብቷል። አየህ ኤሳው ምነው ባደረገኝ ለምን አላልክም።በኸርነቱን አሳልፎ ስለሰጠው።ርቦት ነው ንፍሮ የጠየቀው፣ያዕቆብ ግን ሙሰኛ ሆነ። እንደቸርነትህ በል ሁልህም።

እስማኤል እኮ የአብረሃም ልጅ ነው።የመጀመሪያ ልጁ ነገር ግን እንደቸርነቱ ሆነ።

እስማኤል ይሰሀቅን በጣም ይወደው ነበር።ተዋጊም ነበር ሁሉን የሚጥል ከአቅሙ በላይ የሆነውንም ጥሏል ይስሀቅን እሽኮኮ ብሎ።የእስማኤል ነኝ፣የይስሀቅ ማለቱን ትተህ ወንደምህን እሽኮኮ ብለህ ችግርህ የሆነውን የስርአት ግንባታ ለማምጣት አንድ ሁን።

አብይ ሆይ ታድያ እንዴት እንደመርልህ፣

ቁልቁል፣ወደ ጎን፣በካልኩሌተር እንዴት እንደመር።

በአጠቃላይ ለማለት የፈለኩት ህገ፣መመሪያ፣ደንብና ስረአት ወዘተ የመሳሰሉትን አውጥተህ አትምጣ።ከቻልክ ከተገለፀልህ ነብይ ከሆንክ ህዝቡን ድረሰው፣ኑሮችንን አውራ፣ምን ብል ሰው ይደሰታን ሳይሆን እውነቱን ተናገር።

መፅሃፍና ፍልስፍናህን ይዘህ መምጣት በአለም የተለመደ ነገር ነው ነገርግን ተቋም በአላቸው አገር ነው።ምክንያቱም ፍልስፍናህ የምታጋራው እንጂ ሀገር መምሪያህ አይደለም ተቋም ነው መገንባት መፅኃፍ አሳትሞ ከመሸጥ።

እኔ ማንም የሚከፍትኝ ቧንባ አይደለሁም አልክ አሉ? ወሬ አይደበቅም። እሺ የቤተመንግስት ቧንቧ ሃሃሃ።

መሆን ግን የነበረብህ የቦኖ ውሃ ነበር ሁሉም፣ማንም እየከፈተ የሚጠጣህ። በገጠራማው ኢትዮጵያ ያለው ቧንባን ታወቀዋለህ በእጅ እየተወዘወዘ ውሃ የሚሰጠውን ቧንቧ እንደሱ እየተወዘወዝክ ውሃ መስጠት ነበረብህ።

ማንንም አልሰማም ነው እኮ እልክ ያለኸው።

ህዝብ ሆይ ንጉሱ አሜሪካ ሲሄዱ በብዛት ኦሮሞና አማራው አብሮ አአልተገኘም።ሚኒሊካዊያንን ዲሲ፣ኦሮሚያውያን ሚኒሲዮታ/ሲያትል።ያን ግዜ ነበር መታዘብ የነበረብህ።ህዝብ አብሮ ሳይሆን ኢትዮጵያ ሱስ ናት ቀልደኛ ናችሁ።

ሀሰተኛው መሲህ እንደዚህ ነው የሆነ ነገርህን ክሊክክ አድርጎ የሚያስገድህ። መርምር መርምር መርምር ተግባር እንጂ ንግግር የማይችል ፖለቲከኛ ኢትዮጵያ ውስጥ የለም።ገብቶሃል ታማኝ።እምነትህ የት ገባ ወይስ የዳንኤል ክብረትን ቦታ ፈልገሃት ነበር።

እኔ እያወራሁ ያለሁት ብዙ ግጭት አፈታት መንገዶች ቢኖሩም።እኔ ማንነቴ የተገነባው By win win Methods ነው።ከዚህ ውጭ እኔጋር አትግባባም።for me win win is God's way. Angles way. Hollys way. Else get out of my way.

<u>የኢትዮጵያ **7** ኛው ንጉስ ለምን ንጉስ መሆን ፈለጉ</u>?

1. አናትዎ ትንቢት ስለተናገረች እሺ ጥሩ ነው ምን ራዕይ አብራ ሰጠችህ የገነባውልህን ሀውልት አስብ እሱ ነበር አላማዋ ስለዚህ ትንቢቷ ከማን እንደሆነ አስብ ትንቢቶች ሁሉ ከእግዚያብሄር አይደሉም።It may be a disciple of evil. Because you are a butcher. የእነትህን ምኞች ያመከንክ።

2. የስልጣን ፍላጎት ስላለዎት ወይም ራዕይዎን ለማሳካት

3. ህዝብ ለማገልገል (you must be a servant or democratic) But where is that?

ይህንን ጥያቂ ያነሳሁት ለ 7 ኛው ንጉስ ብቻ አይደለም ንጉስ፣መንግስት መሆን ለምትፈልጉ በሙሉ ነው።ለምን መሪ መሆን ፈለክ? ይህንን ጥያቄ ለራስህ መመለስ አለብህ። ማንም የኢትዮጵያ እናት ልጇ ንጉስ ነው ።

መንግስት መሆን የሚችል ልጅ እየገደልክ እናቴ ንጉስ ትሆናለህ ብላኝ ነብር ብሎ ማሰብ ኃጢያት ነው።የሌላይቱ እናት ንጉስ ኩላሊቱ ወጥቶ ሲበላ እያየህ ዝም ትላለህ አዝናለሁ።

በአንተ የንግስና ዘመን ንጉስ የመሆን ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ጨምረዋል ለምን ይመስልሃል? ሁሉም ባይሆኑም አብዛኛዎቹ ህፃናት ብልጭልጭ ነገርን፣አሻንጉሊት፣መዝናናት፣የእንጦጦ ፓርኳን ዐይነት መኪና መንዳት ስለሚወዱ ነገር ግን እነሱ መውደዳቸው It is proportional to their age. And it deserves for them.The problem is it doesn’t consider the majority of Ethiopian children. ለማለት የፈለኩት የሸቦ መኪና የሚነዱትን እየታደገህ አሳያቸው ነው።ህዝብ ያጨበጨበልህ ለምን እንደሆነ ታውቃል? **It is all about your god. Peacock god. It is all about Peacock seduction. It is all about seducing people.you let the people lie in your bed**.

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የሚመችህን የምታውቀው አንተ ነህ። የእግዚያብሄር ዘመን እስከሚመጣልህ በያለትህ በርታ። እየመራህ ያለው መንግስት መፅደቅ ከፈለገ እድል አለው።

እስረኞችን ይፍታ፣የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ድምጽ ይስማ፣ሁሉም ድምፆች ይወከሉ።የሽግግር መንግስት የሚሉትም ይሰሙ፣ብሄራዊ እርቅ የሚሉ ድምፆችም ይሰሙ፣ህገ መንግስት ይሻሻል የሚሉም ይሰሙ፣የሁሉም የህዝብ ጥያቄዎችና የወከሏቸው ፓርቲዎች ጥያቄ ይወከሉ ይመለሱ።የህዝቡን ጥያቄዎች የሚመለሱበትን መንገድ መስርተህ ንጉስ ባትሆን ባትመረጥም አንተ የዘላለም የ ኢትዮጵያ ንጉስ ትሆናለህ።ከዚህ ውጭ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር እንጂ ንጉስ መሆን አትችልም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፣ ህዘብ ሆይ ለ እኔ የአብይ አህመድ፣የደመቀ መኮንን ፣የገዱ አንዳርገቸው፣የአባ ዱለ ገመዳ፣ከኢህአዴግ ወደ ብልፅግና የዞሩ አመራሮች እና የበረከት ስምኦን፣የታደሰ ጥንቅሹ፣የእነ ጀነራል ከንፈ የመሳሰሉት ሁሉም አንድ ናቸው። ስለዚህ ይቅርታ ለአብይ ካደረግህ ለእነሱም ይቅርታ ልታደርግ ይገባል ምክንያቱም አሳሪዎቹም የቀን ጅቦች ናቸው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ በጁሃር እና በአብይ አህመድ ያለው ልዩነት ምንድን ነው**?** በጁሃርና በሽመልስ አብዲሳ ያሉ ልዮነቶች ምንድን ናቸው**?**በሁለቱም አመራርና የስልጣን ዘመን የሚያሳዝኑ አዳዲስ ህውልቶች ተግንብተዋል።ስለዚህ አሁን ስልጣን ላይ ላሉት አመራሮች ይቅርታ ከተደረገ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ይቅርታ ለነሱም ይገባል።

ለመንግስቱ ኃይለ ማርያምም ይቅርታ ማድረግ አለብህ።እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች ከእስር ተፈተው ይቅር ተባብለን መሻገር አለብን።ኪዚህ ውጭ አንድን ሀውልት አፍርሰህ ሌላ መገንባት ነው።

ለምሳሌ የአኖሌን ሀውልት አፍርስ የምትሉ ሓይሎች ሀውልቱ የሰው ጭንቅላት ውስጥ ተገንብቷል። መጀመሪያ ከሰው ጭንቅላት ውስጥ አፍረሱ በኃይል አይደለም። በየሚዲያው የራስህን ኃሳብ መሰንዘር አይደለም for like and share. Subscribe , subscribe.....ስልጣን ላይ ያለኸው መንግስት ይህን ማመቻቸት የአንተ ስራ ነው።

ለምሳሌ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያውቁ ምሁራን፣አባቶች፣የተለያዩ ባለሞያዎች በማሳተፍ ጭንቅላታቸው ላይ ያሉ ሃውልቶ እንድያፈርሱ ለማድረግ ሞክር ትክክል ከሆኑ ከተበደሉ ይቅርታ ጠይቀን በይቅርታ ሃውልቱን እናፍርሰው ከዚህ ውጭ አዲስ ለሚሰሩት አኖሌወች አስተዋፆ እያበረከት ነው። conviced but not confussed. የብልፅግና አመራሮችና ተደማሪዎች ብዙ አኖሌዎችን እየገነባችሁ ነው።ቴዲ አፍሮንና ሃጫሉ ሁንዴሳን ማነፃፀር አይደለም ፖለቲካ.ሁለቱም የገነቡትን የማንነት ሃውልት ማንም ማፍረስ አይችልም።ሁለቱ ናቸው ተስማምተው፣ተዋደው አንድ መሆን የሚችሉት። አንተ አይደለህም ዜማና ግጥም የምታዘጋጅላቸው።ቴዲ አፍሮ በራሱ ስሜትኦሮምኛ እኮ ቢዘፍን ምን ነካው የምትል ደጋፊ ነህ ያለኸው። ለአጫሉ መታሰቢ ቢዘፍንማ አለቀለት።

ወደድክም ጠላህም አጫሉ ሁንዴሳ ጀግና አሮሞ ነው።ለእኔ ኢትዮጵያዊም ነው።ማንም ሳያሳምነው እምነቱን ኖሮ ለእምነቱ ሙቷል ጀግና ኢትዮጵያዊ ነው። ስለአጫሉ ሀውልት ሰለመሰራት ከምትጫጫ ለስመኘው በቀለ ሃውልት እንዲሰራ አትታገልም።ትግል ደግሞ አንድ ቀን በሚዲያ አውርቶ ላይክና ሰብሰክራይበር በልተህ አትደር እሲኪ ፈፀም ታገል።

የኦሮሞ ወጣት ሆይ ቴዲ አፍሮ ሌላ አጫሉ ነው። የራሱ እምነት ያለው።እምነቱን የሚኖር።እሱን መንካት መስደብ አጫሉን መስደብ ነው።ሌላ አጫሉን ሊያሳጡን የሚሞክሩትን አትስማ።የአጫሉን ደም ሁለተኛ በአንተ እጅ ደም ሊያስፈስሱ። ችግራችን አጫሉን ማን ገደለው እንጂ ቴዴ አፍሮ አይደለም።የፖለቲካ ጨዋታው ይግባህ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ቴዲ አፍሮ ወይም አጫሉን ሁን እነጂ።ከሁለቱ ማን ይባልጣል ጦርነት ውጣ። ከቻልክ ራስህን ሁን። በግድ ከቴዴ አፍሮና ከጐሳየ ተስፋየ ማን ይበልጣል ብሎ ግግም። taste the difference. They are life spice.

ከቴዲ አፍሮና ከየጐሳየ ማን ይበለጣል ብለኽ ትከራካለህ።ፖለቲካውም የዚህ ግልባጭ ነው።በዚህ ክርክር ደም ታፈሳለህ፣ደም ታስፈስሳለሁ።

አገራችን እኮ በማንችስተርና በአርሴናል ማን ይበልጣል ደም ፈሶባታል። ስለዚህ ህዝቡም ደም አፍሳሽ ነው። ተናግረህ ማሳመን ሲቅትህ ዱላ፣ስድብ፣ደም አትምረጥ።

እግር ኳስ ተጨዋች ስትደግፍ ለምን እደሆነ የማታውቅ። መሲ/ክርስትያኖ ሮናርዶ. ለምን ደገፍካቸው፣

- ✓ መሲ ሆርሞን ወስዷል ክርስትያኖ አልወሰደም
- ✓ ክርስትያኖ ማንችስተር ስለነበረ
- ✓ ክርስትያኖ እስላም ሳሆን አይቀር ኦዚል ጓደኛኛው ነወ
- ✓ አይ ክርስትያኖ ቀማሽ ነው።መሲ ሰጋጅ ነው መብታችሁ ነው
- ✓ የባርሳ ደጋፊ ስለሆንክ ወዘተ ነው ምክንያትህ ፣መብትህ ነው ቁም ነገሩ ግን ችሎታን መዝን ነጮቹ ለእኛ የሚያሳዩን ኳሊታቸውን ነው። ኳሊቲ ደግሞ መለኪያ አለወ።for example
    - ✓ No of balls he assist
    - ✓ No goal he score
    - ✓ No perfect pass and cross.
    - ✓ No of tophy he wins etc
    - ✓ The position he play and his roll must be considered

      ለባለሞዎች ትቸዋለሁ።

ሙዚቃ ውድድር ስታይ ደምፅ የምትሰጠው ብሄርህን እየመረጥክ፣ቅስቀሳውም የአማራ ፋኖ።ከአማራነት ወርዶ ጐንደሬው፣ጐጃሜው፣የብሄር አይደለም ውድድሩ ሙዚቃ ነው ጓደኛየ።

በራስህ ብሄር መወዳደር ትችላለህ።ነገር ግን ውድድሩ አዲስ አበበ ቅስቀሳው ዳንግላ ምን ይባላል።ባህልህን እኮ የዳንግላ ህዝብ ያወቀዋል፣ቤተሰብህ ነው ።ለምን የአዲስ አበባ ህዝብ ላይ፣የኦሮሞ ህዝብ ልብ ሰብረህ አአልገባህም ።

በነገራችን ላይ ዳንግላ ስል ይህ ሰው ዳንግላወችን ጠመዳቸው እንዳትል.For me Dangela is Verginia.

እንዳውም ዳንግላ ነው ቤቴ የሚል ሲንግል ብትለቅ ደስ ይለኛል ። ያው የሀረርን ለዳንግላ ነው የምልህ ገብቶሃል ።

እስኪ በአሁኑ ዘመን አማራ ሆኖ የኦሮሞን ልብ ሰብሮ የገባ አርቲስት፣ፖለቲከኛ፣ግለሰብ፣ኢትዮጵያዊ አሳዩኝ።ፀጉሩን የቆጠረ መሆን አለበት።

ስለዚህ ኢትዮጵያዊ አይደላችሁም ሁላችሁም። ምክንያቱም ከ 30 ሚሊየን በላይ ህዝብ የእናንተ አይደለም። ሁሉም አይደሉም አትበል። የኦረሞ ወጣት down down እያለ ሰላማዊ ሰልፍ ከወጣብህ አንተ ኦረሞም፣ኢትዮጵያዊ አይደለህም።ራስህን መርምር፣አስመርምር።

ሌላው የፋና ላምሮት የመጨረሻውን ውድድርን በተመለከተ ውድድሩን ዮናታን በህዝብ ድጋፍ በሰፊው እየመራ እንደነበረ ይታወቃል በህዝብ ድጋፍ የሚፎካከረው ሰለሞን ጥጋቤ ነበር ።ዮናታን ሊያሸንፍ እንደሚችል ፍንጭ ነበረው።

ከመጨረሻው ውድድር በፊት የነበረውን ውድድር አይታችሁት ከሆነ በህዝብም በዳኛም ኤልያስ ተ/ኃይማኖት አንደኛ ነበር ።ግዛቸውም ብዙ ደጋፊ ነበረው ከዮናታን ባላነሰ ።ስለዚህ ሁሉም በሂደት ብዙ ደጋፊ አፍርተዋል ።በዚህም መሰረት የፍፃሜው ውድድር ለእኔ አጓጊ ነበር ።ሁሉም ብዙ ደጋፊ አፍርተዋል በሂደት ።

ስለዚህ የመጨረሻው ውድድር ላይ የዮናታን ድምፅ ብቻ ነው እየቆጠረ የነበረው ።የሌሎቹ አይጨምርም ።እኔ በሰአቱ ያሰብኩትን ልንገራችሁ፣ለምን ኤልያስ ተ/ኃይማኖት ከሳምንት በፊት የነበረውን ከ 30 ሺ በላይ ድምጽ አጣ።የግዛቸው ድምፅ የት ገባ ከሳምንት በፊት 20 ሺ በላይ ድምፅ ዛሬ የት ገባ፣የሰለሞን ጥጋቤስ፣የኤልያስ ተሾመስ ድምፅ የት ገባ፣መቅደስ እንኳን ደጋፊ አልነበራትም።ለምን የዮናታን ከ 10 ሺ በላይ ሆኖ የሌሎቹ 3000 መድረስ ለምን አልቻለም የእኔ ጥያቄ ነበር? መልሶቹ፣

- የፋናዎች የቴክኒክ ባለሞያዎቹ የዮናታን ደጋፊዎች ናቸው ከፍፃሜ በፊት የነበረው የኤልያስ ተ/ኃይማኖት ድምጽ ፣ግዛቸው፣ወዘተ የት ገባ።የእነሱን  ድምፅ ካወንት ፎር የናታን ፕሮገራም ሰሩለት እንዴ.የእኔ የውስጥ ሀሜቴ ነው
-  ወይስ የሌሎቹን ድምፅ ፖዝ አደረጉት ማለት ጀመርኩ እንዳውም የአዳነ እጅ አለበት አልኩ ምክንያቴን መርምሩ ይቅርታ አዳነ በጣም ።
- ሌላው ስታክ እዳደረገ ገመትኩ
- ቀጨኔዎች የት ገቡ አልክ? በአል ስለነበረ መድኃኒአለም ናቸው አልኩ ከመድሽ ሲዮጡ ይጨምራል አልኩ
- መነን ሽሮ ሚዳዎች የት ገቡ ወዘተ

በሂደት ፋናዎች ችግሩንና መፍትሄውን አሳወቁ

- ደንግጠዋል የኢትዮጵያ ህዝብ ምን ሊላቸው እንደሚል ገብቷቸወል። የመጨረሻው ድምፅ ሙስና ካልተሰራበት አሸናፊው ታወቀ ስለነበር ።የአዘጋጆቹን ስሜት ብታነቡት ጥሩ ነበር
- የ ሰጣችሁት አስተያየታችሁን እናንተ ታወቃላች እኔ የማንም ደጋፊ አልነበርኩም እውነትን ስርች እያደረኩ ነበር
- መቅደስ የህዝብ ድጋፍ አልነበራትም በዳኞች ድምፅ ግን በአብዛኛው ውድድር የነበራትን ውጤት ቸክ አድረጉ ።
- የሺ.መልስ አብዲሳ እጅ ነው የምትሉም አላችሁ በዘር ፖለቲካ አይሆንም አልልም ነገር ግን ማስረጃ እፍልጋለሁ እንደዛ ካሰባችሁ ደግሞ ፋናዎች ታዛዦች ናቸው ችግሩ ከገባችሁ እነሱን ለቀቅ ነወ ።
- ሌላው የሺ. ደመላሽ አስተያየትሽ የአማራነት ስሜት ነው ሞያዊ ።ስለዚህ ሌሎች ባለሞያዎች ጋር በመጨርሻው ውድድር መቅደስ ወይስ ዮናታን የሚል ወይይትና ውጤት አሳውቁን ዝም ብለሽ አቤልን አትንኪ ። ለእኔ ሁሉም ጎበዞች ናቸው ።
- መቅደስ ወይስ ዮናታን በባለሞያዎች የፍፃሜ ፐርፎርማስ ሌሎቻቸሁን ያለወዳደርኩት የሁለቱ የአማራና የኦሮሞ የበላነት ጥያቄ ስለሆነ ነው ። ሰለሞንን ማካተት ትችላላችሁ ነገር ግን የሌሎቹ ብሄራቸው አልታወቀም ምስኪን የአዲሰ አበባ ልጅ ኢትዮጵዊ ናቸው ።

- ለአቤልና ለብሌን ጥያቄ አለኝ የመጨረሻውን ድምፅ ለምን አልሰጣችሁም? መልሳችሁን ሰምቼ አለሁ።ባለሞያ ነኝ ብለህ ነው የተቀመጥከው ብሌን የአቀናበርሽውን ሙዚቃ አይደለም ስትዳኚ የነበርሽው፣የገጠምሽውን ግጥምም አይደለም ስትዳኚ የነበርሽው ስለዚህ ስራው አልበሰለም ብለሽ፣አቤልንም ይመለከታል ድምፅ አለመስጠት ምን ይባላል ወይስ ዮናታንየ እጂን ታጥቤ አለሁ ብላችሁ አማንኤል አጋፈጣችሁት። ምንም ይሁን በአለው ይዘት ውጤት መስጠት ነበረብሽ።
- ይህ ጥያቄ ደግሞ ለአማኑኤል ነው። አማን መጀመሪያም ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት ድምፅ እንደማይሰጡ ተነጋግራችሁ ነበር ወይስ መጨረሻ የመጣ ሃሳብ ነው። የማንስ ተፅኖ ነበር። ለእኔ ግን ድንገት የከዱህ ይመስለኛል። መልሱን ለራሳችሁ።ለማንኛውም ስራወን ትልቅ ስራ እንዲሆን ጣር የተከዳህበት ስራ ይመስለኛል። ምክንቱም እነሱ ካልዳኙ አዲስ ስራ ለምን አስፈለገ።በፕሮቶታፕ፣በፕሮፖዛልም  ውጤት ይሰጣል። ይመጫችሁ።
- ሌላወ አገው ስለሆነ ነው ያልከው የአገውን ክብር እየነካህ ነው ይቅርታ ጠይቅ ።እሱ በአገውነቱ ኩሩ ነው ።
- ስለዚህ ለአንድ ችግር መፍትሄው ብዙ ነው ።

አዲስ ነገር እየተናገርኩ አይደለም አርቲስቱ፣ፖለቲከኛው፣አክቲቪስቱ፣ህዝብ የተናገረውን ነው ።እንስማማ ነው የእኔ አስተያየት ።

የኢትዮጵያ ዘፋኞች እስኪ ስለኢትዮጵያ ያላነሳችሁትን ሀሳቦችና መፍትሄዎች ንገሩኝ ። የአነሳችሁትን ጉዳይ የሚመልስ መሪ እንጂ አዘፋፈን ና አገጣጠም የሚያስተምር፣እስክሪብት ኤዲት የሚያደርግ መሪ አይደለም የሚያስፈልገህ ።

ለጥላሁን ገሰሰ ቅለፃ ስታስተምር ።መጀመሪያ ያነሳልህን ጥያቄ መልስ ።ለችግራችን መልሱን ነግረውህ ሁሉም ቢተባበር ብለው ። ለተቦርን (ተ the Born)  ትቸዋለሁ ያስረዳችሁ ።

ያደማመሩ ስትራቴጂ ሊገባህ ይገባል ።

We are living in 36o degree try to solve a problem in each loop. Don’t stack in your own quadrant. Don’t fight for your own lattitiude and longitiude shar for me your coordinate.

ኢትዮጵያውያን የኦሮሚያ ህዝብና ቄሮ ሆይ ስለአኖሌ የተነገረህ እውነት ስለመሆኑ ማረጋገጫ በእጅህ አለ ወይስ ጥላቻ ተሰርቶብህ ነው። ምክንያቱም ይህ አንዱ የፖለቲካ ስትራተጂ ነው። ቁስል ይሰጡህና ተከታይ ተደማሪ ያደርጉኃል።

ማረጋገጫው በእናንተና በመሪዎቻችሁ በእጃችሁ ካለ ሀገሪቱን የሚመራው አካል ውይይት ያመቻችና ችግሩ እከመጨረሻው ይፈታ ሰነዶች ይቅረቡ እውነት ይሰበክ ከዚህ ውጭ ኮሽ ባለ ቁጥር ወንድምክን አትግደል።

ምክንያቱም በሰማይ፣በምደር የሚያስጠይቅህ ሀውልት እየገነባህ ነው። ሰላማዊ እርቅ ነው መፍትሄው ተበደያለሁ ያለ ይክሰስ፣ማስረጃ ያቅርብ፣ተከሳሽም አለመበደሉን ማስረጃ ያቅርብ በፍቅር በይቅርታ እንካካስ ስንሞትም ብቻ ሳይሆን ስንኖርም ኢትዮጵያ እን ሁን።

መንግስት ሆይ አሞኛል እያልኩህ አላመመህም አትበለኝ ከቻልክ መድኃኒት ስጠኝ ወይም አለመታመሜን አረጋግጥልኝ።በሰው ቁስል አትጫወት ቁስሉን አክመኝ ወይም እንዳልቆሰልኩ አሳየኝ።የቆሙ ሃውልቶችን ለማፍረስ ብትሞክርና ብታፈረስ የጭንቅላቴን ሓውልት ግን መንካት አትችልም።ጭንቅላቴ ላይ የሰራሁትን ሀውልት ሳታፈረስ ሌላ የመታሰቢያ ሃውልት አትገንባ።

ታሪክ አዋቂ ነኝ እያልክ በዩቲዩብና ለዲያስቦራው ሚኒሊካውን  እምየ ሚኒሊክ እያልክ ከምታናፋ መጀመርያ የኦረሞን ህዝብ አሳምን ። ካላሳመንክ የአጫሉን ሁንዴሳን ፈረስ የሰረቅኸው፣ያሰረቅኸው፣የዘረፍከው፣ያዘረፍከው አንተ ነህ ።

የኢትዮጵያ 7 ኛው ንጉስ ለፖለቲካ ፍጆታ ስትል የኦሮሞ ህዝብ፣ ቄሮ ኦነግንና እነ ጃዋር መሃመድ ወዘተ የገነቡትን ሀውልት ሳታፈርስ ቤተመንግስት የአፄ ሚኒልክና የአፄ ኃይለስላሴ ሀወልት ለፖለቲካ ፍጆታ ትገነባለህ ይህ ሚኒሊካዊያንን ለማስደሰት ነው። we call it confussion.

ይህ የኢትዮጵያን ህዝብና ታግሎ ከርካብ ወደ መንበረ ያመጣህን የኦሮሞን ህዝብ መናቅ ነው። ምክንያቱም አማራጫቸው እኔ ነኝ፣ተረኛ ናቸው የሚል አስተሳሰብ በተደማሪዎችህ እያሰበክ መሲሁ እኔ ነኝ አልካቸው።የትም አይሄዱም ብለህ ሌላውን ለማስደሰት ሃውልት ስታስመርቅ እነ ጃዋር አኖሌን ሊያስቡ ሄዱ ትክክል ናቸው።you must conviced them. ቁስላቸውን ማከም ነበረብህ።

እነሱና የኦሮሞ ህዝብ አንድ አይደሉም በል ደግሞ ከማን ማህፀን ወጡና.....................ቄሮ ሆይ በደም ሳትታጠቡ ፤ሳታፈናቅሉ ታገሉ። የበደለህ ሌላ የምትገለው፤የምታፈሰው ሌላ። ደም ወደ ዘርህ ይተላለፋል ደም አታፍስ።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።

ሌላው ችግር......

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ እኛ ነፃ ኃይማኖት፤ነፃ ተቋማት ነው የምንፈልገው የኃይማኖት አባቶች አያሳዝኗችሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ምእመናን ተጨፍጭፈው ፓትሪያሊኩን ቤተ መንግስት አስጠርተህ ትመሰገናለህ ያሳፍራል። ኃማኖቶች የውስጥ ግጭታችሁን እራሳችሁ ፍቱ መንግስት ጣልቃ ካስገባችሁ ይጫወቱባችኋል። ከዲየቆን ዳንኤል ክብረትና ተደማሪ የሃይማኞት አባቶች ይጠብቀን።

አገር የሚመራው አሽከር የሆነው ለዚህ ነው። ፓትሪያሊኩ፤የሁሉም ኃይማኖት አባቶች አሽከር ናችሁ። መንግስት የኢትዮጵያ ህዝብ ለኃይማኖቱ ሟች ስለሆነ ነው የሚጠቀሙባችሁ።መሪ ናችሁ አሽከር አትሁኑ። ሁላችሁም የሀይማኖት አባቶች እናንተና ህዝባችሁ ነው የአገር መሪ እውነቱን በግልጽ ተጋፈጡ ።

ትግራይን ብልፅግና ለማድረግ ታዘህ መቀሌ ትሄዳለህ እፍረት ነው ቁጭ በሉና ችግራችን ምንድን ነው ብላችሁ ጀምሩ ።ትግራይ ብልፅግናን ብትቀላላቅል የኢትዮጵ ችግር ይፈታል ብላችሁ ታስባለችሁ? አዎ ከሆነ መልሳችሁ እንዴት መልሱን ስጡን? አዲስ ንጉስ በመጣ ቁጥር መንበር ጠባቂ አትሁን ።ህዝብ ጠባቂ ሁን ።

መይሰው ካሳ ለምን የጨከነባችሁ ይመስልሃል? ባለሞያዎች ጥናት ይደረግበት ።ለምን ሚኒሊክ ጋር ተስማሙ ጥናት ያስፍልገዋለል ።እጅ አትቀስር ።

የመንግስት ተቋማትም ነጻና ገለልተኛ ካልሆነ ሁልግዜ ለመሪዎች አሽከሮች ናችሁ ለምሳሌ መአዛ አሸናፊ ለቦታው ሁሉም ይስማማባታል ብየ አምናለሁ። But she Is the zero sum game. Even The president.

ያልገባችሁ ሰው አገር የሚመራ እየመሰላችሁ ነው።አገርን የሚመራው ተቋም እንጂ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሆን የለበትም ለዚህ ነው ተጠያቂ የጠፋው። ከአብይ ውጭ ማን አለ አትበል 110 የኢትዮጵያ ህዝብስ፤

ለምሳሌ ባለ ተራ ነን የምትሉ ሰዎች ብሄርህ ስልጣን ስለያዘ ለአንተ ምንም ጠብ አይልልህም ተቋም ቢገነባልህ ግን ለልጅ ልጅህ ነው። የአብይ አህመድ መንግስት ለልጆቻችሁ እንግዲህ የፈለጋችሁትን አውርሱ የዘላለም ንግስና ወይም ውርደት።

በግልፅ ቋንቋ የምትኖረው በሰው ደም ነው ሀገሪቱ የሁላችንም ናት እኩል ልንጋራት ይገባል።የሀብቷ እኩል ተጠቃሚ የኢትዮጵያ ህዝብ መሆን አለበት። ይህ በአልሆነበት ንግስና የለም።ጣሊያን ወይም ሮም ውስጥ በጎች ሰው በሉ የተባለበት ዘመን ነበረ።ኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች ሰው በልተዋለ። ደም እየጠጣችሁ ነው፣ኩላሊት እየበላችሁ ነወ እስከ ቤተሰቦቻችሁ።

እንደ ኃይማኖት አባቶች አርቲስቶቻችንም በጣም ያሳዝናሉ እናቶች እያለቀሱ ባሉባት አገር፣ደም እየፈሰሰ የጃዝ ኮንሰርት ታዘጋጀለህ የመንግስትህን ገፅ ለመገንባት  እባካችሁ መንግስታት ነጻ ተቋም ይኑር እንደሰርፀ አይነት ተደማሪዎች ይወገዱ ለማለት የፈለግሁት አርቲስት ስልጣን አይያዝ አይደለም እንደ ተቋሙ፣ እንደተቋሙ ያስፍልጋል፣ጠቅላይ ሚኒስተር መሆን ይችላሉ የፖለቲከኛ ጥገኛ አትሁን ነው።ተቋምም በባለሞያው ነው መመራት ያለበት ።የተቋሙ መሪ ስለ ሆንክ ተፅኖ መፍጠር ግን አትችልም።

ለምሳሌ የጃዙን ኮንሰርቱ አናዘጋጅም ቢሉ የሚደርሰብባቸውን ተፅኖ እግዚአብሄር ይወቅ።አፍቃሪ ተደማሪዎች በፍቃድ የሚሰሩም አሉ።

ሌላ ምሳሌ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የኖቤል ሽልማት አጅቦት ከሄደው አንዱ የሙዚቃ ቡድን ልዕኩ ነው። በብቃታቸው ባልጠራጠርም የተመረጡበት መሰረት ምንድን ነው? ያሳሰበኝ መመረጣቸው አይደለም፣የሙዚቃ  ቡድን አብሮ መሄድ የለበትም እያልኩ አይደለም ተፅዕኖውውን ነው እያወራሁ ያለሁት።

 አሁንም ባንዱን ሰርፀ ፍሬ ስብአት ያላመኑበትን ስራ አምጥቶ ለመንግስት ገፅታ ግንባታ ሲባል ነው ። ስሩ ቢባሉ ከመስራት ወደኃላ አይሉም ምክንያቱም እሱን ስትገረፍ ታወራዋለሁ ነው ጨዋታው።

አርቲስቶቻችን ስሜታቸውን ይስሩ ክቡር አርቲስት ዶክተር ጥላሁን ገሰሰ ኢትዮጵያን የዘፈነው በስሜቱ እንጂ በትእዛዝ አይደለም ወይም በግዴታ አይደለም  ።ወይም የእውነት፣ስሜት የሚሰጥ ትዕዛዝ አምጡ።በነገራችን ኢትዮጵያ የሚለው ዘፈን ነው ለእኔ የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር። ሁለቱም ኢትዮጵያዎች የንጉሱና የልዑሉ። This is my Emotion.

ሀዘን ላይ ሁነው ቢያንስ ኮንሰረት እንዲያዘጋጁ አታድርጉ።መንግስታዊ አርቲስትን እየተቃወምኩ አይደለም። ህዝባዊ አርቲስትን አትንኩ።

በኃማኖትም አባቶችን ስብሰባችሁን፣ልደታችሁን በቡራኬ አታስጀምሩ እያልኩ አይደለም ነገር ግን ወንጀላችሁ ሲበዛ፣ኃጢያታችሁ ሲበዛ ለገፅታ ግንባታ አትጠቀሙባቸው።Don’t be image builder for Evil.If it is truth that you build that is good. Cause you are blessed.

ሌላው ችግር የመንግስት ስራተኞች ነው መንግስት የህዝብ ድጋፍ ማግኛት ሲያቅተው የመንግስት ሰራተኛውን በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ በመክተት አባል የሚያደርገው ሴራ የሚታገል ጠንካራ ተቋም ያስፍልጋል።

አባይ የሀገር ህልውና ሆኖ ሳለ በአቅም ችግር 100 ፐርሰንት ማወጣት ያልቻለ በተፅኖ ስር ወድቀው የነበሩ ብዙ ነበሩ ቤት ይቁጠራቸው።አሁንም ገበታ ለሃገር እያለ የመንግስት ሰራተኞችን ያሳቅቃል ወንድሙ ሻሸመኔ ሞቶቦት፣ቆስሎበት ማስካሚያ ያጣ የመንግስት ሰራተኛ ገበታ ለሸገር 100 ፐርሰንት ቀልድ ነው።

ልማትና ፓርክ እየተቃወምኩ አይደለም ነገር ግን የደምና የእንባ ልማት እና ፓርክ አትገንባ አኬልዳማ ነው።ለእኔ የገነባኸው ፓርክ አኬልዳማ ነው።

ደም ያፈሰሱና ያስፈሰሱ የሚዝናኑበት የእንጦጦን ፓርክ ከምታስገነባ የአጫሉን ደም ፍትህ እፈልጋለሁ።አባይ የመጀመሪያም ሙሊት ተሞላ ከምትለኝ የስመኘውን ደም ፍትህ ስጠኝ። ከዚህ ውጭ የደም ግድብ ነው አኬልዳማ ።

የኢትዮጵያዊ ህዝብ ሆይ በጣም አዝናለሁ። አባይ እራሱ ስመኘው የት ነው እያለ ነው።ይህ የእኔ እምነት ነው። እኔ በብርሃን ለመኖር የማንም ደም በግፍ እንዲፈስ አልፍልግም። ስመኘው የሞተው ከግብፅ ጋር ሲዋጋ አይደለም በግፍ መስቀል አደባባይ ሞቶ ነው የተገኘው ነገር ግን ምንግዜም ጀግና ነው።የስመኘው ደም እለልባት ካላገኘ አባይ ለኛ የስመኘው ደም ነው ።ፍትህ ፍትህ ።የስመኘው መታሰቢያ ጉባ ላይ ያስፈልገናል ።ሌላውን እግዚያብሄር ይፍረደረ ።

ቴዲ አፍሮ ለስመኘው ሳትዘፍን ለአባይ መዝፈን ቀልድ ነው።ለፖለቲካ ማሚያ ሆነሃል። እውነተኛ ብትሆን አባይ መሰረቱ ሲጣል መዝፈን ነበረብህ።ጨዋታው ፖለቲካ ነው።ብዘፍንም ህዝብ ቴዲ ህወሀት ይልህ ነበር።ያልዘፈነበት እኮ ብሎ የሚከራከርልህ ሞልቷል። የቁም ፖለቲካ አስተማሪዎች።አሁንም መልሱ ያሰተሰርያል ነው ።የደረሰብህን ግፍ አወቃለሁ ።ብትሰራም ህዘቡ ይበላሃል ።

የማዝነው የሚፈሱ ደሞች ለአንዱ ዳንኪራ ለሌለዋ ሁልግዜ ሰብራትና የማይጠፋ ሀዘን መሆኑ ነው።ማወቅ ከፈለግህ ደማቸው በግፍ የፈሰሰባቸውን ቤተሰቦችና ልጆች መሆን ይጠበቅብሃል።ይህ ሲገባህና እነዚህን ደሞች ስትከላከል ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው። ብለህ አውራ፣ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ ብለህም ማውራት ትችላለህ።ደም ከፈሰሰ በኃላ የ go fund me ጀግና አትሁን።መሰረቱን ተባብረህ አክም።

በአሳምነው ፅጌ ስም የተሰራው የግፍ ሴራ፣የእነ ጄኔራል ሰአረ መኮንን ደም መልስ ሊያገኝ ይገባል ።ቁስላችን የሚያክምልን እንጂ በቁስላችን የሚታገል አንፈልግም ።

ከዚህ ውጭ ኑረውም ኢትዮጵያ ሞተው ኢትዮጵያ የሆኑትን ኢትዮጵያውያንን ጠይቀህ ተረዳ ብዙ ጀግኖች አሉን ለኢትየጵያውያን ትቸዋለሁ።አንተ ግን ኑረህ ደም አፍሻስ ሞተህም ሲኦል ነህ።

ኢትዮጵያዊያንን ገሎ ኢትዮጵያን መገንባት ከሚሞክር መሪ ይጠብቀን።ሞተውልን ኢትዮጵያ የሆኑልን ክብር ለነሱ ነፍሳቸው በገነት ትኑር።የውጭ ጠላት ትግልን አይደለም የምልህ፣ከወንድምህ ጋር መታገል አቁም።

ኢትዮጵዊነት ሱስ ነው አልክ ። ሱሷ እንዴት ያደርጋል? እሷን ማጣት ሱስ እንዴት እንደሚያደርግ ማወቅ አለብህ ። ሱስህን ስታጣ ምን እንደሚያደርግ እንዲገባህ የሚረዳቸው፣የሚረዳቸው አጥተው በሱስ አንገታቸውን የደፉትን ጠይቅ፣የማስቲሽ ፣የጋንጃ ሱስ ወዘተ እንዴት እንደሚያደርግ ጠይቃቸው ። ኢትዮጵያን ሱስ ከሆነችብህ የሱስህን ስቃይ አሳየኝ ።ለማ እንኳን በሱስ ስቃይ ሪሃብልቴሽን ላይ ነው ሃሃሃ፣፣

ባለሃብቶችምን የሚያገለግል፣ድሃውንም፣ ጋዜጠኛውን፣አርቲስቱን መላው የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያገለግ ሴክተሮች ያስፈልጋል።ይህ በሌለበት መሻገር አይቻልም።

- ባለሀብቶች ከዶላር ማግኘት ጀምሮ የተደመረና ያልተደመረ መመሪያ አለባቸው እኩል አገልግሉን ።
- ድሃውን፣ገበሬውን ለመርዳት የሚዘረጋ አሰራር መኖር አለበት በዘላቂነት ።

We need how to fight poverity strategy,

የኢትዮጵያ ሀብት በሙሉ ለኢትዮጵያዊን እኩል ወይም በአንፃሩ መዳረስ አለበት ። ለልማት፣ለኢንደስትሪ እያልክ ስታፈናቅል አይደብርህም ። አቅም ቢኖርህ አሜሪካ ሄደህ የአሜሪካን ህዝብ አፈናቅልህ ፋብሪካ የምትገነባ ይመስልሃል ።ለአሜሪካ ህዝብ ምን ምን ይዘህ መጣህ ነው ጨዋታው ። ባሪያ አደረጋችሁን ።

ለምሳሌ ከአራት ኪሎ የተፈናቀለውን ህዝብ አፈናቅለህ ልማት ከምታመጣ የአራት ኪሎን ድሃ ኢኮኖሚውን አሳድገህ የአራት ኪሎ ነዋሪ ነው ማድረገረ የነበረብህ ።ወይም ማሳመን አለብህ ።መለስ ነው ያፈናቀለን ለምትሉ መለስ እቅዱን ማወቅ አለብህ በመለስ እቅድ ውስጥ አለመኖሩን እንዴት አወቅህ የፓርክ እቅዱ ።

ከቦሌ እስከ አራት ኪሎ ገፅታ የሚገነባበት ቦታ ነው መለስ ለምን እንደፈለገው ማወቅ አለብህ ።የገንዘብ ምንጭ የሚጠብቁ እቅዶች አሉ ።አዲስ መሪ ሲመጣ የአለፉ መሪዎችን እቅድ ሪቪው ያደርጋል የተመቹተን ይፈፅምና እኔ ነኝ ይልሃል ።ፖለቲካ ሊገባህ ይገባል ። እየፈረጅሁ አይደለም ሴራዎችን እንዴት እንደምይታ ሃሳቤን እያካፈልኩህ ነው ።ሁሉም በቦታው ይበልፅግ።

ስለዚህ በሚወደው ቦታ ማንም ሰው ታሪኩ ተጠብቆለት መኖር ነው የሚፈልገው እስከ ድህነቱ ። ከቻልክ ደህነቱንን አጥፋለትና ባደገበት እስከ ባህሉ ይኑር ።ካልቻልክ መጠበቅ አለብህ ግዜአቸው እስከሚመጣ ።አራት ኪሎ አድጋ ቻይና ቢኖርባት ለእኔ ዜሮ ነው።

የአሮሞን ህዝብ አታታለው ለዲሞግራፊ ብለህ ከአደገበት ከሰፈሩ አምጥተህ ቦሌ ብታሰፍረው ለሱ ምኑ ነው ያደገበት ሰፈር፣ባህል ጨዋታ ይበልጥበታል ። በአደገበት ቀየ ልማት አምጣለት ። ነገር ግን የሚመቸው ሊኖር ይችላል የእኔ ሃሰብ ነው ።

እያልኩህ ያለሁት ለፖለቲካ ጥቅም ብለህ አንደ የሱርማን ብሄሮች ከቦታው አፈናቅለህ አዲስ አበባ ወርቅ ከምታነጥፍለት

በአለበት አሳድገው ማሳደግ ካልቻልክ እስክትችል ጠብቅ ።ዲሞግራፊ ለማስፋፋት ብለህ የምታደርገው ተፅኖውን ነው የምነግርህ ገባህ ።አውቃለሁ በማንነታችን እንደሚወስን ። ሁሉንም ዳይሜንሽን ማጥናት ያስፍልጋል ።you must be multi dimensional if you want solve a problem.

- ያስገነባሽው ፓርክ ያመጣላቸውን ጥቅም ያለ ኢትዮጵያውያን አሉ ። ደስ ይላል ሌላውንም እይ ነው ጥያቄአችን ።
- ባለቡናማው አይንና  የፒኮኳ ፣ ሁሉም የአይን ጡንቻዎቻቸው የሚሰሩ አይመስለኝም ።ለአይን ስፔሻሊስት ሪፈር ፅፌላቸው  አለሁ። ከዚህ ውጭ፣

ለቀጣዩ ትውልድ ትተህ የቤት ስራወን የራስህን ፍልስፍና እንደ አይጥ ሞክርብን ይህ መንግስት መሆን ለምትፍልጉ በሙሉ ነው መልዕክቴ።ዴሞክራሲዊ ምርጫ አካሄድክም፣አላካሄድክ  ስልጣን ላይ ነህ።ነገር ግን መሰረታዊ ችግሮችን ሳትፈታ ያው ችግሩ እንደዘረ መገንዘብ አለብህ።

ማወቅ ያለብን ጃዋር መሀመድን የፈጠረው የተቃወመው ኃይል ነው።አነግንም ጭምር ሌሎችም ተመሳሳይ ናቸው።ሳትረዳኝ፣ሳታሳምነኝ  በጭፍን ስትናገር ተቃዋሚህ አድርገህ ትፈጥረኛ አለህ።ጃዋርን፣በቀለ ገርባን ወዘተ ብታስር ሌላ ጃዋር፣በቀለን ትፈጥራለህ። አሁንም ምንጨን አክም።Free all poltical prisnor.

የኢትዮጵያ **7** ኛው ንጉስ ሀገር እየመራህ ስለሆነ ይህን የማድረግ ዕድል አለህ ምርጫ አካሂደህ ማንም ቢመረጥ የሚመራ ተቋም ከሌለ አንተም ነገስክ ሌላ ለኛ በ **17** መርፌ እንደተባለው ነው።

ተቋም ለመገንባት በደም ውስጥ ካለፍክም ያው አኬልዳማ ነው። ስለዚህ ብልፅግና አኬልዳማ ሆኗል በንስሃ እስካልታጠበ። ከዚህ ውጭ  ንጉስ ሆይ እንቁላል ሰብረህ የወጣኸውም ለራስህ ነው። ለክብር እና ለንግስና ነው።

ለኢትየጵያ ህዝብ አሁንንም ልክ 17 ዓመት  በመርፌ ቁምጣውን ጠቅሞ እንደመጣው ነወ። የሰሩትን ታሪክ ባልክድም።ቅጠል አንጥፊህም ተኛህ፣የሸቦ መኪና ነዳህም ፣ የሃሳብ ኮንፎርት ኖረህም ያው ለራስህ ነው። ምክንያቱም ደሞች እየጮሁ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የአቤል ደም እስከአሁን ድረስ እየጨኸ እንደሆነ ታውቃላችሁ እስከ አሁን ድረስ ማለትም የቃየል ዘር በምድር እከሚጠፋ ድረስ የአቤል ደም ይጮሃል።

የኢትዮያ 7 ኛው ንጉስ ሆይ የአቤሎች ደም እየጮኸብህ ለምን መስማት አቃተህ ለማንኛውም ቅዱስ መላዕክተ ሞት አፍንጫህ ላይ ነው።የእነዚህ ዶሞች ግፍ እግዚያብሔር ጋር ደርሰዋል በዘርህም ተላልፈዋል።ለህዘቡም ይቅርታ ጠይቅ፣ንሰሃ ግባ፣ንሰሃ ግባ፣ንሰሃ ግባ።ይህ በደም ላለፋችሁ መንግስታትና ህዘቦች ጭምር ነው።

የኢትዮጵ ህዝብ ሆይ ማወቅ የሚገባችሁ ማንኛውም ነገር ማለትም መከላያ፣ፖሊስ፣ፍርድ ቤት፣ሁሉም የመንግስት ተቋማት በቁጥጥሩ ስር የሆነ መሪ ምንም አያውቅም የሚሉ ደጋፊዎች እና ተደማሪዎች ፍርፋሪውን የበሉ ናቸው።

የኢትዮጥያ ህዘብ ሆይ እባካችሁ ፍርፋሪ አትብሉ ባይበላስ ቢቀር እንደ ኢሳት፣ኢዜማ ትሆናለችሁ።አብዛኛዎቻችን ድሃ ነን ፍርፋሪ  እንበላለን  እኔ ለማለት የፈለኩት ማንነታቸውን ሸጠው የመንግስት ሽርፍራፌ የሚያገኙትን ነው እንጂ ድህነት ፍርፋሪ የሚያበላንን አይደለም።

እደግመዋለሁ የኃማኖት አባቶች ሆይ እባካችሁ ፍርፋሬ አትልመዱ ህዝብ እያለቀ ቤተመንግስት ገብታችሁ ቡራኬ ትሰጣላችሁ፣የኢትዮጵያ ህዝብ ሲያልቅ ምንም መልስ ያልሰጠ ፖሊስ  ልደቱን ሲያከብር ቡራኬ ትሰጣላችሁ።በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ ከእንደዚህ የህዝብ ክደት እግዚብሄር ይጠብቀን።

በመጨረሻ ለማለት የምፈልገው ስለሂወታችንና ስለነፍሳችን  መሰረት ነው። ስለ ኃይማኖታችን አለም አቀፍ ህግና ሀገራዊ ህግ እንዲወጣ የሃሳብ ንቅናቄ ቢኖር መልካም ነው።

እስላም ሆነህ ኦርቶዶክስን መተቸት አትችልም፣ጴንጤ ሆነህ ድግልን መተቸት መንቀፍ አትችልም፣እስልምናንን መተቸት አትችልም።

ስለ እምነትህ መርምረህ እምነትህን አስተምር እንጂ ጌታችን መድሃኔታችን እየሱስን እየነካህ፣እመቤቴ ድንግል ማርምን እየነካህ ማስተማር አትችልም። አንተ የምትነካው ለእኔ ፈጣሪየ ነው፣እናቴ ናት የመዳኛየ ሚስጥር ናት።

ስለዚህ የተደነገገ ሕግ ያስፍልጋል።ማንም የማንንንም የሓይማኖት ቤተክርስትያኖችን፣መስጊዶችን ወዘተ ማቃጠል አይችልም። ሰማይ ይፈርዳልም፣ ምድራዊ ህግም ያስፈልጋል።

ለምሳሌ ለዶክተር ዛኪርና ለተከታዮቹ ጥያቄዎች አሉኝ፣ የኦርቶዶክስ ተዋህዶን ለመተቸት ከምትሞክር እስልምናን አስተምር እሲኪ ወደ ጥያቄየ፣

1. መፅኃፍ ቅዱስ ቁርዓንን እንደሚቀድም ታወቃለህ

2.ቁርአን ለነብዮ መሃመድ እንደወረደ ታውቃለህ በጀብሪል አማካኝነት

3.የእስልምና መሰረቱ አላህ አንድ ነው፣ አይወለድም፣ አይወለደም ብሎ ማመን ነው።

ስለዚህ አላህ ቁርአን ሲልክላችሁ

አላህ አይወልድም አይወለድም ብሎ የላከለችሁ፣

- ቅዱስ እግዚያብሄርን(አብ፣ ወልድ፣መንፈስ ቅዱስን/ቅድስት ስላሴን ለመቃወም አይመስልህም)
- ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንህ አለሁ የሚለውን ቃልኪዳን ለመቃወም አይመስልህም?
- ቅድስት ድንግል ማርያምን ለመቃወም አይመስልህም?
- ሚስጥረ ስጋዊ ለመቃወም አይመስልህም?
- ሌላወ አደምና ሀዋ ከገነት/ከጀነት መባረራቸውን ታወቀለህ።ከአላህ ጋር እንዴት ታረቁ?

ስለዚህ የሰውን ሐይማኖትን ከመንካት እምነትህን መርምር ለምዶባችሁ ነው። መቃወም የጀመረው ቁርአን የቀደመ እውነት ስላላ ነው እሱም ወልድዋህድ ነው። የገባችሁ አይመስለኝም ልንገርህ ቁርአን መሰረቱ አላህ አይወልድም አይወለድም ተብሎ ለመፃህፍ ቅዱስ መልስ ለመስጠጥ የተፃፈ ምድራዊ መፅሃፍ ነው።

እውነት ቢሆን አላህ አንድ መሆኑ፣አለመወለዱን ተብሎ መመሪያው መውረድ ያለበት ለአደም፣ወይም ለኖህ፣ወይም ለኢብራሂም፣አልያም ለኢስማኤል፣ወይ ለዳውድ መሆን ነበረበት ከስንት ዘመን በኃላ ለምን ለመሃመድ።ከመሀመደረ በፊት መሰረታችሁ ምንደን ነው?

ምክንያቱ ግልጽ ነው እግዚያብሄር ወልድ ዋህድ እየሱስ ክርስቶስን ለመቃወም ነው።

ሌላው ለእኔ ጅብሪል እና ቅዱስ ገብርኤል አንድ አይደሉም ቅድስት ድንግል ማርያምን የመወለዱን ዜና አብስሯት እጥፍ ብሎ ጅብሪል ሆኖ አላህ አይወልድም አይወለድም የሚል ቁርዓን አወረደ ቀልድ ነው።

ኃይማኖትህን መርምር እንጂ የማንንም አትንካ። ስለዚህ ንቅናቄውን ለሃይማኖታችሁ የምትቆረቆሩ ሁሉ አስኪዱት ሃሳቡን ሰጠኋችው እንጂ እኔ ሶሻል ሚድያ ተጠቃሚ አይደለሁም።

መምህር ዘመድኩን በቀለ እና እሱን መሰል ለኃይማኖት ቀናዊ የሆናችሁ እርዕሱን በሚመቻችሁ አድርጋችሁ ንቅናቄውን ምሩት ሁሉንም ኃይማኖት ባሳተፈ አድርጉት።

እባካችሁ ማንም የማንንም እምነት መንካት አይችልም። እኔ ዶክተር ዛኪርን የጠየኩት እስልምናን ለመንካት ሳይሆን እየሱስ ክርስቶስ አምላክ አለመሆኑን ለማስተማር ከመድከም አላህ የባህሪ ልጅ እንዴሌለው አሳምነኝ፣የባህሪ ህይወት እንደሌለው አሳምነኝ።

**303** ጥያቄ አምላክ ክርስቶስ አምላክ አለመሆኑን ለማስረደት ከምትደክም በ **303** መንገድ አላህ ፈጣሪ መሆኑን አስተምር።እኛ ስለክርስቶስ አምላክነት የማይቆጠሩ መልሶች አሉን።

- ሌላው ፓስተር ዳዊትና መሰሎቹ እምነትህን አስተምር እንጂ ማርያምን አትንካ እኛ ማሪያም ማማለዷን የምናውቀው በ google አይደለም ጐግልማ ስጠይቀው ፓስተሩ ዳዊት አውሬው መጣ ማርያም አታማልድም አለኝ። አሪዎስ ብየ መለስኩለት። በአፋችሁ አትፀዳዱ።ለነገሩ መምህር ምህረት አብ አሰፋ መልሱን ሰጥቶሃል። መምህር አገልግሎትህን እግዚያብሄር ይባርክ ንቅናቄ ያስፈልጋለል የማንቂያ ደወል ጋር አስኪደው።
- የመጨረሻ ነጥቤ B.G,I Ethiopia የሚለውን ኩባንያ ይመለከታል ቅድስ ጊዮርጊስ ቢራ የሚል ቢራ እንደሚያመርት ይታወቃል ቢራው ጠርሙሱ ላይና ቆርኪው ላይ የሰማዓቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ስዕል አድኖ ይጠቀማል።

ይህ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምን ማለት ነው? ለአንድ አንድ አማኝ ፀበል ሊመስለው ይችላል ዋናው ቁም ነገር ቆርኪው ላይ ያለው ስዕል አድኖ እየተላጠ የት እንደሚጣል ማሰብ ነው፣ቆርኪው፣ስሙ የተፃፈበት በየቆሻሻው እየወደቀ ነው።

በየዳንኪራ ቤቱ ስሙ የተፃፈበትን፣ስዕል አድኖ ያለበትን ይዘህ ዳንኪራና የሴት ወገብ ይዞ መጨፈር ፣ዝሙት ማስፋፊት የሚያሳዝን ድርጊት ነው።

የኢትዮጵ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ይህንን ሳታወግዙ በአራዳ ጊዮርጊስ የምትቀድሱት ቅዳሴ ጠብ አይልም ስልዚህ ምዕመናኑን አስተባብራችሁ B.G,I Ethiopia ን ልትከሱ ይገባል።

ቢራውን ማንም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ተከታይና ሁሉም የኢትዮጵ ህዝብ እንዳይጠጣ ማውገዝ ይገባችኋል።

መጀመሪያ ቢራወን የሚያመርተው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ ነበር በአሁን ሰኣት ፋብሪካው የ B.G,I Ethiopia ንብረት ነው።

ስለዚህ ኩባንያው ከተመሰረተበት ጊዜ ጀመሮ የተሰላ ካሳ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትን ይገባታል።

አሁንም ያልገባችሁ አለምን እየመራ ያለው **Brand and symbol** ነው። ቅዱስ ጊዮርጊስ የሚል ስምና ስዕል አድኖ በመጠቀሙ ገበያወን ለረጅም ግዜ ተቆጣጥሮታል።

ችግሩ ግን ያላአግባቡ የኢትዮጵያን ገበዝ፣የነፃነታችን አርማ ስዕል አድኖ፣ስም በየቆሻሻ ቦታው ወድቆ ማየት ነው።

የእግር ኳስ ቡድኑ ስም በእኔ ዕይታ ችግር የለውም ነገር ግን ውይይት ያስፈልጋል።ይህንን እንደምሳሌ አነሳሁት እንጂ ሌሎች ተቋማት ኃይማኖታዊ ስሞች የሚጠቀሙ ስራቸው ተፈትሾ መታየት አለበት።

ለማለት የፈለኩት አንድ ኩባንያ ቅዱስ ሚካኤል ብሎ የቢራ ፋብሪካ ከፍቶ ቅዱስ ሚካኤል የሚል ቢራ አምርቶ የቅዱስ ሚካኤል ሰዕል አድኖ ቆርኪውና ጠርሙሱ ላይ ለጥፎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶከስ አማኞች ስዕሉን ላጥ አድርገህ ጥለህ በቅዱስ ሚካኤል ቢራ ስትዝናና።

እንደ ብስራተ ገብርኤል ሆስፒታልና ትምህርት ቤት፣እንደተክለኃይማኖት ሆሲፒታል፣ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና የመሳሰሉትን እየተቃወምኩ አይደለም ይብዙልን ሳር ቅጠሉ በስማቸው ይጠራ።

ስለዚህ B.G,I Ethiopia ካሳ መክፈል አለበት በካሳው ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብረ ይድራስ ቤተክርስትያን በየክፍለ ሐገሩ መሰራት አለበት። ኮምቦልቻ ደቡብ ወሎ B.G,I Ethiopia ዋና መስሪያ ቤት ያለበት ነው።

መታሰቢያወን ከምቦልቻ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብረ ይድራስ ቤተክርስትያን ማስራት ቢጀምር የእኔ ምኞት ነው፣እግር ኳስ ቡድኑም ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብረ ይደራስ የሚለውን ስም ቢጠቀም ደስ ይለኛል፣ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብረ ይደራስ ስታዲዮም ቢገነባ በስሙ ብዙ ካሳ እንፈልጋለን።

የኦርቶዶክስ አባቶች፣መምህራን፣ዘማርያን፣ምዕመናናን ይህን ሳታሳኩ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን መቀደስ፣ መስበክ፣ማመስገን ከንቱ ነው። ይህንን ሀሳብ ያነሳችሁ እንደነበራችሁ አውቃለሁ የሰማእታቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በረከት ከናንተ ጋር ይሁን አሜን። በናንተ ላይ ኃላፊነቱን የጣልኩት ተሰሚነት ስላላችሁ ነው።

የማጠቃለያ  መልእክቴ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ አባቶችና አማኝ ምዕመናን ነው።ለምን ቤተክርስትያን ትቃጠላለች? ችግሩ የማን ነው? ለምን ጠላቷን ማሸነፍ አልቻልንም? ቤተክርስትያናችን እሳት ያቃጥለዋል ወይ?

በእምነቴ ቤተክርስትያንን እሳት አያቃጥለውም የእኔ መልሴ።በቤተክርስትያኑ ውስጥ ያሉትን ንዋየ ቅዱሳት አሰቡ በየቀኑ መንፈስ ቅዱስ የሚወርደበትን መንበር አስቡ፣፣፣፣፣፣፣ይህ ሁኔታ ባለበት እምነት ታዲያ ለምን ቤተ መቅደሱን እሳት በላው።እንዴትስ ደፈሩት፣አንዳዶቻችሁ፣የምትቃጠለው እውነት ስለሆነች ነው ትላላችሁ እውነትን እሳት ያቃጥለዋል እንዴ? በፍፅም። ታዲያ ችግሩ ምንደን ነው?

ዋናው ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ዘመን ሀይማኖት እንጂ የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ያለው አማኝ የለም።ያለው ተራራ አንቀሳቅሷል። የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት ቢኖረን ሊያቃጥሉ የመጡት ተቃጥለው ይመለሱ ነበር።

ስለዚህ ተራራውን አንቀሳቅሱት፣ባህሩን ክፍሉት የሚል ፈተና ነው ለእኔ የመጣብን ስለዚህን አንቀሳቅሰን፣ከፍለን ማሳየት አለብን ፣ማሳየት አለብን ነው።ከዚህ ውጭ እምነት አለኝ ማለት ከንቱ ውዳሴ ነው።

ሲኖዶሱ የሚመራው በመንፈስ ቅዱስ ነው። በጣም ጥሩ በጉባያችሁ ጵራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ፖለቲካ ከምታወራ ለመንፈስ ቅዱስ በእምነት የሚሰማ ፆሎት ማድረስ ነበረብህ።እሺ ታደርሳላችሁ ለምን አልተሰማህም? ምክንቱም ሀይማኖት እንጂ እምነት የለህም።መንፈስ ቅዱስ እንደወረደ ተሰምቶአችሁ ያውቃል። ሲወርድ በአንተ ላይ ለውጥ ማየት ነበረብህ።

መንፈስ ቅዱስ አንድ ግዜ ከወረደለህ ዘላለም በአንተ ላይ ነው።ከጉባኤ ስትወጣ ኤክስፓየርድ አያደርግም።

በቅዳሴ ላይ የወረደልህ መንፈስ ቅዱስ ስትወጣ የት ሄደ።ስለዚህ ቤተክርስትያንን የከበቧት political Monk ናቸው።እውነተኞቹ አባቶች የት ናችሁ።

የሀዋርያትን ስርአት ተከትለናን እንጂ መንፈስ ቅዱስ አልወረደልንም ቢወርድልህ በደመና ትሄድ ነበር።

የሰው ሓጥያት በዝቶ ነው ትላለህ አዎ ሀጥያተኛ ነን በተጨማሪም አንድም መንፈስ ቅዱስ የወረደለት አባት የለም።ቢወርደልህማ ሰይፈ ነበልባል ነበርክ።ስለዚህ አባ የሚለው ስማችሁን አቦሆይ በሉት።ንሰሀ ሁላችንም መግበት አለብን።እናንተ ንሰሀ ግቡና ንሰሃችንን ተቀበሉንን።ስርአት ማስፈፀም ብቻ ሳይሆን እምነት እምነት ሊኖርህ ይገባል።ለዚህ ነው መሪው አሸከር የሆንከው።

የሰው ሐጥያት ሲበዛ እስራኤሎች በፍልስጤም እንደወደቁ አስተምራችሁናል። ታቦተ ፅዮንም ተማርካ ወደ ፍልስጤም ሄዳ ነበር።ማቃጠል፣መንካት አልቻሉም ለምን በኛ ዘመን ይቃጠላል።በሰው ስለተሰራ?

መልሱ አይደለም ነው ምክነያቱም በእግዝብሄር እጅ የተሰራው ፅላት ተሰብሮ ሙሴ በእግዝያብር ትዕዛዝ ነው የሰራው።ምክንቱም ሙሴ በእጁ በትዛዙ ሲሰራ እምነት ነበረው በእግዝያብሄር እጅ እንደተሰራ ሆነለት፣እግዝያቤርም በእጁ እንደተሰራለት አድርጎ ባረከለት።

እምነት ስለለላችሁ ጣኦት ነው የምታስብሉት እናንተ ናችሁ።

በአሁኑ ዘመን የሙሴም፣የአሮን ካህን እምነት ያለው የለም ስርአቱ ነው ያለው። አየህ ባርከህ ያሰመረቅኸው ቤተ ክርስትያን ከተቃጠለ የባረከው መሰለህ እንጂ እግዝያቤሄር አልባረከልህም። መንፈስ ቅዱስ አልወረደልህም።

ስለዚህ እምነት ያስፈልገናል ፓትሪያልኩ ለምንድን የሙሴን በትር የያዘው ለስርአት ብቻ እምነት ቢኖረው ሙሴ እኮ ነው።

ባህሩን ከፍለህበት፣ርኩስ መንፈስን ውጠህበት ወደ ከነአን ጉዞ መጀመር ትቻላለህ ነው እያለኩህ ያለሁት። በትረ አሮንን ይዘህ ባሪያ አትሁን። እናታችን ፅዮንን ይዘህ ተገኘ አትሁን ፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣

ቤተክርስትያን ተቃጥሎ የእግዝያብሄር ክብር ተነክቶ። ቤተክርስትያን ለማሰራት አትሯሯጥ።ቃጠሎን አስቁመህ።

ከዚያ በኃላ ግንበታ ጀምር።

እኔ ሸክሜ የከበደኝ ኃጥያተኛና በስቃላ ነኝ።ነገር ግን ብዙ ጥያቄ አለኝ።

የጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ደም በመስቀል ላይ በቀራኒዮ ሲፈስ ሊቀ መላዕክት ቅዱስ ኡራኤል ደሙን በፅዋ ቀድቶ ወደ ሰማይ ከፍ ብሎ ደሙን በአለም እደረጨውና ቤተክርስትያንም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በእነዚህ ቦታዎች እንደሚታነፁ ቤተክርስትያን አስተምራን አለች።

ታድያ በአሁኑ ዘመን ቤተክርስትን እየተገነባ ያለው በዚህ የተቀደሰ ቦታ ነው። አንዳዶቹ ቦታው ይገኝ እንጅ ማንም በግል፣በሼር ያሰራውን አባቶች ትባርካለችሁ።በመባረክም መንፈስ ቅዱስ እንደሚወርድ አውቃለሁ።የተሰጣችሁን ፀጋ ማስተላለፍ እንደምትችሉ አውቃለሁ። ነገር ግን የባረከው ለምን ተቃጠለ።

ሳውድ አረብያ ቦታ ሰጥታህ ቤተክርስትያን ብትገነባ ለእኔ ምንም ላይሆን ይችላል።ምክንቱም የሰጠችን ቦታውን በማን ተመርታ ነው።ለፖለቲካ ወጥመድም ልሰጥህ ትችላለች።ሌላው በማን ተመርተህ ተቀበልካት።ተቀብሎ መስራቱ ሀይማኖታችንን ለማስፋፋት ይረዳል።ዋናው ግን እምነትም አብሮ ሊኖር ይገባል።

አባቶቼ ሁሉም ነገር እንደ <u>ቸርነቱ </u>መሆኑን አውቃለሁ። <u>መተላለፊ ንሰሃየ ነውና ይፍቱኝ</u>። ነገር ግን

አሁንም ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ለ ጴጥሮስ ለሁለተኛ ግዜ ሊሰቀል እንደመጣ የሚገለፅለት አባት ያስፈልገናል።

ሌላው መምህር ግርማንና መሰሎቹን ይመለከታል።ለገበያ በሲዲና በቴዩብ ህዝብን እያስጓራህ ሰይጣን አወጣሁ ከምትል መንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋር ካለ ለምንደን ነው ጠቅለልል አድርገህ ኢትዮጵያን አትነኩ ብለህ የማትገዝትልን።

ለምን ቆሪጥን አትገዝትልንም፣ስለሰይጣን ማወቅ ፃድቅ አያደርግም።አብረህ ኖረህ የተዋረስካቸውን አገልጋዮችህን ነው የምትሰብከው።ማርያም ለምን ካንተ ጋር ከሆነች አትነግርልንም የኦርቶዶክስን ምእመናን ጭፍጨፋ እባክሽ ብለህ ለምን አታማልደንም።ማርያም ካንተ ጋር የለችም።ራሄሎህ፣ሊለት ወዘተ ሸወደውህ ነው፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣፣

የሚቃወምህን ሰው ለመገዘት አንደኛ ነህ።በጣም ዘምነሃል ደግሞ online and phone healing ጀምረሃል።ርኩስ መንፈሶችህ ሰልጥነዋል።ኢትዮጵያ ሆነህ ሄሎ ማን ልበል፣ ከአሜሪካ ነው።ማን ነህ አንተ ጠቋር። ዉጠህ ውጣ። ቀልደኛ ለሰውየው አንተ ያወረስከው ጠቋር ነበር።ወይም ዘሮችህ ያወረሱት።

ሰወን ማስለፍለፍ በብዙ መንገድ ይቻላል።ለምሳሌ የአሜሪካ የስለላ ድርጅትና ሌሎችም ወንጀለኛ/ሰላይ ሲይዙ ሚስጥር ለማስወጣት ብዙ መንገዶች አሏቸው።በሁለተኛው አለም ጦርነት spy monk ነበሩ ጥናት ለማድረግ ሞክሩ።

ሌላው የውሹ ባለሞያዎችን፣የቴኳንድ ባለሞዎችን ፣የማርሻል አርት ወዘተ ባለሞያዎችን ተመልከቱ።there is a practice to connect physical with mental.this is a training to acquire a sprit through meditation.In this concept you can see what is coming behind you with closing eye. Ask them for more.

ብሩስ ሊ ሳይመታ ይጥልሃል።you can transefer physical energy to the air and you can strike.like other energy can transefer in their medium.even they can touch you with out actual touch.read,ask and search.

ኢትዮጵያውያን ሆይ ብሩስ ሊ መስቀል ይዞ ቢመጣ ያሰግድሃል። አሜሪካን ጋት ታለንትድ፣አይድልስ ወዘተ ላይ የሚወዳደሩ አስማተኞች መስቀል ይዘው ቢመጡ ያሰግዱሃል።

የቻይና ካራቴዎች የት እንደሚሰለጥኑ ታወቀላችሁ ቴምፕል አላቸው ኤሸንት ቴንፕል እነዚህ የእነሱ የስልጠና ገዳማት ናቸው የቡድሃ ገዳማት ምክንያቱም መንፈስ ማግኘት ስለሚፈልጉ በስልጠናው።

እያወራሁ ያለሁት ስለእነሱ ኤሸንት ገዳም ነው ገዳም ሲባል ኦርቶዶክስን ነካህ እንዳትል።

ምክንያቱም የእኛ ቅዱስ መንፈሳዊ ገዳም ነው።እያወራሁ ያለሁት ስሌሎቹ ገዳም ነው።

እያልኩ ያለሁት መንፈስን መርምሩ ነው።ገዳማውያን ስትሆን ፈተናዎች ይበዛብሃል የበቃህ፣መንፈስ ቅዱስ ያደረብህ መስሎህ እንደ ባህታዊ ገ/መስቀል የዮጋና ሌሎች መንፈስ ይዘህ ልትወጣ ትችላለህ።

መንፈስ ቅዱስ ካደረብ heal the world. እግዚያብሄር ስላላሰረላቸው ነው የሚል መልስ እንዳትሰጠኝ።

መንፈስ ቅዱስ እየመረጠ ነው እንዲ የሚያስረው። እሺ መርጦም ሊያስር ይችላል።

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከአንተ ጋር ካለ ሀጢያተኛም ብንሆን ለምን አታማልደንም።አንተ እኮ በስጋ እየኖርክ ያለህ ፃድቅ ነህ።ለምን አታማልደንም።ነው ወይስ የመምህር ግርማ ቃል ኪዳን እየተባለ የወደፊቱ ትውልድ እንዲያመልክህ ነው ፍላጎትህ።

ለማንኛውም አሜሪካን አይደል ተወዳደርበት እሺ አቦሆይ ግርማ።

ደጋፊዎቹ ምን እንደምትሉ አውቃለሁ? ኢትዮጵያን አድነህ አሳየኝ? መንፈስ ቅዱስ፣መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ፣ፃድቃን፣ሰማዕታት ከእኔ ጋር ናቸው  አትበለኝ።

ሰው አስለፍልፍህ ከአቡነ ተክለኃይማኖት ጋር ትነፃፀራለህ ደፋር ጠንቋይ ነህ።ከቤተክርስትያን ውጣ። ጠብቅ ግዜው ሲመጣ እያንጓለለ ቁጥር 2 ይሰራልሃል።ሰይጣናዊ ሴራችሁንና የገንዘብ ፍላጎታችሁ አሳወቀኸናል።አሰራራችሁን ማሳወቃችሁ ጥሩ ነው።

ሌላው የአባቶቻችን ጥበብ እያሉ የሚመፃደቁባቸው መጽሀፎች በአብዛኛዎቹ አስማትና የሰይጣን መፅሀፍ ነው።ጥበብን መርምሩ፣ለዩ።

እኛ የምንፈልገው የመንፈስ ቅዱስን ጥበብ ነው።እንደ ኤልያስ በሰረገላ፣እንደ ሀዋርያቱ ማርያምን፣ከገነት እንደትመጣ ማድረግ፣እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ በደመና መመምጣት፣ ሰማያዊ ቅዳሴን ለማየት መብቃት ወዘተ ነው ምኞታችን።።።።።።።

ከመፅሀፍ ቅዱስና ሌሎች ድርሳናት፣ገድላት፣አዋልድ መጽሀፍትን ውጭ ያሉ መጽሀፍት ና መፅሀፍ ቅዱስን መሰረት ያላደረጉ የጥበብ መፅሃፋት የሚሏቸውን መመርመር አለባችሁ።

ጥበብ የምንለው ሁሉ ከእግዝያብሄር አይደለም ምክንያቱም እነ ስምያዝና ጭፍራዎቹ ለልጆቻቸው ያስተማሩትም መኖሩን አትዘንጋ።የመፅሀፈ ቅዱሱን መፅሃፈ ሄኖክን አንብቡ።

ጥቁር አስማት ክልክል ነው ነጭ አስማት ችግር የለውም ትላለህ።ሁለቱም ሀጥያት ነው። መስተፋቅር ክልክል ነው ትልና በነጭ አስማት መስተፋቅር ግን ችግር የለውም ትላለህ ካህኑ ክህነቱ እንዳይፈረስ መስተፋቅር ሚስቱን ቢያሰራ/ቢሰራባት ችግር የለውም ይላሉ ነገር ግን ክህነቱ የፈረሰው መስተፋቅር ሚስቱ ላይ ሲያደርግ ነው።

እያልኩ ያለሁት አቶሚክ ቦምብ፣የተለያዩ የጦር መሳሪዎች የተሰሩት በእግዚያብሄር ጥበብ አይደለም።የሰው ልጅ የበላይ የመሆን ፍላጎት ነው የፈጠራቸው።የአያቶቻቸው የእነ ስምያዝ ትምህርት ነው።

- የእግዚያብሄር ጥበብ በቃሉ በሐር መክፈል ነው።
- የጥበብ መጀመሪያ እግዚያብሄርን መፍራት ነው።ማለትም እግዚያብሄርን ከፈራህ ጥበበኛ ነህ ማለት ነው።ስለዚህ
- የእኔ **$E=mc^2$** እግዚያብሄር ነው። ድል አለ በስሙ። የምን አስማት ነው።
- የተለያዩ የፊልም ርዕሶችን እየጠቀሱ ይህ የኛ ነው ከኛ ወስደውት ነው ቢሉህ ትርጉም የለውም ሁሉም የስምያዝ ከሆነ።
- የመንፈስ ቅዱስን እወቁ ምክንያቱም የእስምያዝ አሰራር መንፈስ ቅዱሳዊ ሆኖ ቀርቦልሃል። ሁሉንም በመፅሀፍ ቅዱስ አይን መርምሩ። ስር መማስ፣ቅጠል መበጠስ የእግዚያብሄር ባህሪው አይደለም እኛ በባህሪው ነው የምንድነው።
- እግዚያብሄር በምክንያት እንደሚያድን አውቃለሁ ይህንንም አሳይቶናን አፈር አይን ቀብቶ፣መፅጎፈ ጦቢትን አወቃለሁ በአሳ ሀሞት እንዳዳነ አስተምራችሁናል። እኔ የምላችሁ ይህ ፈውስ የማን ነው ፣መለየት ነው።

ከእነስምያዝ ልወጣና አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ በዘመናዊ የህክምና ታሪክ ውስጥ የሰውን ልጅ የሰውነት ክፍሎች(Anatomy) የምታጠናው በሰው አስከሬን ነው። ለቀዶ ጥገና ትምህርትም መሰረት ይሆንሃል። የእኔ ጥያቄ፣

✓ በሰውን ልጅ አስከሬን መማር የእግዚያብሄር ጥበብ ነው ወይ?

መልሱ አይደለም ነው ለእኔ። የእናንተን መልስ ተወያዩበት።እያልኩህ ያለሁት የራሳችንን ነፃ አምዕሮ ተጠቅምን ችግራችንን ለመፍታት የመረጥናቸው መፍትሄዎች እንጂ የእግዚያብሄር መንገድ አይደሉም።

- ✓ ሌላው ቀዶ ጥገናን በተመለከተ  እንዬ የቀዶ ጥገና ትምህር  እንዴት ተጀመረ የሚለውን ከባለሞያዎች ጋር ተወያዩ።

እኔ ለማንሳት የፈለግሁት ግን ጀርመን በቀዶ ጥገና ቀዳማዊት ነበረች።አሁን ብዙ አገሮች ቢኖሩም መሰረት ጥላበት አለች በሞያው።

ትምህርቱን ያጎለበተችው  በዘመነ አዶልፍ ሂትለር ነው። አይሁዶቹን በመበለት።ስለዚህ ትምህርቱ ወይም እውቀቱ የሰው  መሰዋት ተከፍሎበት ነው። ታዲያ ይህ የእግዚያብሄር ጥበብ ነው? አይደለም ለእኔ ችግራችን የወለደው እውቀት እንጅ እግዚያብሄርን በመግለድ የመጣ እውቀት አይደለም።ሽምድደህ ያወከውን የእግዚያብሄር ነው አትበል። ሚርተኛ!!

- ✓ ሌላው የበሽታዎች የህይዎት ታሪክ የሚባል( pathogensis ) ጥናት አለ ይህም የአንድ የበሽታን ሕይዎት ታሪክ የምታጠናበት ማለትም አንድ በሽታ የሰው ልጅ እስኪሞትና ከሞተም በኋላ የበሽታውን ታሪክ የምታጠናበት ነው።በዚህ የእወቀት ዘርፍ ብዙ የግፍ ጥናቶች በሰው ላይ ተካሂደዋል።
  - o ምንም መድህኒት ለበሽተኛው ሳይሰጥ በሽተኛውን መከታተል።በየቀኑ የሚታየውን ሁኔታ ማጥናት።ሁሉም አይነት ምርመራውች ይደረጋሉ፣ ህክምና የለም።አላማው ካለመድሃኒት የበሽታውን ሂደት ማወቅ ነው።በእየቀኑ የበሽተኛወን ሰውነታዊ ለውጦችና የምርመራውጤቶችን ማጥናት እስኪሞት።ከሞተም በኃላ ከሰውየው ባዮፕሲ እየተወሰደ ከሞት በኋላ ስለ በሽታው ማጥናት።
  - o ሌላው በሽታውን በመድሃኒት ለማስቆም በመሞከር ማጥናት ነው።በተጨማሪም ምርመራ አብረህ ታደርጋለሁ መድሃኒቱንና ውጤቱን ለማወቅ።
  - o የህክምና ኢቲክስ እንዳለ አውቃለሁ።በተለይ በአሁኑ ግዜ።ነገር ግን ሳይንሱ በግፍ የተጠናባቸው ግዜም ነበሩ። የራሳቸው ከለር ያልሆኑ ሰዎች ላይ ግፍ ሰርተዋል።ለዚህ ነው በጥቀር፣በነጮች፣በህንዶች፣በሞንጎሊያ፣በጥቀር አሜሪካ፣፣፣፣፣ወዘተ ውጤታቸው የተለያዩ መሆኑን የታወቀው የበሽታዎች ባህሪ።
  - o ግልፅ እንዲሆንላችሁ ሩሲያ የኮሮና ክትባት አገኘሁ ብላለች።ነገር  ግን ውጤቱ በሌለዎች የአለም ህዘቦች ላይ ስላልተሞከረ ግኝቱን ለማጽደቅ የሚያስቸግረው ምክንያቱም ብዙ አለማት ላይ ካልተሞከረ ውጤቱ አስተማማኝ አይደለም በአልተሞከረባቸው አለማት።

- በአሁኑ ዘመን ሰብአዊ መብት ስላለ እንጂ አያቶቻችን ጥናት ተካሂዶባቸዋል።አሁንም ቢሆን WHO ና ሌሎች አለማት ከአፀደቁት ይመጣና ክትባቱ ይሞከርብናል።ችግር ሲፈጥርብን ሳይድ ኢፌክቱ ነው ትባላለህ።ሌሎች ብዙ ኮንስፓይሬሲ ቲዎሪዎች እንዳሉ አውቃለሁ።
- እኔ እየገርኩህ ያለሁት ግን እውነቱን ነው። መድሃኒቶች በአጠቃላይ ከሰው ጋር ተመሳሳይነት ባህሪ ካላቸው እንስሳት ጋር ይሞከራል፣ከዚያ በሰው ነው የሚሞከረው።በቃ የመደሃኒቱ ጉዳትና ጥቅም ጥናት ይደረግብናል።ሌላው በሃይማኖት ካወገዝከው እንስሳና እጽዋት መድሃኒት ተሰርቶልህ እየወሰድክ ነው።
- በግፈፍ የተደጉ ጥናቶችን አሉ ቀጥታ የራሳቸው ያለሆነውን ዜጋ ላይ ኩፍኝ፣ቲቢ፣ወዘተ የመሳሰሉትን በሽታ ወደሰውነታቸው በማስገባት በግፍ ጥናት የተደረገባቸው ሰዎች አሉ።
- ምንም እንኳዋን በዘመናዊው አለም ጥናት የሚደረግባቸው ሰዎች የሚመረጡበት መንገድ ቢኖሩም።
- ሌላው ህክምና የግምት ሳይንስ ነው።ምክንያቱም ሆድህን ታመህ ሀኪም ቤት ስትሄድ ሆዴን ያመኛል ሰትለው ለሀኪምህ ግምቶችት ናቸው ወደ አምሮው የሚመጡት ሁሉንም የሆድ እቃ ክፍሎች ያስባል ጨጓራህን፣አንጀትህን ትልቁን ና ትንሹን አንጀትህን፣ጉበትህንና ሀሞትህን ፣ኩላሊትህን ፣ጣንፊያህን፣ፊኛህን፣ፕሮስቴት፣ሴት ከሆንች ማህፀኗን ጨምሮ ሁሉንም የሆድ ክፍሎች የህመም ምልክቶች አንተ ከነገርከው ጋር በመጠየቅ ግምቱን ያጠባል።ሌለዎች የአሰውነት ክፍሎቻችንም ዝምድና ስላላቸው በግምቱ ውስጥ ያካትታል።በምትሰጡት መልስ ግምቱን ያጠባል።ከዚያ ፊዚካል ምርመራ፣ላብራቶሬ ምርመራ ያደርግልሃል።ምርመራዎች በበዙ ቁጥር በሽታህ በትክክል የመታወቅ እድል ይኖረዋል።ኢኮኖሚው እያሳሰባችሁ እንጂ ምርመራ መብዛቱ ለእናንተው ነው ግምቱን ያጠጠበዋል።አንዳዶቹ ለጥቅም ምርመራ ቢያበዙም።
- ለዚህ ነው ጠንካራ ህግ በሌለበት በህክምና ስህተት የሚሞቱ ሰዎች በአገራችን ፍትህ የሚጠፋው።ምክንቱም አንዳንድ ችግሮች ለሁሉም አዲስ ይሆኖናሉ በተማሩት የሃይፖቲሲስ ሳንይስ ስለማይኖሩ አንተ ልጅህ ትሞትና ለቀጣዩ ትምህርት ካሬክላማቸው ትሆናለች።ይህን ችግር የማወራችሁ ኀበዝ የምትሏቸውም ሀኪሞች ችግርን ነው።

o በቸልተኝነትና በእውቀት ማለትም የዝግጅት ችግር የሚጠፉ ነፍሶችንም ይሸፋፍናሉ ነገ በእኔ ይደርሳል እየተባባሉ።በጣም ጎበዝ የምትለውም ዶክተር ገሎ የወጣለት ነው።ብዙ ከገደልክ ሁሉም ልምድ ይኖርሃል።ስለዚህ ትምርቱ የሚሰጠው በሰው ህይወት ነው።

እኔ ልነግራችሁ የፈለኩት ህክምናው አያስፈልግም እያልኩ ሳይሆን የእግዝያብሄር ጥበብ ነው የምትሉትን ነው።ህክምና ሳንይንስ የሰው ልጅ ለችግሩ የፈጠረው መፍትሄ ነው። ከላይ በጠቀስኩላችሁና በጣም እጅግ ብዙ ባልጠቀስኩላችሁ ምክንያቶች ጥናት ተደርጎት የመጣ እውቀት ነው።Medcine is a probable science. It is a science of error and trial. But wisdom from God is always perfect and Holly.

ለምሳሌ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በግ መበለት ይችላል።ብልቱን ማውጣት ይችላል።በግ መበለት ይህን ጥበብ ማን አስተማረህ። በቃ በግን የመብላት ፍላጎትህ።ምንም እንኳን አምላክ በሁሉም መንገድ መኖሩን ባውቅም።አብዛናዎቹ ግኝቶች የእግዝያብሄር የሆነ መንፈስ ካልተጨበረባቸው የራሳችን ችግርን የመፍታት ብቃት እንጂ ጥበብ አይደሉም።ሁሉም ጥብብ ግን የእግዝያብሄር ነው።

አብዛኛዎቹ የእውቀት ምንጮች እግዝያብሄር የሉም ብለው በሚያምኑ ሚስጥራዊ ቡድኖች የተፈጠሩ ናቸው።አማኝ አገር ሲመጡ የእግዝያብሄር ጥበብ ናቸው ይባላሉ።

ከሙዚቃ እስከፊል ሁሉም የዘመኑ ጥበቦች።እግዚያብሄር የሰጠኝ ጥበበብ ነው ብለህ ሞዛርትና ቤትሆቨን ....ወዘተ የመሳሰሉትን ሚስጥራዊ ቡድኖች ያገኙትን ግኝት አትደስኩርብን።

ጥበብ አዋቂ ነኝ ብለህ ቅዱስ ያሬድን ከቤትሆቨንና ከሞዘርት ጋር አታወዳድር።አንቺ ሆየህን፣ባቲህን፣አንባሰልህን ፣ትዝታህን፣ራፐ፣ሂፕ ሆፕህን፣ሬጌህን፣ሮክህን ወዘተ እዛው ጠበቅ አድርግ።

ቅዱስ ያሬድ የኦርቶዶክስ ነው ክብሩን ከፍ ማድረገ ካለባት ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስትን ናት ከዚያ ውጭ ሞዛርት ጋር አታወዳድረብን።ለሚስጥራዊ ቡድን አስተዋዋከው አንተ ምንም ማለት አይደለህም ለራስህ ዲስኩር ካልሆነ።

በፒያኖ ቁጭ ብለህ የሆነ ኖታ ስትጫዎት መንፈስ ሊያርፍብህ ይችላል? የማን መንፈስ ይመስልሃል? የእግዚያብሄር እንዳትል። በቃ የስምያዝ ወይም እንደ ኮንታክ ሊሰትህ ይወሰናል።

የቤቶሆቨንን አንድ ኖታ ብትጫዎት የእሱን መንፈስ ነው የምትጠራው ከአገርኛ መንሶች ጋር ልታዋህደው ትችላለህ።ምክንቱም ኖታውም ፒያኖውም የተሰራው እግዚያብሄርን በካዱ ሰዎች የተሰሩ ናቸው።ሁሉም የሙዚቃ መሳሪያዎችና ስልቶች ማን በማን መንፈስ ተሰሩ ይወስነዋል።ግጥሙና መልዕክቱ ብትልም መልዕክቱም የምታሰተላልፍለት አለማ ይወስነዋል።

ራፕ ብትጫዎት፣ሬጌ፣ሮክ፣፣፣፣፣የእነሱ መንፈስ ነው የሚያርፍብህ በድጋሚ ከራስህ ጋር ልታዋህደው ትችላለህ ገባህ።

ዳንስና ኬሮግራፊዎችን ብትመለከቱም እንደዛው ነው። የውጬን ኬሮግራፊ ስይታይ ቡዳው ከበላህ በጉራጌኛ የማይክልን ዳስስ ልታመጣወ ትችላለህ።ማይክል ጃክሰን ከኛ ወስዶ ነው ትላለህ።የማይክል መንፈስ መጀመሪያ በውስጥህ ነበር እሱ ነው አንተን ጉራጌኛን በማይክል ያሰራህ። ግርማ ወንድሙ ጋር ሪፈር ብየሕ አለሁ።

ምክንያቱም በዳንሳቸው፣በላይታቸው ፣በሙዚቃቸው፣በስቴጅ ግንባታቸው ፣በአልባሳታቸውና በሁሉም ነገራቸው አምላካቸው ሉሲፈርን ነው የሚያስመልኩህ።ስለዚህ የኢኔ የምትለው ካለ በፈጣሪህ አስባርክህ ተጠቀም።

ሌላው ራፕ ቀረርቶ ነው ከእኛ ወስደውት ነው ትላለህ።በ west coast and east cost ቡዳ ተበልተህ ነው።ቀርቶውን በራፕ ስምተኸው ነው።

የቢዮንሲን ስዘፍኚ ሳሻ እንዳረፈችብች አስቢ የሜካብ ሼድሽን ከእሷ ጋር ታመሳስይና ኢትዮጵያዊቷ ቢዮንሲ ትባያለሽ።

ሌላው zodiac shade/make up. ማወቅ አለብሽ ሆሮስኮፕ በማን ተጠና ነው።በሉሲፈርና በጭፍራዎቹ ነው።ዞድያክ ቤዝድ ሜካብና ስታሎች እንዳሉ እወቂ አጥኚ። የሰይጣን፣የሳጥናኤል፣የሉሲፈር ሚስቶች የሚባሉ ሴቶች መንፈሶች እንዳሉ እወቂ።በሰዎች አእምሮ የተሳሉት ደግሞ በነ ቢዮንሲ፣ሪሃና፣ሌዲ ጋጋ፣ኒኪ ሚናጅ፣ቴይለር ሲዊፍት፣ኬቴ ፔሪ ወዘተ በመሳሰሉት ነው።እነዚህ የሉሲፈር ሚስቶች የሚባሉት የሴት ርኩስ መንፈሶች እያደነቃቸኋቸው ባላችኋቸው ሴቶች ዘፋኞች ላይ በማረፍ ሴክሽዋል ሴደክቴቭ ያደርጓቸዋል።እሱን ስታደንቁ ከእነሱ ወደ እናንተ ያርፋሉ።

አብዛናዎቻችሁ ሴት ኢትዮጵያውያን ስታይላችሁን በማየት እንትናን ትመስሊአለሽ ብሎ እንጂ በማንነተሽ የሚጀነጅንሽ/የሚያፈቅርሽ ወንድ ትንሽ ነው። የሉሲፈር ሚስቶች የሚባሉትን መንፈስ በነቢዮንስ በውስጥሽ ስላሳደርሽ እነሱ ናቸው ወንዱን የሚስቡልሽ  ስላንቺ ሌላ ማወቅ አያስፈልገውም ዩ ሶ ሴክሲ ማለት በቂው ነው።ምክንያቱም ከአንቺ የሚፈልገው ሴክሽዋል ሂሊንግ ነው።

አንቺም የምትፈልጊው እሱን ህክምና ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ጄ ዚን፣ክሪስን ፣አሽርን፣ቢበርንም መስሎሽ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም እሱም በነሱ በሉሲፈራውን ተበልቷል።ምርጫው የእናንተ ነወ። እኔ ማንንም የመቃውም ሀሳብ የለኝም።ችግሩ ግን እነሱ የሳጥናኤል ነን ብሎው አምነውበት ነው፣ አንቺ ግን ማህተብ አድርገሽ ኢትዮጵያዊቷ ሪሃና ነሽ። እንደሷ አምነሽበት ከሆነ ምርጫው የራስሽ ነው።ስለዚህ እውነት የገባቸው ወንዶች ስታይልሽን ማለትም የአለባበስ፣የሚካፕ፣የአወራር ባህሪሽን አይቶ ማን ምን መሆንሽን ማወቅ ይችላሉ።ድብቅ ባህሪሽን ማወቅ ይችላል።ሜካፕሽ የዞድክያክ ባህሪሽን ስለሚናገር ለኮኮብሽ በሰይጣን የተሰጠሽን ባህሪ ማወቅ ስለሚቻል።አንችን ለማንበርከክ መጥፎ ወንዶችም ይጠቀሙብሻል።

ሴት እህቶቼ ሜካፕ ልትሰሩ ስትሉ የተወለዳችሁበትን ቀን የጠየቃችሁ ባለሞያ አለ? መልሱን ለእናንተ።የሜካፕ ባለሞያዎች ጥናቱን ያደረጉት በብዙ መንግድ ነው። ከዚህ ውስጥ ኮኮብሽን በማጥናት የኮከብሽን የሚመስል ሜካፕ፣አልባሳት የሚዘጋጁልሽ።

ይህ በውጪ አለም የሚደረገውን የ 666 ሰታይሊስቶች ነው የምነገርሽ። ውጭ ተምረን መጣን የሚሉ ኢትዮጵያውያን ሰታይሊሰትን በዚሁ መነፅር እዩ።

በፊልም አይተሻት የወደድሻትን አክተርስ ስታይሏን አይተሽ ብትሰሬ የእሷ ዞደይክ ኢፌክት በአንቺ ላይ ይታያል።የአንቺን ዞደይያክ ባታውቂውም።

ስለዚህ ነው በቀን፣ በሰአት፣365 ቀኑን ስታይላቸው የሚለያያው ምክንያቱም ዞድያካቸው በጊዚአቶች ኢፌክት ስላላቸው ነው።ሁሉንም በአምላካቸው በሉሲፈር የተደረገ ጥንት ስለሆነ ሊገባችሁ ይገባል ነው አስተያየቴ።

አንዳንድ ነገሮች ደግሞ ሳንኮራረጅ ሊመሳሰሉና አንድ ሊሆኑ ይችላሉ።ለምሳሌ ጀግንነትን፣ ፉከራን፣ብሶትህን  የምትገልፅበት የድምፅ ቅላፄ አንድ ሊሆን ይችላል።ራፕ የእኛ ነው እያልን የምንከራከረው ትተን እነሱን ብትጠይቅ ከእኛ ወሰዳችሁ ነው ብትል መልሱ ምን ይመስለሃል። ጠይቀህ ተረዳ ነው መልሴ።

ይህን ለማስረዳት የሞከርኩት እውቀትና ጥበብ  የምንላቸው  ሁሉ የእግዝያብሄር  አይደሉም ለማለት ነው።ጥበበቦች በእግዝያብር መንገድ ካላለፉ፣ከልተመረመሩ፣በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን አይን ካልታዩ አሳሳቹች ናቸው።

አዳምና ሄዋን በሀጥያታቸው ከገነት ከተባረሩ በሀኋላ በራሳቸው ፈቃድ ነው እየኖሩ የነበሩት ይቅርታቸውን ተቀብሎ ቃል ቢገባላቸውም በምርጫቸው ነው መኖር የጀመሩት። ስለዚህ በዚህ የህይወት ውጣ ውርድ ግማሹ ልጆቹ አቤል እየሆኑ ግማሾቹ ቃየል እየሆኑ ነው እዚህ የደረስነው።አቤላውያን አምላካቸውን እየተማፀኑ ጥበብን ሲቸሩ፣ቃየላውያን ደግሞ ለራሳቸው ችግር የራሳቸውን የእውቀት መንገድ መርጠዋል።

በተጨማም የስማያዝ ጭፍሮችንም የሰውን ልጅ ተቀላቅለዋል የሰውን ልጅ እውቀቶችን አስተምረዋል።ለምሳሌ መዋብን፣ጌጣጌጥን፣የጦር መሳሪያ መስራትን፣ስር መማስና ቅመማን፣ኮኮብ ቆጠራን፣ዘፈንና ዳንኪራን ወዘተ። ስለዚህ ጥበብህ ከየትኛው ወገን ነው? ተወያዩበት።

ሀኪም አበበችና መሰሎች እስኪ በዲስኩርሽ የእግዝያብሄር የሆነውን አሳይኝ።የዘሮችችሽን የእነስምያዝን እውቀት የእግዝያብሄር መሆኑን ትደሰኩሪአለሽ።

እግዝያብሄር ለችግራችን መልስን የሰጠን በጥበብ ተወልዶ በመስቀል ስጋውን ቆርሶልንና ደሙን አፍሶልን ነው።

ሀገራችንን ዝቅ ያደረጋት እናንተ ጥበብ የምትሉት መተት ተብትቦ ይዞን ነው።አብዛኛው ሱሰኛ የሆነውን ትውልድ ብትመለከቱ የእናንተና መሰሎቻችሁ እጅ አለበት። ሱሰኛና እብድ ሆኖ እዲቀር የተደረገው በእናንተና በዘሮቻችሁ ውጤት ነው።አገራችን የምትበለፅገው፣ትንሳኤዋ የሚረጋገጠው እናንተ በእግዝያብሄር ሀይል ስትመቱ እንጂ በእናንተ አይደለም።

መንፈስን ስትመረምር ወገንተኛ ሁነህ አይደለም ለምሳሌ አሸንዳን፣ሆለልየ፣ሶለል ወዘተ የሚባሉ ትውፊታዊ ባህሎችን በመፅሀፍ ቅዱስ ሳትመረምር ኢሬቻን ስትመረምር የዘረኝነትህን ጥግ ለማሰየት ነው።ገብቶሃል። ዳንኪራዎች ሁሉም መንፈስ ቅዱሳዊ አደሉም። ከዚህ ውጭ የአሸንዳን ባህል በዩኒስኮ ለማስመዝገ እየሮጥክ ኢሬቻን መንካት የኦሮሞን ህዝብ መናቅ ነው።

በሃይማኖት አይንን ከአየህ ግን ጥላሁንም፣ቴዲ አፍሮም፣አጫሉም ዘፋኝ መሆናቸው በኦርቶዶክስ ሀይማኖትክ ክልክል ነው።

ከዚህ ውጭ ቴዲ አፍሮን አድንቀህ በዘፋኝነቱ አጫሉ ሁንዴሳን ሀጥያት ነው አትበለው። ሓጥያት ከሆነ እኩል አስተምር።ከዚህ ውጭ የብሄርህን ጥግህ አታሳየኝ።ለእኔ አብዛኛወቻችን የተዋረስናቸው ባህላት ጥናት ቢደረግባቸው ሀይማኖት ያወግዛቸዋል።

እንደነጮቹ ካርኢቫል thanks giving day ነው ካልን ማንን ነው የምናመሰግነው።የፈጠራችን አምላክ ነው ካሉ መብታቸው ነው።ከሃማኖት አንፃር አንተ ተሳስተሃል። ነሃሴ፣መስከረም ላይ የአማራን፣የትግራይን፣የደቡብን በመስቀል ስም የሚደረጉ ትውፊታዊ ባህሎችችን አስተያየት ሳትሰጥ ምን ነው ኢሬቻ ላይ እሳት አደረገህ።

የአገውንም፣የወላይታንም፣የጉራጌ ወዘተ ትውፊቶችን  ለምን አስተያየት አልሰጠኸባቸውም ባህሉ በሁሉም አገር መኖሩን አስተምረሃል መምህር ችግሩ ግን መቼ ነው ስአቱ የሚለው ነው።መረጃውን የሰጠህበት ጊዜ ይወሰወናል።አሸንደየ ሲከበር ሁሉንም ዳሰህ በሀይማኖት ብታስተምር ልክ ነበርክ ለእኔ።ቅዱስ  ሳሊበላ ሶራ ነው ምንጣፋ ሲባል እያጨብብክ ሌላውን አትንካ።የቅዱስ ላሊባላ ምንጣፍ ሶራ መሆኑን የኦርቶዶክስ ዘማሪያን ናቸው ሊዘምሩ የሚገባው።

ለአባታችን ተክለሃማኖት በጉራጌኛ ቢት ዘፈን ብዘፍንላችው ምንድን ነው የምትለኝ።ግጥሙ ነው ዋናወ የምትለው አንተ። ይመችህ ሁልህም በገባህ ልክ ነው ጉዳየ።

ሌላው ለምንድን ነው ጴንጤዎች በኦርጋን፣በጊታር በመሳሰሉት መሳሪያዎች ሲያመሰግኑ የምትቃዎመው ብዙ ምክንያቶች ይኖራሉ።

- ✓ መሳሪዎቹ አለማውያን ሰዎች የፈጠሮቻቸው ናቸው
- ✓ ሌላው አለማዊ ዘፈኖች የሚሰራባቸው መሳሪያዎች ናቸው

✓ ሌላው መሳሪያዎቹ የተሰሩት አምላክ የለም በሚሉ ሰዎች ነው

✓ እንዲገባህ ድንግል ማርያምን በዘመናዊ መሳርያ ብትመሰግን ቀኖናችን አይፈቅድም ማርያምን ስለካዱ ነው ምክንያቱ እንዳትል

ስለዚህ ነገሮችን በብዙ መንገድ ለማየት እንሞክር።

በጣም ግልጽ እንዲሆንልን ማሲንቆ፣ዋሽንትና ክራር የኦርቶዶክሳዊ ቀኖናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው እንዴ? ወንጌላወያንና አባቶች ይመልሱት።በተለይ ማሲንቆና ዋሽንት መልሱልን እኔ አላውቅም።

አባታችን እዝራ በማሲንቆ እንዳመሰገናት ታስተምራላችሁ፣ቅዱስ ስእል አድኖ ላይም አለ።ስለዚህ በቀኖናችን ካለ የኦርቶዶክስ ነው። እንደንዋየ ቅዱሳት ነው የሚቆጠረው ስለዚህ።የቤተክርስትያን ከሆነ አስከብሩልን ተረ አለማዊ ከሆነ አሰውግዱት ከመዝሙር።ነው ወይስ ለሪሚክስ ነው።

በጣም ግልፅ ላድርገው የቤቴክርስትን ከበሮ ከቤተክርስትያን ንዋየ ቅዱሳትአንዱ  ነው። የዘመናዊ ሙዚቃ ቢታጀብበት መልሳችሁ ምን ሊሆን ይችላል።ሙላቱ አስታጥቄ በአለም አቀፍ መድረክ ከበሮ፣ ፀናፅንና መቋሚ ከሌሎች መሳሪዎች አዋህዱ ኮንሰርት ቢሰራባቸው ንዋየ ቅዱሳታችን በአለም መድረክ ተዋውቀዋል ትላላችሁ ቸግሩ የተመሰገነበት ሉሲፈር ነው። አቶ ሙላቱ አሰታጥቄ ሁሉም ቢደግፍህ ቢያጨበጭብልህ እንኳን ስህተት ነው መልሱ።

ለአለም ማሳወቅ ካስፈለገ ቤተክርስትያናችን፣ ለቤተክርስትያኗ ዕድል ማመቻቸት ነው።

ከዚህ ውጭ የቄሳርን ለቄሳር።

አይ ማንም ይስራው ባርከን፣ቀድሰን ልንጠቀምበት እንችላልን ካልክ።ፒያኖንም ባርከህ መጠቀም ነው።

ማን ሰራው፣ከየት መጣ የምልህ ለምን እንደሆነ ታውቃለሁ? በምትሰራው ነገር ላይ መንፈስህ አርፎ በመሳሪያው ወደሌላው ስለሚተላለፍ ነው።የምትጽፈው ነገር ላይ እንኳን የሚጽፈው ሰው መንፈስ  እንደሚያርፍ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

በመናፍቃን የተሰሩ ቁሶች የእነሱ መንፈስ እንደሚያርፈበት እንድንገነዘብና በግሎባላይዜሽን ዘመን ሁሉን በእምነታችን ባርከን መጠቀም እንደሚስፈልግ ማወቅ ነው።

ይህ ማለት ቅዱሳን አባቶቻችን ዲያቆናትን፣ካህናትንና ጳጳሳት የሚሾሙበትን  መንገዶች ተረዱ።መንፈስን ቅድስናን በመንካት እንደሚተላለፍ ሁሉ።ሌሎቹም ርኩስ መንፈሳቸውን በመንካትና በነኩት ቁስ ማስተላለፍ ይችላሉ።የሰራው ሰው መንፈሱን በሰራው ቁስ ላይ ማሳደር ይችላል ስለዚህ ሁሉንም ባርካችሁ በእምነታችሁ ጀምሩ።በእምነታችሁ ጨርሱ።

ዜማ ደራሲዎችን እስኪ ጠይቋቸው ግጥም ዕፈው ዜማ የሚደርሱ አሉ።ዜማውንም ግጥሙም እኩል የሚመጣላቸው አሉ።ዜማ ብቻ ወይም ግጥም ብቻ የሚደርሱ አሉ።

ሌላው የሙዚቃ መሳሪያ ሲነኩ ዜማ፣ግጥም፣ሁለቱም የሚመጣለቸው አሉ።ለማለት የፈለኩት የሙዚቃው መሳሪያ ሊያናግርህ ይችላል፣አንተም ልትመልስለት ትችላለህ።አንዳንድ አርቲስቶች የሚጫወቱት መሳሪያ እንደሚያናግራቸው ያውቃሉ። መሳሪያው የሚያናግርህ ከዚህ በፊት በሰራው፣በተጫወተበት ሰው መንፈስ ነው፣አዲስ መንፈስ አድሮበት፣የራስህ  መንፈስ ወዘተ አድሮበት።

በሂደት ቀድሞ የነበረውን የሰውየውን መንፈስ ትወርሳለህ ወይም በሂደት የራስህን መንፈስ አሳድረህበት የራስህ መንፈስ ባለቤት ታደርገው አለህ።ዋነው ቁም ነገር መንፈሱ የማን ነው ቅዱስ ወይስ እርኩስ?  በሃይማኖትህ የዚህ ነገር መሰረቱ ምንድን ነው ብለህ አምነህበት ኑር።

ለምሳሌ ስቲቭ ወንደር፣አሊሽያ ኪስ፣ያኒ የተጫወቱበትን ፒያኖ ብታገኝ/ቢሰጡህ መንፈሳቸው አለበት ነው እያልኩህ ያለሁት።ሊያናግሩህ ሁሉ ይችላል።ስትነካው ከጣቶችህ፣ጀምሮ መላው ሰውነትህን ሊቆጣጠርህ ይችላል ጥሩ ዘፈን ልትሰራ ትቻላለህ።ነገር ግን ማወቅ ያለብህ ዘፈን የእግዘያብሄር ጥበብ አለመሆኑን ነው።

የምንኖረው የተመረዘ አለም ነውና ሁላችንም አወቀነው በፆለት እየታገል መኖር አለብን።

ሁሉንም የእግዘያብሄር ጥበብ ነው እያላችሁ አትሸውዱን።

የሰው ልጅ መኪና የሰራው የራሱ መኪና የመስራት ፍላጎቱ እንጂ በእግዚብሄር መንፈስ አይደለም ለዚህ እኮ ነው እግረኛው ፍቅረኛሽን በባለ መኪናው ሹገር ዳዲ የቀየርሽው።ከእግዝያብሄር መንፈስ ቢሆንማ ባርኮሽ ወደ ፍቅረኛሽ ይመልስሽ ነበር።ገንዘብም ያው ነው የእግዝያብሄር ቢሆንማ ለገንዘብ ወንድምህን አትበድልም ነበር።

አውሮፕላንም እንደዛው። All innovations are  problem solving approach methods of human being. ። ምክንያቱም አብዛናዎቹ ግኝቶችን የሰሩት ሰዎች እግዝያብሄር የሉም ብለው በሚያምኑ ሀይሎች ነው በድጋሜ ። ነው ወይስ እየሸወዱን።መንፈሳዊ አባቶችን እና ወንጌላውያንን ጠይቁ መልሱን።

ለምሳሌ መርከብ ብታዩት በእግዝያብሄር የተመራ ጥበብ  ነው። አባታችን ኖህ በአምላኩ እተመራ ነው የሰራው። ለሌሎቹም እንዲዚህ የአምላክ ትዕዛዝ እንዳለ አስተምሩኝ።

ሌላው ጥያቄየ ሳጥናኤል ከመውደቁ በፊት የእግዝያብሄርን ጥበብ ያወቅ ስለነበር ለልጆቹ እያሰለጠናቸው ነው ወይ? ምክንያቱም ሁላችንም የተፈጠርነው  በእግዝያብሄር  ስለሆን።እግዝያብሄር የሰጠንን ቀደመው በርኩስ መንገድ በአቋራጭ ስላገኙት  እንጂ ሁሉም ነገር የእግዝያብሄር ነው። ከሰው ልጅ በተሻለ መንገድ የተደበቁ ነገሮችን  መንፈስ ስለሚያወቅ ነው።እነዚህ ለሰው ልጅ  የተደበቁ እውቀቶች ባለቤቱ እግዝያብሄር ነው።እውቀቱ መቼና እንዴት ተገለጠልህ ነው ቁም ነገሩ። በእግዝያብሄር መንገድ በሰአቱ የሚገለፅልህ ጥበብ በሰይጣን ለማወቅ መጣር ነው ሃጥያቱ።መርከብን እግዝያብሄር ለአባታችን ኖህ እንደገለፀለት አውሮፕላንንም በግዜው ሊገልጥልህ እንደሚችል ማወቅ አለብህ።

ሁሉም እውቀቶች የእግዝብሄር ናቸው መገለጥ የሌለባቸው እውቀቶችም እንዳሉ ማወቅ አለብህ ምክንቱም ሀጥያት ስለሚሆኑ። እነዚህ ድብቅ ሚስጥሮች ለሰይጣንን እየገበርክ መረዳት መሞከር እንጂ ሓጥያቱ፣  ሁሉም ጥበብና እውቀት ከታህታዊት ምድር እስከ ላዕይ ሰማይ ብትሄድ የእውቀት ባለቤት አልፋና ኦሜጋ መድህን ክርስቶስ ነው።እንጂ ሰይጣን እውቀት የለውም በስልጣን ዘመኑ ፈጣሪው የገለፀለትን ከሱ ጋር ያሉትን/የቀሩትን ትንሽ እውቀት ወዳጁ ከሆንክ ያጋራሃል።

ጨረቃ እንዴት መሄድ እንደሚቻል ሰይጣን ያወቀው ከአምላኩ ነው።

አምላኩን ከድቶ እሱን ያመነውን የሚያወቀውን ያህል ይገልጥለታል ስለዚህ ሁሉም ጥበቦችና እውቀቶች የእግዚያብሄር ናቸው። ዋናው ጉዳይ ማን እውቀቱን ገለፅልን ነው? ሉሲፈር የሚያወቀውን ከገለፀልህ አንተ የሉሲፈር ነህ ከሃዲ።እሱ ግን የራሱ የሆነ ምንም የሚሰጥህ ነገር የለም። የሰውን ቀምቶ፣ዘርፎ፣ሰልቦ፣ ነው ሊሰጥህ የሚችለው እንጂ የራሱ የሆነ ስጦታና እውቀት የለም።

በዚህ ፅሀፌ አንድ ነገር ላሳያችሁ ሞክሬ አለሁ ተፅኖ እንዴት እንደንሚፈጠር ምክንቱም ጥበቦች ሁሉ የእግዚያብሄር አይደሉም በማለት፣ ዋናው ሃሳቤን  እውቀቶችን መርምሩ  እንጂ።

ሁሉም በእግዚያብሄር ይታወቃሉ።ሰይጣን እራሱ የእግዚያብሄር የጥበብ ውጤት ነው ።መላእክ በነበረ ግዜ ደስ የሚል ጥበብ ተጠቦበት  ነበር አምላኩን ሲክድ ደግሞ ሌላ ጥበቡን ተጠበበበት፣ገና ሌላ ጥበቡን ይጠበብበታል።በሁሉም መንገድ እዩ።

ይህን ስልህ ደግሞ ማወቅ ያለብህ ዜማና ምስጋና የቅዱሳን መላእክት ግብራቸውን ነው፣ ለፈጣሪያቸው።ስለዚህ በዚህ ሀሳብ ዜማን የፈጠረው እግዚያብሄር ነው። አላማውንም  ግን እንዳትረሳ።

- ዜማውን ለቂጥና ዳሌ እንድትጠቀምበትና ለዳንኪራ እንደትጫወተው ግን ያጫወተህ ስምያዝና ጭፍሮቹ ናቸው።

በህክምና ሰውን እንደምታክም እግዚያብሄር ያወቃል። የእግዚያብሄር መንገዱ ግን በመድሃኒትና በቀዶ ጥገና አልነበረም።  እሱ አልነበረም የአምላካችን ፍቃድ፣ የኛን ፍቃድና የእርሱን ፍቃድ ለዩ ነው ጉዳዩ።

ሌላው አዳምና ሄዋን የግብረስጋ ግንኑነት ማድረግን በገነት አያውቁም።  ሃጥያት ሲሰሩ ግን መተፋፈር ጀመሩ።የሆነ የገባቸው ነገር ያለ አይመስልህም። በሀጥያት የሚገለጡ እውቀቶች መኖራቸውን መረደት እንጂ ሁሉም በእግዚያብሄር ይታወቃል።ስለዚህ አዳም በገነት መኖርን ሳይሆን መሬትን መረጠ። ሁሉም ነገርር ግን በእግዚያብሄር ይታወቃል። ምርጫውን እኛ ነን የወሰነው ። ስለዚህ አዳም በግብረስጋ ግንኑነት ልጁን መተካት ጀመረ።

ከገነት ባንባረር የህወታችን ጣእም ሌላ ነበር። ህይወትን እናጣጥም እልያክ የምትኖረው ህይወት አሁን ሀጥያታችን የወለደው ኑሮ ነው። ስለዚህ አዳም ተፀፅቶ ንሰሃ ገባ አምላክ እኛን ሆነልን።አምላክ ሰው ሆነ።የጽድቅ እመቤትን ሰጠን፣የአሮን በትርን፣የእሴ ስርን፣የሰለሞን ሙሽራን፣የጥበብ መንገድን ፣፣፣፣፣፣ሰጠን

እግዝያብሄር ፍቅር ነው ምስጋና ይገባው።ሰው እንደአምላኩ ፍቃድ መኖር ስላልቻለ ፍቃዱን ባህሪውን የምትሰጠንን እናታችን ቅድስት ድንግልማርምን ሰጠን።

በአጠቃላይ የእግዝያብሄር መንገድ በደመና መብርር ነው። ሰማያዊ የእሳት ሰረገላዎች ናቸው መንገዶቹ።

ስለዚህ ምርጫችን ናቸው ችግሮቻችን። የአገራችን መንግስታት ችግርም ይህ ነው ባለ ስልጣን መሆኑን እንጂ ማን፣ለምን፣እንዴት ወደስልጣን እንደመጣ ይክድሃል።በእግዝያብሄር ፈቃድ ነው ይልሃል።የእግዝያብሄር ፈቃድ መሆንህ የሚለካው በስልጣን ዘመንህ በሰራኸው ስራህና በህዝብህ የተፈፀሙ ደረርጊቶች ናቸው የማን መሆንህን የሚመሰክርብህ።ከዚህ ውጭ ከዘራችን ከአዳምና ሄዋን የመጣች ስልጣን የመያዝና የበላይ የመሆን ፍላጎት ነው።

ስለዚህ ሁላችሁም የምታደርጉት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ትክክል አይደለም።ቢያንስ ሁላችሁም ወደራሳችሁ ተመለሱና ቢያንስ ከ ዳግማዊ ሚኒልክ እስከ ንጉስ አብይ አህመድ ያሉትን አገዛዛዊ ስርአቶች በማጥናት፣የነበሩ ግጭቶችን መፍታት ያስፈልጋል።

ተጨፍልቀን ነው እንጂ እንደ ኢትዮጵያ ትልቅ ሁነን አናውቅም የሚሉትን ህይሎች ሳታሳምን የአንተ ዲስኩር ለራስህና ደጋፊህን ለማስደሰት ነው። እውነት ነው እነዚህን የህዝብ ህይሎች ሳታሳምን ስለኢትዮጵ አታውራ።አውሮፓ መራሹን እውቀትና ፍልፍስና ብታወራ ወደ ስልጣን ለመምጣትና የምታደርገው ጥረት ነው። በናታችሁ የእወቀት ችግር የለባችሁም። ደም መፈስሱን የምታቆሙበት መንገድ ካለ ፈልጉ።

ዛሬ **23/02/2013** ዓ.ም ሌላ አሰቃቂ ዜና ሰማሁ።በምዕራብ ወለጋ ከ **200** መቶ በላይ የአማራ ዜጎች ተገድለዋል።ደም እየፈሰሰ ነው።ደሙን አስቁሙልን።በመላው አለም የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራውያን እባካችሁ ለአለም አቀፍ ፍርደ ቤትና ለመላው አለም አሳውቁልን በግፍ ጄኖሳይድ እየተፈፀመብን ነው።ከዚህ ውጭ ኢትዮ 360 ዎች ፕሮግራማችሁ ሃሳብን የመሸጥ ንግድ ነው።

የአብን ሰላማዊ ሰልፍ ለምን ከሸፈ ብላችሁ የራሳችሁን አስተያየት ከምትሰጡ የፍትህ ዘመቻ በመጀመር ለአለም አቀፍ ማህረሰብ ኣሳወቁልን።ከዚህ ውጭ የሃሳብ ነጋዴዎች ናችሁ።አብን ያልተሳካለትን አላማ እናንተ በውጭ ሞክሩት።

ሌላው የኢትዮጵያ ዲያስቦራ ማህበረሰብ  ሆይ መንግስት መስራት ያልቻለውን ወይም ያላመቻቸላችሁን ታሪክ ስሩ ኦሮሞና አማራ ዲያስቦራው ለምንድን ነው ተነጋገራችሁ እርቅ የማትፈፅጽሙት። እናንተ ታረቁ ሌላ ማውራቱን ትታችሁ።ልዩነቶችን ፍቱ።ሁላችሁም ኢትዮጵያን መስርቱ በመላው ያላችሁ ዜጎች። ከዚያ ለሚፈሱ ደም ታገሉ። ከዚህ ውጭ እደምታውቅና ፖለቲካ እንደገባህ ብተነትን ለእኔ ፣ለእኔ ለህዘንተኛው ምኔም አይደለም። ደሞችን እናስቁም አሁንም ተጨማሪ ደም እንደማይፈስ ዋስትና የለንም።

ትራንፕ ስለአባይ አስተያየት ሠጠ ብለህ ሰላማዊ ሰልፍ ትወጣህ የኢትዮጵያውያን ደም ሲፈስ ግን በዩቲዩብ የአዘን መግለጫ ትወጣለህ።ፍልፍስናህን ታወራለህ የአብይ መንግስት ደም አፍሳሽ ነው፣ ኦሮሞ ዲያስፖራው ጋር ታርቀህ የሚፈሱ ደሞችን አስቁሙልን ይህን ማድረግ ካልቻላችሁ በዩቲዩብ ለዶላር ስትሉ አታላዝኑብን።

የሚኒሊክና ዘውዲቱ አገዛዝ የተመቻቸው ነበር፣የልጅ እያሱም፣ የኃይለስላሴም፣የደርግም፣የህወሀትም፣የኃይለ ማርያምንም የተመቸው ነበር፣መደመር ብለፅግናዊው አብይ አህመድም የተመቸው አሉ።

በሁሉም ስርአት ደግሞ ግፍ የተሰራበት አለ። ስለዚህ አንተ የትኛው ላይ ነህ? ስለዚህ ሁልህም የራስህ የአመለካከትና የብሶት ጫካ ውስጥ ነህ። ልክ የምትሆነው ራስህን በሌላው ፋት ስቴፕ ስታይ ነው።የማንኛውም ስርአት ደጋፊ ብትሆን ደም አለብህ በዘርህ።በቃ ተውን በወንድሞቻችን የምታስገድሉን እናንተ ናችሁ።መፍትሄው እርቅ ነው ከዚህ ውጭ ማንም ብትነግስ ፔይን ኪለር ልትሆን ትችላለህ እንጂ መድሃኒት ልትሆን አትችልም።

ሁላችንም የያዝነውን የፖለቲካል አቋም ትተን ስለመሰረታዊ ችግሮች እንደማመጥ።አመለካከትህንማ እናትህ ፣አባትህ ፣ዘመድህ ጓደኛህ ሊወድልህ ይችላል።አመለካከትህ ለሁሉም ትረፍ ሊሆን ይገባዋለል፣ሁሉንም ካላዳናችሁ ስልጣን ምን ያደርግላችኋል።  ስለዚህ አሁን እየተፈፀመ ያለውን ግፍ ታግላችሁ አስቁሙና መሰረታዊ ችግሮቹን ፍቱልን።አገራችንን የደም መሬት ለማድረግ ጦርነት በትግራይ ህዝብ ላይ ታውጃለህ።ኢሳቶች በዚህ በኩል ተጠንቀቁ በድጋሜ አሜሪካና አውሮፓ አይደል የምትኖሩት ቢያንስ ከእኛ የተሻለ እየኖራችሁ ለምን ትሸጡን አላችሁ።

ሲሳይ አጌና፣መሳይ፣ግዛው ወዘተ የኢሳት የቀንም የማታም ጅቦች ጦርነት ማወጅ አቁሙ።

ከደም ወደ ደም ትግል ይብቃ ህወሃትን አሳምነህ ግዛ  አቶ አብይ አህመድ።

በህይወቴ እንደ እናንተ የጋዜጠኝነትም እውቀትና የሞያው ዲስፒሊን ባዶ የሆኑ ጋዜጠኞቹን አይቼ አላውቅም።ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የመንግስትም የግል ጋዜጠኞች ቢዋሹ የህይወት ዋስትና ስሌላቸው ነው፣ አንነተ ግን የሆድና የጥቅምህ ጉዳይይ ነው የሚሳስብህ።

አንዳርጋቸው ፅጌ፣ብርሃኑ ነጋ ትግል የጀመርከው ለራስህ ነው ከህወሃት ጋር የጥቅም ችግር ያለብህ ታጋይ ነህ።ችግርህ የኢትዮጵያወያን ችግር አልነበረም ቢሆንማ ትግልህ አሁንም ቀጥሎ ነበር።ችግራችን ሳይፈታ መደመር መደመር አትልም ነበር።

ለማንኛውም የቅንጅት አባላት 1997 ዓ.ም ለጠፉት ነፍሶች ተጠያቂዎቹ መንግስትና እናንተ ናችሁ።

ቅንጅቶች ችግሩን በልደቱ አያሌው አድረጋችሁ ራሳችሁን የኢትዮጵያ ጀግና ለማድረግ ሞከራችሁ። የልደቱን ሃሳብ ብትመርጡ ኖሮ አንድም ደም አይፈስም ነበር።ሃሳቡ ምንም ይሁን ምን ደም ከማፍሰስ ይሻል ነበር።ለማንኛውም በሰከነ መንፈስ ለእነዚህ ችግሮች ሁሉ ማን ጥፋተኛ እንደነበር መልስ ካልሰጣችሁን የግፋችሁን ሀውልት በሰው ጭንቅላት ውስጥ አለ።

አብዮት ካሰችን ጠይቁት ስለሀውልቱ።መደመር ሲመጣ ደስተኛ ነበር።ምክንቱም የእናቱን ገዳይ የተበቀለለለት፣የሌሎች እናቶች ሞት የቆመ መስሎት ነበር።አሁን ብሶ ባላበት ሁኔታ ህወሃት ላይ ጦርነት ታውጃለህ።የንፁሃን፣ እናትና ልጅ ደም ለማፍስ አዋጅ ታውጃለህ ።ስለዚህ እርቅ የምንፈልገው ከእናንተም ጭምር ነው።  አቶ የሺዋስ ወርዳችሁ ይቅርታ ካልጠየቃችሁን ያው ደም አፍሳሽ ናችሁ። አሁን አቅም ብናጣ የልጅ ልጅህ ከመጠየቅ ውደኋላ እንደማል እርግጠኛ ሁን። የእናንተም መቃብራችሁ ይቅርታ እያለ የሚጠይቅበት ዘመን እንደሚመጣ እርግጠኛ ሁን። በመቃብር እየተቃጠላችሁ ይቅርታ ከምትጠይቁን አሁን ሁላችሁም ይቅርታ ጠይቃችሁ ህዝብን የሚያገለግል መንግስት መስርቱልን።ህዝቡን የሚፈራ መሪና የሚያገለግል ተቋም መስርቱልን።

አብይ አህመድ ይችን አገር መላዕክት መጥቶ ያስተዳደረበት ግዜ የለም በማለት በማን እንደምትመራን  አሳውቀኸናል።ቅዱሳን መላእክት እንዳልመሩንና እንደማይመሩን እሱን ስትገረፍ ታወራዋልህ።የፅድቅ መንገስቱ ብዙ ነውና ሁላችንም ንስሀ እንግባ።

ምን ያህል የስልጣን ፍላጎት ቢኖራችሁ ነው።ደም እየፈሰሰሰ የግፍ ደም እየበላችሁ ዝም የምትሉት።ደመቀ መኮነን ፣ገዱ አንዳርጋቸው የአማር የብልፅግና አመራሮች፣ቫንፓየርስ ናችሁ።ቫንፓየርስ ያለ አይመስለኝም ነበር።

አብይ አህመድ፣ሽመልስ አብዲሳ ሁላችሁም የብልፅግና መንግስት አመራሮች እንኳን ነፍሳችሁ ስጋችሁም በመቃብር ውስጥ በቃጠሎ ይጮሃል። ሰው በላዎች ናችሁ፣ ልጆቻችሁ ደም አብረዋችሁ ሲበሉ ዝም ትላላችሁ።ኦነግን ያስገባኸው አንተነህ በስምምነት።ለምን ስምምነቱን አታከብርም። ለምን ደም አፍሳሽ ታደርገዋለኽ። አይ ይህ ሸኔ ነው አትበል።ሁሉምም የኦሮሞ ህዝብን ጥያቄ ነው የያዘው አንድም ሰው ቢሆን ደም መፍሰስ ማቆም ካልቻልክ ስልጣን ለምኔ በል።የውይይት መድረክ አመቻችና የወንበር ዙሪያ ትግል ጀምሩልን።ካልተመቸህ ውይይት የሰው ስጋና ደማችሁን እያፈሰሳችሁ እስከ መቼ። በቃ፣ በቃ፣ በቃችሁ።

Bloody Killers. ባይነገስ ቢቀርስ ።የኢትዮጵያ ህዝብ ይፍረድ።

የኢትዮጵያ ህዘብ ችግር እስከ ቀበሌ የወረደ ነው። ከላይ የአማራና የኦሮሞና ብሄር ለማመጣጠን የምትሉት ችግር በቀበሌና በሰፈር አለ።ለምሳሌ በብሄር አገዘዛዝ ውስጥ ያለውን ተፅኖ እንመልከት አዳማን ብንመለከት የስልጣን የበላይ ያላቸው እነማን ናቸው።አርሲ/አምቦ፣ወይስ ሌላ።የስልጣን ቦታህ አዳማ ሆኖ የአዳማን ኗሪ ምን ያህል አሳትፈሃል። ሁሉንም በዚህ መንገድ እዩት።

ትግራይም ውስጥ፣አማራም ውስጥ፣ደቡብ፣አፋር፣ቤኒሻንጉል ውስጥ፣፣፣፣፣ሁሉም ክልል ውስጥ ይህ ተፅኖ አለ። የሆነ ብሄር፣የሆነ አከባቢ ስልጣን ከወጣ እስከ ዘበኛ ሃላፊ የሚቀጥረው የአከባቢውን ሰው ነው።

ለምሳሌ የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳዳሪው ቦረና ከሆነ ደሴ በቦረናዎች ትጥለቀልቃለች።የዲሞግራፊ ሺፍት ይኖራል።የዩኒቨርስቲው አስተዳዳሪም ቦሬረክስ ይሆናል፣ ይሆናል እሱም እስከ ዘበኛ ና ካፌ ሰራተኞች በቦሬክስ ይከበበባል።

ማንንም የመውቀስ ሀሳብ ኖሮኝ አይደለም የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ራሳቸውን እንዲመረምሩ ነው።በብቃትህ ተወዳድረህ ስራ የምትይዝበት ሆኔታ አናሳሳ ነው በሁሉም ክልል ፖለቲካዊና ሰፈራዊ ሁኔታህ ይታያል። ለዚህ ነው ስራ በዘመድ ነው የሚባል።

የደቡብ ህዝቦች ለምን ይመስላችኃል ክልል መመስረት የሚፈልጉት ምክንያቱም የደቡብ መንግስት ሁሉንም የደቡብ ብሄር ብሄርረሰቦች መወከል ስላልቻለ ነው።እኩል የስልጣን ተዋፅዎ የለም።የሲዳማዎች የበላይነት ነበረበት። አሁን በመስተዳደሩ ማንነት ይወሰናል የበላነቱ ወይም እሱን በሚዘውረው ሃይል።

ስለዚህ በራሳቸው ለመመራት ክልል ለመመስረት መጠየቃቸው ትክክል ናቸው መሰረታዊ ችግሮች ካልተፈቱ።

ምንም እንኳን አሁን በአለንበት ሁኔታ ወላይታ ሆነው የሰፈር ፖለቲካ ለመገንባት እንደሚሯሯሙጡ ግልፅ ቢሆንም።

ለምሳሌ በአማራ ክልል ውስጥ የጎጃሜው ተፅኖ ከበዛ ጎንደሬው ክልል ለመሆን እንደሚጠይቅ አትዘንጋ።አገውን በደንብ መወከል ካልቻልክ አገው የሚል ብሄር መመስረት ነው የሚፈልጉት።ትግራይም ኢሮብን፣ኩናማን መወከል ካልቻልክ የራሳቸውን ክልል ለመመስረት ጥያቄ ያነሱብሃል።ወልቃይትም ችግሩ የመወከል ነው። ወይ ትግራይ አድርጋችሁ፣ወይ አማራ አድርጋችሁ ሳትይዙን የፖለቲካ ማቀጣጣያ ታደርጉን አላችሁ።

ስለዚህ የአገራችን ፖለቲካ አንተ በምታውቀው ዲግሪህን፣ማስተርህን፣ፒኤችዲህን በሰራህበት እውቀት ሳይሆን የሚፈታው የኢትዮጵያን ህዝብ ችግር በሁሉም ክልል ያሉትን ህዝብ በመጠየቅ ነው። ችግሩ ያለው ህዝብ ጋር ነው መፍትሄውው እንደዛ ነው።

ዌስተር መራሹ እውቀትህ እና ያነበብካቸው መፅሀፍ በማን እንደተፃፉ ማወቅ አለብህ ብየሃለሁ።ደም እየፈሰሰ ለእኔ አብይ አህመድን በእውቀት ብትተቸው ለእኔ ምንም ነው ደም መፍሰሱን ካላስቆምክልኝ።ስለፈሰሱ ደሞች ታገሉ ሁልግዜም ቢሆን።

ስለዚህ አሁንም በድጋሜ ዲያስፖራው አብይ አህመድ መከሰስ ካለበት ከሰሱልን በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት።ሊከሰስ ይገባወል።ወሬውን ተውትና አለም አቀፍ ንቅናቄ አድርጉልን።ደጋፊህን ተኮር ወሬ ተወና ዲያስፖራው አንድ ሁናችሁ የወገናችሁ ደም እየፈሰሰ ነው ታደጉን።

ሌላው የችግራችን ማሳያ ሀጫሉ ሁንዴሳ ሲገደል፣የተገደሉ አማራዎች ነበሩ።የኦሮሞ ተወላጅ ዲያስፖራው ሰልፍ እየወጣ ዳውን ዳውን ሲል አንተ ግን ስለተገደሉት አማራዎች መገደል ሰልፍ አልወጣህም።ይህን የምልህ የምትኖርበት ሀገር የመኖር ዋስትና ስለሰጠህ በግልፅ ብትታገሉልን መልካም ነው።የትግራይ ሀዘን፣የኦሮምያውያን ሀዘን ፣የደቡብ፣የአፋር፣የሶማሊ፣የሁሉም ብሄሮች ሀዘን ሀዘንህ ማድረግ መቻል አለብህ።በግለፅ የምልህ ሀጫሉ ሲገደል አብረህ ዳውን ዳውን ማለት ነበረብህ አብይ አህመደን ።ምክንያቱም ሁለቱም ሀጫሉም፣አማራውም የተገደሉት በአብይ አገዛዝ እንጂ በዲያስቦራው ኦሮሞ ወንድምህ አይደለም።

ጀነራሎቹ ሲገደሉ የማን ሀዘን ነበር የበረታው።እነ አምባቸው ሲገደሉ የማን ሀዘን ነው የበረታው።የአሳምነው ፅጌ ሞትስ ለማን ነበር ሀዘኑ፣የስመኘው ሀዘንስ፣የአጫሉ ሀዘንስ፣የአማራ ኦርቶዶክስውያን ሀዘንስ ለማን ነው ሀዘኑ የበረታበት፣የአማራ ህዝብ በቤኒሻንጉል፣በምዕራብ ወለጋ ሲገደሉ የማን ሀዘን ነው የበረታው፣ የኦርቶዶክስውያንስ ሀዘን ለማን ነው የበረታው ።ሁላችንም የራሳችን ሀዘን ነው የምናቀነቅነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ነን ትላላችሁ እንጂ ኢትዮጵዊ አይደላችሁም።ኢትዮጵያዊነትን እንዴት ነው የምትረዱት አስረዱኝ።

ለምሳሌ ዲሲ የሚኖር ነጭ አሜሪካዊ ሲያትል የሚኖር አንድ አሜሪካዊ ቢገድል አሜሪካዊ አሜሪካዊን ገደለ ነው። ብዙም ልዩነት በአመለካከት የለባቸውም።

ሌላው ላስ ቬጋስ የሚኖር ነጭ አሜካዊ ኒዮርክ የሚኖር ብላክ አሜሪካዊ ቢገድል ወደ ዘር ፖለቲካ ይሻገራል።ምክንያቱም የበዳይ ተበዳይ ታሪክ ስላላ። ጥቁሩ አሜሪካዊ እኮ ጥቁር አሜሪካውያንንም በድለዋል እሱ አያሳስባቸውም። ነጮቹም ነጬን በድሎታን።ስለዚህ ሰውን የምትበድለው የራስህ ማንነትና የግሩፕህ ማንነት እንጂ ከለርህና ብሄርህ አይደለም ችግሩ።

ለማለት የፈለኩት 100 ፐርሰንት እርግጠኛ ሁኜ የምነገርህ ዳግማዊ ሚኒሊክ አማራውን በድለውታል።ከእኔ ጋር አልበደሉም ብልህ በማንኛውም መንገድ መከራከር ትችላልህ ወዳጄ።

ስለዚህ አማራውን የበደሉ ኦሮሞን የማይበደሉበት መንገድ የለም። የኦሮሞን ብሄረሰብ እንደበደሉም እርግጠኛ ነኝ። የማላውቀው ግን ጡት መቁረጣቸውን ነው። ሲወራ ግን ሰምቻለሁ እንጂ አላውቅም፣ማረጋገጫም የለኝም።ነገር ግን በዚህም መንገድ ተበድለሁ የሚል ህዝብ ስላላ ልታሳምኑን ይገባል።

ሚኒሊክ ወንጌል ይዞ አይደለም ወደ ሌሎች ክልሎች የዘመተው ጠመኝጃ ይዞ ነው።አምነህ ከገበርክ ጥሩ ካላመንክ ግን በደም ነው አያቶቻችን ያስገበሩት። ስለዚህ በደም ያስገበረኝ እኔን በደሎኛል።

ምን ምንም እንኳን አሁንም የሚኒልክ አላማ የፃድቃን ነው ብትልም ያሳኩበት መንገድ በአንዳን ክልሎች በጠመንጃ ነው።ስለዚህ ችግራቸውንና ጥንካሬአቸውን መርምረህ ትክክለኛውን ክሬዲት ስጥ።ዝም ብለህ ጥቁር ሰው ብትል ለራስህ እንደዘፈንከው ቁጠረው።እስኪ ጉዞ አደዋ  አዘጋጆች ስንት ኦሮሞች  በጉዞው ተካተዋል።አድዋን እንደ አደዋ እንጂ እንደ ሚኒሊክ ማክበር የማይፈልጉ አሉ።መሰረታዊ ችግር ፍቱ አሁንም።

ሌላ ምሰሌ ልገራችሁ አብይ አህመድ እኮ የሸገር ፓርክ ጀግና ነው።ብዙ ሰዎች አድንቀውለታል።ኩላሊት የተበላበት ወገን፣እናቱና አባቱ፣ወንድምና እህቱ ደማቸው ለፈሰሰበት ዜጋ  ግን በሸገር ፓርክ አይመፃደቅም አብይን እያገነነ።ለሱ ምኑም ነው።

የአባይ ግድብ ምናቸው የማይመስላቸው ኢትዮጵውያን እንዳሉ ታወቃለሁ።ይህ እንዲገባህ ዩሃንስ መርድን፣ለኢሳት የደውለውን ምዕራብ ወለጋ ወላጆቹን ተለይቶ ጫካ ውስጥ ሆኖ የሚያለቅሰውን  አባይ ላንተ ምንህ ነው ነው በለው።ለአንተ ዳንኪራው ለሌላው ሀዘን ነው።

አባይንም የሁላችን አድርጉት ነው ጥያቀየ እንጂ ለአባይ አትታገሉ አይደለም ሃሳቤ።

አንዳንዴ ከኢትዮጵያውያን ችግር ይልቅ የዩቲዩብ ስቲከር ችግር ያሳስባችሃል።ይህ አስተሳሰብህ ስህተት ነው ካለችሁ እውነት አዘል የመፍትሄ ትግላችሁን አሳዩኝ።ልጨምርላችሁ አብዛኛዎቻችሁ የፖለቲካ ዩቲዩበሮች ገቢያችሁ የኢትዮጵያውያን ደም ነው።ስለዚህ በርገርህ የኢትዮጵያውን ደም ነው።ቢያንስ የፈሰሰው ደማችንን አውርተህ ልጅህን እያስተማርክ ነው።ችግር የለውም በርገርም መኪና

እንሁናችሁ ነገር ግን ለችግሮቻችን መፍትሄዎች ታገሉልን።ለዘላቂ መፍትሄ እባካችሁ።ምንሊክ ቲቪ ብለህ የምታቀርብልን ሀሳብ ለኢትዮጵያውን መፍትሄ መሆን አይችልም።መጀመሪያ አዌውን የሁላችንም አድርጉት።

ወዳጄ ነጭ ነጩን ስታወራ የራስህን ነጭ ብቻ አታውራ።የሁሉንም ነጭ አውራ።ከገባህ መፅሀፍ ቅዱስ ለሁሉም እውነቶች ምሳሌና መልስ ስላለው የአንተን እውነት በመፅሀፍ ቅዱስ ለማሳዬት ስለቻልክ የእኔን እውነት ብትክድ እኔም በመፅሀፍ ቅዱስ መልስ አለኝ ግልፅ ውይይት ማድረግ እንችላልን።

ስለዚህ ከቻልክ የሚሰሩትን አያውቁትም በልና የእኔንም ነጭ አውራ።ስለዚህ ኦነግ ጫካ ያስገባ በደል፣ወይም የበደል ጥያቄ ነበረበት ወይስ የለበትም።እሲኪ ይህን ጥያቄ ጥናት አድርገህ መልስልኝ።አንተ የለብህም ብትለው እኔ የምሰማው በደል አለብኝ ያለውን እንጂ በደል የለበትን ያለውን አይደለም።በሌላ መንገድ ደግሞ በኦነግና በስሞቹ የተሰሩ ብዙ በደሎችም መኖራቸውን አምናለሁ።ሁሉንም ጥናት ይደረግና ያስተሰርያል በል።

ህወሀትም ፣ብአዴን ፣ደህዴን፣ኦህዴን፣የሁሉም ክልሎች መንግስታት በድለዋል የአሁኑ ብልፅግናን ጨምሮ ።አብዱ ኢሌና አህመድ ሽዴ እኮ ያወ ናቸው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ሁሉም በድለውሃል።የሚሰሩትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው በሉ።

ሌላው የዩቲዩብ ቡራኬን ይመልከታል።ቅዱሳን አባቶች አስተያየታችሁ ማወቅ እፈልጋለሁ።የእግዝብሄር ሀይል በሁሉም መንገድ ይተላለፋል አወቃለሁ።ቡራኬንም በቴሌቪዝን መስጠት እንደምትችሉ አወቀለሁ።ማለትም ቅዳሴ ገብታችሁ ስትቀድሱ በቴሌቪዝን ብታስተላልፉልን ትክክል ነው ቅድስተ ማርያም፣ቅድሰት፣ስላሴ፣ ቦሌ መድሃኒ አለም ወዘተ መምጣት ላልቻልነው በረከት ነው **EOTCTV** and **EOTCMK** የሚያስተላልፉልን በረከት ነው።ፕሮግራሞቹም በሶሻል ሚዲያ ቢለቀቅ ትክክል ነው።

አሁንም ማለት የፈለኩት መምህር ምህረት አብ አሰፋና መምህር አስቻለው ከበደ የማንቂ ደውል ፕሮግራማችሁ ላይ እናንተ ቡራኬ መስጠት ስለማትችሉ ደውላችሁ በስልክ ቡራኬ ማሰጠት ብትሞክሩ አላማችሁ ምንድን ነው።ነገር ግን መንፈስቅዱስ በሁሉም መንገድ እንዳለ አምናለሁ።

ቀሲስ መምህር ዶክተር ዘበነ ቡራኬ ለአስተማራቸው ቢሠጥ ለእኔ ችግር የለውም ።ከዚህ ውጭ ግን አስተምሩኝ።

ሌላው ሀሳቤ ደግሞ እሺ አስደውለህ ቡራኬ አሰጥ ቤተክርስትያን በሌለበት አለም  የሚኖሩ ብዙ ምእመናን አሉ።ነገር ግን ፕሮገራምህ ይወሰወነዋል።የአንተ ፕሮግራም ሀይማኖቶፖለቲኮ ይባልል።ፖለቲካውን ስታስተምር ሴረኛ ነህ።አንተ ጥሩ ኢትዮጵያዊ እንደሆንክ አውቃለሁ። ፖለቲካ ስታወራ በመንፈስ ቅዱስ ማሽነፍን ረስተህ በሴራ ማሽነፍን ታስተምራለህ።ስለዚህ የሚባርክህ/ቡራኬ የሚሰጥልህ አባት ጋር መንፈስ ቅድሱ ቢኖርም እንኳን ወደአንተ በስልክ ተላልፍ ተመልካቾችህን አይባርክልህም።

ስለዚህ የማንቂያ ደውል አዘጋጆች ሲፈልጉ አባት ጋብዘው፣ሲፈልጉ በስልክ ቢያስባርኳችሁ ጉባያቸው የመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።ሁሉንም በመንፈስ ቅዱስ አይን ነው የሚያዩት።ስለዚህ የዩቲዩብ ምዕመናን ቡራኬ የምትውስዱበትን ቢንስ እወቁ።

ዛሬ 25/02/2013 ዓ.ም ደግሞ ሌላ አስደንጋጭ ዜና ንጉስ አብይ አህመድ ጦርነት አወጁ።የእኔ ጥያቄ ለምን ኦነግ ሸኔ ላይ ጦርነት አላወጀም ነው? ኢትዮጵያን ሆይ አሁንም ድብቅ ፍላጎት እንጂ ፍትህ እንዳልሆነ ሊገባችሁ ይገባል።ንጉሱ አጋጣሚ ነበር የሚፈልጉት የአማራውያን ደም ያፈሰሱትን ፍትህ ሳይሰጡ ህወሀት ላይ ጦርነት ማወጅ ምን ይባላል።

አዋጁን ሲያውጁ የተናገረው የክተት አዋጅ ጥሪ የሚያስፈልገው ለሱ ነበር።አገር የከዳውም እሱ፣ጡት የነከሰውም እሱ፣እንደመርም ማለት መብታቸው ነው።ለምን ጦርነት ታድያ።

በትግራይ ህዝብ ላይ የመከላከያ ሰራዊቱ የቀድሞ የአሸናፊነቱን ድል እንዲደግም አወጁ።ወንድምህን እንድታሸንፍ ጥሪ ሲቀርብልህ ያጨበጨብክ ሌላ ሀውልት አስገንብተሃል።የሚኒልክም ችግር ይህ ነበር። የኦሮሞ ህዝብ፣የወላይታ ህዝብ አንገዛም ለአንተ ሲሉት ጠመንጃ የተመዘዘበት።በእርስ በእርስ ጦርነት የመጣች የደም ኢትዮጵያዊነትን መሰረቱ።አኬልዳማ ነው ስልጣንህ አባ።

ስለዚህ በጦርነት የሚመጣ ድል ሁሉ ማንም ያሸንፍ ማን ያው የደም ውጤት ነው።በመላው አለም  ያላችሁ ኢትዮጵያውያን አላስፈላጊ ደም ማፍሰስና የደም ፖለቲካ እንዲያበቃ ንቅናቄአችሁን እባካችሁ ጀምሩ።

የኢትዮጵያያ መከላከያ ሰራዊት ሆይ ወንድምህን ገለህ ጀግና ተብለህ ሲጨፈርልህ ተመልከት።አገሩን የከዳው ወደ ጦርነት የከተተህ ሃይል ነው።ይህ ዘመን አልፎ ሌላ ሲመጣ ያው አገሩን የከዳ ባንዳ ነህ።

በኢትዮጵዮ -ኤርትራ ጦርነት የተዋጋችሁ ንጉሶቹ ሲታረቁ ምን አላችሁ።መልሱን ለእናንተ።

አሁንም የኢትዮጵያ አርቲስት አሸው አንበሳው ቁጥር 2 ሊሰራ ነው።ለበጎ ከሆነ ለቁም ነገር ጉዳይ ሊባል ነው።አመመኝ በጣም፣ ኢትዮጵያ ሊዘፈን ነው ኢትዮጵያ ታማ ፣ ኢትዮጵያን፣ኢትዮጵያውያን ለመሰዋት እያዘጋጁ።

ከነጮቹ 8 አመት አይመስለኝም ልዩነታችን የስምንት አመት ልዩነት ይህን ያህል የአመለካከት ልዩነት አያመጣም።

ጦርነት መቼ ለምን፣እንዴት ተጀመረ የሚለውን አጥኑት።የጋርዮሽ አስተሳሰብ ነው፣ከአንተ ውጭ በከለርም፣ በባህልም፣በአስተሳሰብም ከአንተ የተለየውን አውሬ መስሎህ የምታጠፋበት ነው።

በአሁኑ ዘመን በሃሳብ ማሸነፍ ሲያቅታቸው ጦርነት የሚያውጁ አብዛናዎቹ አፍሪካውያን ናቸው።ለምን ይመስላችኋል።መልሱን ለእናንተ እኔ መልስ መስጠት አይደለም አላማየ።

በዚህ የክተት አዋጅ በጣም የተደሰቱት ሁለቱ የኢሳት ጅቦች ሲሳይ አጌና፣መሳይ አጌና ናቸው። ህወሃት እንዴት አድርጋ ብትገርፋችሁ ነው ይህ ሁሉ አላስፈላጊ ጥላቻ።ተበድላችሁ ሊሆን ይችላል ግን እየታገላችኋቸው ያላችሁት ከሰይጣን ጋር በመሆን ነው። መደመር ቅዱስ መንፈሳዊ ቢሆን በሃሳብ አሸንፎአቸው ለፍርድ በሃቅ ያቀርቧቸው ነበር። እንዴት ላስረዳችሁ አጌናዎች አዎ ሁላችንም ተበድለናል  በደም የሚመጣ ፍትህ  ያው ደም አለበት ነው የምላችሁ።

ወይም ወደ ብሉይ ህግጋት እንግባና eye for an eye ተግብሩ። ይህ ማለት በትክክል አይንህን ያጠፋብህን ፈልገህ አይኑን አጥፋ።ከዚህ ውጭ በጦርነት የሚጎዱት እነማን እንደሆኑ እወቅ።

ኢሳት አጌናዎች ዛሬ ጫጉላችሁ ነው።ጦርነት ታወጀልህ ትንቢተኛ እንደሆንክም ተሰምቶሃል።እርግጠኛ ሁኚ ልንገርህ የምትበሉት በርገር ካቻ አቹ የሰው ደም ነው። እስከስንተኛ ክፍል ነው የተማራችሁት ተውት በመማር አይደለም ለካ።

ምን እንደሚሰማኝ ታውቃላችሁ እናንተን ከማይ በጣልያን ብገዛ ይሻለኝ ነበር።ለውጭ አልጋ ለቤት ቀጋ ከሆነ መሪየ።

እያልኩህ ያለሁት ገብቶሃል ወንድሜ ጋር እየተዋጋሁ ደሙን ከማፈስ ጣልያንን እድሜ ልኬን እየተዋጋሁ መኖርን  እመርጣለሁ። የአደዋን ድል ከንቱ ያደረጋችሁ ናችሁ።በመደመር የአዲስ አበባ ህዝብ ምን አገኘ፣የአማራውስ፣የኦሮሞውስ፣የደቡብስ ወዘተ።ያልገባህ ለሌላው ክልል አብይ  አህመድ ጥሩ ነገር አድረጎ ቢሆን የትግራይ ህዝብ ራሱ ህወሀትን ይታገለው ነበር።

አባካችሁ የደም ታሪክ አትፃፉ።አልገባህም እንጂ ጥቁር አሜሪካዊ ከአፍሪካ አገራቸው ይልቅ በአሜሪካ የተሻለ ክብር አላቸው የእነሱ ዘመዶች ግን በአፍሪካዊ፣ በአባገነኞች ነው የሚገዙት።

ሌላው ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ኢትዮጵያዊ ጣልያን ውስጥ ያለ ኢትዮጵያዊ የተሻለ ዲሞክራሲዊ መብት አለው።ወደ መነሻችን ሁላችንም ብንመለስ ያው የአዳም ነን።የአጊናዎች የለም። ገብቶሃል የምልህ።ጣልያንም በጦርነት ከሆነ ያው ነው፣ግን ሊወርህ ስለመጣ በመጣበት ትታገለው አለህ።መደመርም እንደዛው።የትግራይ ህዝብ ህወሃት ነኝ እያለህ አንተ ምን አገባህ።አንተ ስለኔ ምን የተሻለ ሀሳብ አለህ።ነው የቂም በቀል ፖለቲካ ነው።

My Friend you are burger Minded politicians.You got bloody burger enjoy. My blood is your burger.

ህወሃት ላይ ጦርነት ማወጅ ያለብህ መቼ እንደሆነ ታውቃለህ? የትግራይ ህዝብ አቅቶት ምን አልባት እርዳኝ ካለህ ነው።

ከዚህ ውጭ አብይ ስልጣን ከያዝክ በኋላ ለተሰሩት ወንጀሎች ህወሃት እጁ አለበት ካልክ በመረጃ አቅርበህ ለፍርድ ማቅረብ ትችላለህ።ከዚህ ውጭ ኮሽ ባለ ቁጥር ካለማስረጃ መወንጀል አትችልም።

የኢሳት የቦርድ አባለት ትግላችሁን ስታደርጉ የነበረው በህዝብ እርዳታ ነበር። እንዴት አሁን ህዝቡን ትክዱት አላችሁ።

ቆማችሁ እራሳችሁን ፈትሹ ሰላማዊ መፍትሄ ፈልጉ።የሰላም ሚኒስተር አላማው ምንድን ነው።

በድጋሜ በመላው አለም ያላችሁ ዲያስፖራ ኢትዮጵያወያን ለአገራችን ሰላማዊ መፍትሄ ፈልጉልን።ሁላችሁም በትግራይ ክልል የታወጀውን የጦርነት አዋጅን አውግዙ።

በትግራይ ህዝብ ላይ ጦርነት አውጆ ሲጨርስ ፊጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ ከሚል መሪ ይጠብቀን፡፡ሃሳቤን እንዴት እንደምገልፅለችሁ በጣም ነው የተቸገርኩት፡፡ ሲያወራ ሊጥል ያሰበው እንቁላል ይታይል፡፡

አሁንም ደግሜ ልንገራችሁ ከገነት ከተባረርን ጀምሮ አዳምና ሄዋን መኖር የጀመሩት በራሳቸው ፈቃድ ነው፡፡ሱባኤ ገብተውም ሰይጣን እኔ ቅዱስ ሚካኤል ነኝ ብሎ ሱባኤአቸውን እንዲያቋርጡ አድረጓቸዋል፡፡

በመጨረሻም የረዳቸው እግዚያብሄር ነው፡፡ ቅዱስ ገብርኤልን በመላክ፡፡ቅዱስ ገብርኤልም ከገነት የሚበላውን ምግብ በገነት ውስጥ በሚኖሩ እንስሳት፣አእዋፊት አምጥቶ አጠራቅሞለታል፡፡ማለትም እግዚያብሄር ቸርነቱን ሰጥቶናል፡፡ስለዚህ እንኳን ጦርነት ማወጅና ከእግዚያብሄር ፍቃድ ውጭ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ምግብ ብናደርግ ሀጥያት ነው፡፡ስለዚህ ጦርነት አውጇችሁ ያልተፈቀደላችሁን ደም አትብሉ አስናቀዎችና ተደማሪ አጌናዎች፡፡

ከአዳም ጀምራችሁ የመንግስት አመሰራረት አላማዎችን ተመልከቱ፡፡የመጀመሪያውን ጠንካራ አምላካዊ ስልጣን የተመ|ኙት አዳምና ሄዋን ናቸው፡፡እግዝብሄር የሰጣቸውን ሳያወቁ አምላክ መሆንን ተመኙ፡፡

ስለዚህ የንግስና መነሻው ከአዳም ይጀምራል ማለት ነው? ስለዚህ መንግስ መሆን የምትፈልጉ/የነገሳችሁ ንግስናችሁ ከየት ነው? ምክንያቱም እግዝብሄር አዳምን አንግሶት ንጉስ መሆኑን ሳያውቅ በሰይጣን ለመንገስ ፈለገ፡፡

ከማን እንደሆንክ ለማወቅ የተፈፀሙት ግፎች ይናገራሉ፡፡ አጌናዎች ምን አሉ መሰላችሁ? በትግራይ ህዝብ ጦርነት የታወጀው የትግራይ ህዝቦችን ለማሻገር ነው አሉ፡፡ ፈርኦኖቹ እነማን ናቸው ነው የእኔ ጥያቄ፡፡ስለዚህ እግዚያብሄራዊ የሆኑ ንጉሶችን ተመልከቱ ህዝባቸውን እንዴት እንዳሻገሩ፡፡ ቅዱስ ሆነው በእጃቸው ደም ያፈሰሱ አሉ፡፡ ማለትም ከራሳቸው ውጭ የሆነ ህዝብ ጋር ሲዋጉ፡፡እርስ በርእስ ግን አላውቅም ፡፡የራሱን ወታደር ንጉስ ዳዊት አስገድሏል፡፡ግን በንሰሃ ተመልሷዋል፡፡ሳኦልም ጋር ጦርነት ነበረበት ነገር ግን ማን ነው ዳዊት፣ማን ነው ሳኦል አሁን?

ስለዚህ በዚህ ጦርነት መከላከያው ወንድማቸውን ሊዋጉ ነው የሚሄዱት፡፡ሌላው ብሄር ቢጨክን የትግራይ ልጆች የሚጨክኑ አይመስለኝም፡፡መርጦ ያሰልፍ እንደሆነ አላውቅም ፡፡ምክንያቱም እናቱና አባቱ ላይ ጦርነት ማወጅ ንቀት ነው፡፡

በአጠቃላይ ለማለት የፈለኩት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ መንግስታትን በእውነትና በሃቅ ብትመረምሯቸው ማንነታቸው ግልፅ ነው።የሆነ ወገንን ስለጠቀሙ የሚከራከርላቸው ብዙ ነው።ለማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ ስልጣን የሰጠው መሪ እኔ አላውቅም።

ዲሞክራስዊ ምርጫ አካሂዳለሁ ብለህ ብዙ ግዜ ለፍልፈሃል እንደማታካሂድ ማረጋገጫወ የመጣህበት የ 2 አመት የአገዛዝ ስረአትና ፍላጎትህ ያሳያል።አንተ የምትፈልገው ንጉስ ሆይ ሺ አመት ይንገሱን ነው።

ለማንኛውም ከእግዝያብሄር ስላልሆንክ የሀሰተኛው መሲህ ተምሳሌት ነህ። ሀሰተኛው መሲህ እኮ ሲመጣ ምን እንደሚል ታውቀለህ መደመርና መደመር ብቻ ነው እኔ ነን አምላካችሁ ነው የሚለን።ብልጽግና ነው የሚያዋጣችሁው ነው የሚለው።ሁሉም ለእሱ እንዲሰግዱና የመደመርን አርማ እንዲነቀሱ ይፈልጋል።የተቃወሙትን መንገድ ይዘጋል፣ኢኮኖሚክ ሰንክሽን ያደርጋል፣በጀት ይከለክላል፣ጦርነትም ያውጃል።ሀሰተኛ ነብያቶቹ እንደ አጌናዎች አይነቶቹ ጮቢ ይረግጣሉ።ዳንኤል ክብረት ምን ብሎ ይሆን?

የትግራይ ህዝብ ሆይ እግዝያብሄር ሄኖክና ኤልስን ይላክላችሁ።

የሰገደው ማን ነው እንጂ፣ ሀጥያትን የሚመረምር ሀያሉ እግዝያብሄር እርሱ ነው።

ሌላወ ንጉስ አብይ ኦርቶዶክስ ሀይማኖት ብልፅግናንና ገንዘብ ማፍራትን ለምን እንደምትጠየፍ ታውቀለህ? ብልፅግናህ የምን፣የማን ነው የሚል ጥያቄ ስላላት እንጂ የአለም የብልፅግና መሰረቱም መድሃኒ አለም ክርስቶስ መሆኑን አትርሳ። ከዚህ ውጭ የቄሳርን ለቄሳር ነው።

የሚስጥራዊ ቡድን እምነቶች፣ጌን አስፋፍተሀላቸውና የመሳሰሉትን ሀጥያት ሰርተህ የምታመጣውን ብልፅግና ለራስህ፣ አትቀበልህም።

ብልጽግናም ከእግዝያብሄር ሲሰጥ እንጂ ከዚህ ውጭ የሉሲፈር ነው።ሁልህም ለገንዘብ እድትሰግድ የሆንከው ገንዘብ የሰይጣን ስለሆነ ነው። በአለም ላይ ያሉ ገንዘቦችን መርምሩ፣ ድብቅ ሚስጥሮችን ለማወቅ ሞክሩ።ለማን እንደተሰሩ ይገባችኋል።የገንዘብ አምላኮች የሚባሉ እርኩስ መንፈሶችም አሉ። ብልፅግና በነሱ ከመጣ አሁንም ኦርቶዶክስ አትፈልገውም።

ቅዱስ እግዝያብሄር እውነተኞቹን ሄኖክና ኤልያስን ለኢትዮጵያ ህዝብ ይላክልን ከመደመር ፖለቲካ ይገላግለን!!

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ አንተም ስላለተደመርክ ጦርነት እንደሚከፈትብህ እወቅ።ለምሳሌ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ህዝቦች በተደመሩና ባልተደመሩ መካከል ጦርነት አለ።ታክቲካል ጦርነት።

ደቡብ፣አማራም፣ኦሮምያም፣ሁላችሁም ክልሎች ባትደመሩ ግዜውን ጠብቆ ጦርነት ይታወጅባችሁ ነበር።ጦርነት ደግሞ ለማወጅ ምክንያት ይፈጠርብሃል።

ሌላው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአወጁት ምን ነበር? ግልፅ ጦርነት ነበር። እንደገና ሬዲዋን ሁሴን ግጭት ነው አለ ማለት ቀልድ ነው።ግጭት ነው  የነበረው ነገር ግን  በጦርነት ለመፍታት መንግስት አውጇል።በጦርነት መከላከልም ስልታዊ ማጥቃት ነው፣ ጦርነት ነው።ከ ሁለት አመት በፊት ነው፣ በህወሀትና መደመር ግጭት የተፈጠረው በመጨረሻም ግጭቱን መንግስትበጦርነት ለመፍታት ወስኗል እውነቱን ይህ ነው።

ኢትዮጵያዊ ባልና ሚስቶች የከረረ ፀብ ተጣልተው ጎረቤት ሲመጣባቸው ትንሽ ግጭት ነው የሚሉት፣ የሬዲዋን ሁሴንንም በዚሁ እዩት 360 ዎች። ትላንት ስትቃወመው የነበረውን ሬዲዋን ሁሴን ያስመሰገነህን ዛሬ ምንደን ነው? መርምር ስሜትህን።

ለማንኛውም ሀብታሙ አያሌው በየትኛውም አለም ብትሄድ ለጦርነት አሳማኝ ምክንያት የለም።ደም ለማፍሰስ አሳማኝ ምክንያት የለም።ተገደህ የምትጀምረው ጦርነት ሊኖር ይችላል። ህወሃት ምን ያህል መደመርን ለጦርነት ገፍቶታል የሚል መልስ እፈልጋለሁ።ቢገፋውም ጦርነት መልስ አይሆንም።

አብይ አህመድ መግደል መሸነፍ ነው ብሎ አውጆ ነበር።ስለዚህ ሚኒስትሩ ከተሸነፈ ቆይቷል።ስለዚህ 360 ዎቹ በማንኛውም መንገድ መስበክ ያለብህ እርቅና ሰላም እንጂ ጦርነታዊ ትንተና አትስጥ።

የኤርምስ ለገሰን ጥያቄ ጥሩ ነው? የጦርነቱ አላማው ምንድን ነው? መሰረታዊ አላማው ምንድን ነው? ኤርሚ የብልፅግና ወንጌልን በትግራይ ለማስፋፋት እንጂ ሌላ አላማ የለውም።ፍትህ ሰጭ ሓይሎች ቢሆኑ በምእራብ ወለጋ ደም ባፈሰሱ ሃይሎች ላይ እርምጃ ለመወሰድ ኦፕሬሽን ያስፈልግ ነበር።

ስለዚህ ሀብትሽ የትግራይን ህዝብ አትሸውዱት የትግራይ ህዝብና ህወሃት አንድ አለመሆናቸውን ትንሽ እንደ ኤርሚያስ ስታቲክስ ስራ፣ዝም ብለህ የትግራይ ህዝብ ጀኒውን ነው አትበል።ደላላ።እየደለልክ ህዝባችን አትውጋ።Just be evidence based journalist.

ጎበዝ ጋዜጠኛ ከሆንክ የሁለቱንም እውነት ተንትነህ አሳይ።የእግርኳስ ኮሜንታተር ታውቃለሁ 90 ደቂቃውን ጨዋታውን ነው የሚያሳዩህ፣በመሃል የራስህ ሀሳብ ጣል፣ከዛ ወደ እወነቱ፣ እንዲገባህ እግር ኳስ በሬዲዮ ተመልከቱ፣ መሰለ መንግሰቱን ጠይቀው።

አርሴናልክ ሲቲ ሲጫወት የአንዱ ደጋፊ ብቻ፣በከፊል ደጋፊም ከሆንክ ጨዋታውን ለህዝብ መዘገብ አትችልም።አይደል እንዴ

አርቢትር።ስለዚህ ፖለቲካል ኮሜንታተር ሁን ከቻልክ። ካልቻልክ ነዳጅ ብትቀዳ ይሻልሃል።

ከሆነ ጥግ ውጣ።የፕሮግራማችሁ ርዕስ ለምን 360 ሆነ? መልሳችሁ ኢትዮጵያን በሁሉም ኳድራንት ማለት ነው።ተረድተኸኛል። በዚህም መሰረት አንድን ችግር በ 360 መንገዶች እየተነተኛችሁ አሳዩን እንጂ። በ ኢትዮ 360 ያሉ ችግሮችን በራስህ መንገድ አታሳየኝ። እስኪ ከህወሃት ደጋፊ የሆነ ሙህራን ጋብዛችሁ ተከራክራችሁ ታውቃለቻሁ።የኦነግ ደጋፊን ጋብዛችሁ ቻሌንጅ አድርጋችሁ ታውቃላችሁ።14 ሺ ሰው እየተከታተለን ነው ብለህ ብቻ አውራ።sticker minded.pin pole minded.እና ከ 110 ሚሊዮን በላይ ነን።ሁሉም ነገር ከእግዝያብሄር ሊሰጥህ ይገባል፣ከዚህ ውጭ ኑሮህን ለማሸነፍ የተሰማራህበትን ስራህን ነው እየሰራህ ያለኸው።

ብሩክ ይባስ ያለው የጦርነት አቋም ሊኖርህ ይገባል።ማውገዝ፣ማውገዝ፣ማውገዝ አለቀ። ትንታኔህን ከህወሀትም፣ከመደመርም አንፃር ማየት ቻሉ።ሌላወ አስተያየቴ እስካሁን ሪፎርም በመከላከያ በራሱ መንገድ ንጉሱ ሲሰራ ያልጠራቸውን የቀድሞ መከላከያዎች ደም ለማፍሰስ ሲጠራቸው አታድንቅ። ከግብፅ ጋር አይደለም ግጭቱ/ጦርነቱ።

ችግር አለብህ እኮ፣ ኦነግ ሸኔ ላይ አብይ ጦርነት ቢያወጅ ታደንቃለህ? እያልኩህ ያለሁት በማንኛወም መንገድ ጦርነት አይመከርም።መመለስ ያለብህ ለምን ጃል መሮ ጫካ ገባ ነው? ስለዚህ ማን፣እንዴት፣እንደሆነ ባላውቅም ጃል መሮ፣ የሆነ ነገሩ ተሰርቆበታል፣ተቀምቷል፣ተዘርፏል። በሰላም የሚመልስለት አጣ ጦርነትን መረጠ።ጦርነትን የመረጠ አካል ደግሞ በማንኛው ግዜ ምን

ሊያፈነዳ እንደሚችል አታውቅም።ስለዚህ የጃል መሮ ሀጥያት የእሱም፣ ጥያቄውን ያልመለሰለትም አካል ነው።ስለዚህ ሰላማዊ ድርድር ነው መፍትሄው።

ግልፅ እንዲሆንላችሁ በህወሀት አገዛዝ ግንቦት 7 ጫካ ገብታችሁ ነበር።ጦርነቱን ብትቀጥሉበት ብዙ ሀጥያት ልትሰሩ ትችላላችሁ።ሰው ልታገቱ ትችላላችሁ። ብር ለመጠየቅ ምክንያቱም ሰርቫይቫል መካኒዝም ነው።ሌላው በመንግስት ላይ ጫና ለመፍጠር፣ፍንዳታና ግድያ ልትፈፅሙ ትችላላችሁ።ምክንያቱም አማራጭ አጥታችሁ ጦርነትን መርጣችኃል።የደም ማፍሰሱን መንገድ።

ለምሳሌ አንዳርጋቸው ፅጌንና ብርሀኑ ነጋን መንግስት ቢማርክባችሁና ቢያስርባችሁ ጫካ ሁናችሁ እነሱን ለማስፈታት ምን ታደርጋላችሁ።

ብዙ መንገድ ልትፈጥሩ ትችላላችሁ፣ከነዚህም ውስጥ መደራደር፣ንፁሃን ዜጎችን ማገትና አግታችሁ በንፁሀን ነፍስ ማስፈራራት ለውጥ ሁሉ እስከመጠየቅ ልትሄዱ ትችላላችሁ።አሉ የሚባሉትን መንገዶች ሁሉ ትሞክራላችሁ።በዚህ ሂደት ጦርነቱን ለማሸነፍና የእናንተን ሰዎች ለማስፈታት የምታፈሱት የንፅሀን  ደም ሊኖር ይችላል።ይህ የስራው ባህሪ ነው።

ሌላወ በጦርነት ውስጥ የህዝብ ነፍስ አጥፍተህ፣ፍንዳታ አስነስተህ በምትዋጋው ልታሳብብ ትችላለህ። ምክንያቱም የህዝብን ድጋፍ ለማግኘት።ምንም እንኳን የውጊያ ዲስፕሊን የሚባል ቢኖርም። የሰይጣንን መንገድ መርጠህ ዲሲፕሊን የሚባል ቀልድ ነው።በአጠቃላይ ምርጫው ስህተት ነው።

ስለዚህ ጦርነት የሴራ ጨዋታ ነው።ፍትህ ሊያመጣ አይችልም።

ሂሮሽማና ናጋሳኪን ተመልከቱ ችግሩ እስከአሁን አለ።እኛ ኢትዮጵያውን መሳርያው ቢኖረን በወንድሞቻችን ላይ እስከዛሬ ባደረግነው ጦርነት ተጠቅመነው ነበር።

አንተ ጦርነት አሁን ስታውጅ በደርግ ዘመን በተደረጉ ጦርነቶች፣በኢትዮ - ኤርትርያ በተደረጉ ጦርነቶች  ቁስላችን ያልዳነልን ኢትዮጵያውን አለን።

በአጠቃላይ አጌናዎች እያልኳችሁ ያለሁት ለምን ጦርነት ገባችሁ ነው ከግንቦት 7 ጋር ምክንቱም ጥያቄአችሁን በሰላማዊ መንገድ የሚመልስላችሁ ሀይል ስላጣችሁ። ስለዚህ በጦርነት ለሚፈሱ ደሞች ተጠያቂው ሁለቱም ወገን ስለሆነ በአገራችን ሰላማዊ የመድረክ ውይይት፣በሀሳብ ትግል ማሸነፍ የሚኖርበትን መንገድ ለማመቻቸት ታገሉ።ጁሃርና ታማኝ በየነ ሳይታረቁ ኦሮ-አማራ የለም።

ጃል መሮና ሚኒሊክ ሳይታረቁ ኦሮ-አማራ የለም ከገባህ።

በድጋሜ በአጠቃላይ ኦሮሞ ሆነው የኢትዮጵያንና የአማራውን ልብ ያሸነፉ ጀግኖች አሉ።አማራ ሆኖ ግን የኦሮሞን ልብ ያሸነፈ ጀግና ስም ጥራልኝ። ለምን እንደዚህ ሆነ? መልስ እፈልጋለሁ ሙህራን።ለሌሎችም ብሄር ጥናት አድርጉበት።

የኢትዮጵያ አማራው ህዝብ ሆይ መሪዎችህ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ያለህን ችግር ሳይፈቱልህ።ከትግራይ ህዝብ ጋር ሌላ የስህተት ታሪክ ሊያሰሩህ ስለሆነ ጥላቻው ስር ሳይሰድ ንቃ።ቁምጣህን ለብሰህ ና ቁመህ ጠብቀኝህን ይዘህ  አትፎክር፣ የበላይ ነኝ እያልክ አትፎክር።የጀግናው በላይ ዘለቀን ታሪክ አታበላሽ።እሱ ጣልያንን የተዋጋ ጀግና እንጂ እንዳተ ህወሃት  ወንድሙ ላይ የፎከረ አይደለም።በልጁም አልተደራደረም።ለስልጣን ብሎም ወገኑን አሳልፎ አልሰጠም። ወልቃይትን ከማን ነው ፣ነፃ የምታወጣው።ጎጃምም የትግራውያን መሆኑን አስብ እንጂ።መብቱን በሰላም ፍታለት።ስለዚህ አንተ በላይ ዘለቀ ሳትሆን ስምህ ማን ነበር ንገረኝ። ቁምጣና እጀ ጠባቡን ለብሰው አባቶቻችን የፎከሩት ከሮም ለመጣው ወራሪ ነው።ዝም ብለህ አታናፋ።በግድ ጦርነት ከወንድምህ ቢነሳብህ እያዘንክ እንኳን መሆን አለበት መልስህ።ነጋሪት ለማን እንደሚጎስም የማታውቅ የሰፈር ወንበዴ ነህ።

ሌላው የቀድሞ መከላከያ ሰራዊት አባል ሁናችሁ በመደመር ንጉስ ከለላ ያገኛችሁ አፋችሁን ባትከፍቱ ጥሩ ነው።መንግስቱ ሃይለ ማርያምን የከዳህ ነህ።ከዚህ በኋላ ቂም በቀል ካልሆነ አላማህ ምንድን ነወ? የሌሎቹን ጀግኖች ክብር አትንካ እነሱ የታገሉት፣መንጌ የታገለው፣

- ኢትዮጵያ ትቅደም ብሎ ነው
- ኤርትራን አላስገነጥልም ብሎ ነወ፣መቃብሬ ኤርትራ ላይ ነው ብሎ ነው
- ትግራይን ኣላስገነጥልም ብሎ ነው

- ኦሮሚያን አላስገነጥልም ብሎ ነው
- እናት አገር ኢትዮጵያ ወይም ሞት ብሎ ነው።ወዘተ

ስለዚህ መሰዋት የሆናችሁለት ነገር የለም፣ ለምን ብላችሁ ነው የምትደመሩት?

በግፍ ያፈሰሰችሁት ደም የተረሳ መስሏችሁ እንደ ጀግና  አፋችሁን የምትከፍቱ የሰራዊቱ አባለት ተጠንቀቁ።

እንደ መንጌና መሰሎቹ ዝም በሉ።ደማቸውን የአፈሰስከብ ቤተሰቦቻቸው በህይወት መኖራችንን አትርሳ።

ሌላው ማፈሪያ ህወሐት በኢትዮጵያ አንደንት ላይ የደቀነው አደጋ ብለህ ትወያያለህኸ። ኢትዮጵያ አንደነት ስምህ ነው እንዴ።ነው የልጅህ ስም፣ስለየቱ አንድነት ነው የምታወራው፣

ኢትዮጵያኖች እንኳን እንደ ኢትዮጵያውያን እንደ አማራው አንድ መሆን አቅቶናል።እንኳን እንደ አማራው እንደ ጎጃሜነት አንድ መሆን አቅቶናል።እንደ ኦሮሞ አንደ መሆን አቅቶናል።

ስለዚህ የአንድነታችን ችግር ህወሀት አይደለም።የአንድነታችን ችግር ሌላ ነው ጥናት አድርጉበት ምኒልክ አውደ ሃሳባውን።

ከገባህ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ችግር ያመጣብን ፕሮግራምህ ነው፣ ችግራችን አንተ ነህ።እንኳን ምኒሊክ አወደ ሃሳብ ብለህና ምኒሊክ ቲቪ ብለህ ብትመጣ ሃሰብህን ማን እንደሚገዛህ ይታወቃል። ስለዚህ በናንተ ጓዳ ኢትዮጵያ የለችም።እስኪ ለአንተ ምኒልክ ምንህ ነው።በግል ምንህም አይደለም።የምኒልክ ፅድቁም ኩነኔውም የጋራ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው።የአድዋ ድል የኢትዮጵውያን እንጂ የግልህ አይደለም።የግልህ ይመስል ማን ተከራካሪ አደረገህ።ጣልያናዊ አይደለሁም ለምን ትከራከራለህ።

በደሉን ስነግርህ አድዋ እኮ የአፍሪካ ኩራት ምናምን አትበል እኔ ኢትዮጵያዊው ነኝ አውቃለሁ፣ በደሌን ያነሳሁትን፣ አሳምነኝ።

የጭሰኛ ልጅ ሁሉ ትሰበሰብና ጭሰኝነትህን ረስተህ የሰለሞን ዘር ለመሆን ትሞክራለህ፣የንጉስ ዘር ለመሆን ትሞክራለህ። ደርሶ ወ ረ ሴ ክነት ።

የጭሰኛ ልጅ ነኝና ትንሽ እቤት ውስጥ በልጅነቴ ስከፌስ፣ንጉስ ንጉስ ሲያጫውተኝ፣እረ ተው ይህ ደርሶ ወረሴክነት ይቅርብህ ይለኝ ነበር አያቴ። ይህ የእኛ የቤታችን ቋንቋ ነው።ደርሰህ የሌላውን አትውረስ ማለት ነው በማለት ሴት አያቴ አስተማረችኝ።እንዴት የንጉስ ስሜት ይሰማሃል ብለው ያሳደጉኝ የጭሰኛ ልጅ ነኝ። ጭሰኛ ስትሆን አገልጋይ ነኸ እንጂ ገፊ አደለኸም፣የምን የገፊ አስተሳሰብ አመጣ ብሎ ነበር አያቴ ቁጣው።

አውቃለሁ ጓደኛየ፣ ምኒልክ የኢትዮጵያን ስም በውጩ አለም አስተዋውቆታል።ያ ደግሞ ለአንተ ያተረፈልህ ነገር ይኖራል።

ከየት ነው የመጣኸው ስትባል፣ ከኢትዮጵያ ብለህ ስትመልስ፣የት ናት ይች አገር ቢሉኽ፣ሚኒሊክን ብታነሳ ብዙ ህዝቦች ሊያቅፉኽህ ይችላሉ።ማንነትህ ያልሰጠኽን፣ በምኒልክ አትግዛ።እሱ አሻራውን በሁሉም መንገድ ጥሎ አልፏል። አንተ ግን ሚኒልክ ወይስ ኃይለ ስላሴ እያልክ ትከራከራለኸ።አገሬን አያውቅም ብለህ ወይ እንደ ይሁኔ በላይ አስረዳው።

ለምሳሌ ለንጉስ ኃይለ ስላሴ የሚከራከሩት በብዛት የልጅ ልጆቻቸው አይደሉም። አልፎ አልፎ ነው ድምፃቸውን የምትሰሙት ንጉስ ከሆንክ በተፈጥሮህ አትከራከርም ንግስንህ ይመሰክራል።ጭሰኞቻቸው ግን ስለሳቸው እንደተጫጩ ነው።ለምን ይመስላችኃል።ስማቸውን በአለም ስለገነቡ ንጉሱ፣ ጭሰኞቻቸውም ወደ እሳቸው ክብር ለመጠጋት ስለሚፈልጉ ነው።ከልብ የሚወዱአቸውም ቢኖሩ።

እውነቱ ግን ደርግ ወደ ዋገምት ሲያወርዳቸው የአብዛኛዎቻችሁ አባቶች ጨፍረው ነበር።የእነሱ/የጭሰኞቹ ልጆች ግን ጃማይካ ሲሄዱ በራሳቸው መታወቅ ስለማይችሉ ጃ ራስ ተፈርያን ትላለህ።ምክንያቱም ንጉሶቻችን የራሳቸው ብራንድ ትተው አልፈዋል።አንተ ደግሞ ብራንድ ሲከር ትውልድ ነህ።

እንዲገባኸ የቦብ ልጆች በአባታቸውም፣በራሳቸውም የኮሩ ናቸው።

አውቃለሁ የአያቶቻችን ማንነት የሁላችንም መሆኑን፣ነገር ግን ሁሉንም ገፅታ መቀበል ግድ ይላል።የኃላው ከሌላ የለም የፊቱ ።ነገር ግን እየመረጥክ ብቻ አትውሰድ።ሁሉንም እይ።ስለሚኒሊክ ብትዘፍን የሚያኮራው አንተን እንጂ ምኒሊክን አይደለም።ፕሮሞሽን ታገኝበታለኸ። ገብቶሃል።ለሃይለስላሴም፣ለኢትዮጵያም ብትዘፍን፣የሁላችንም ችግር ካልተፈታ እራስህን ፕሮሞት እያደረግህ ነው።you so called self agent!

ስለዚህ ሁላችሁም አንድ ሁናችሁ የእናት ሀገራችሁን ችግር የምትፈቱበትን መንገድ ካለ ፈልጉ እንጂ፣የያዛችሁት የፖለቲካ ትግል አንዱን አስደስቶ ሌላውን ያስከፋል፣ወደ ዘርኝ ይወስድብሃልና ሌላ ትርጉም ይሰጠዋል።ይህ የሆነው ደግሞ ተደባብሰው የሚያልፉ ፣ አዲስ ንጉስ ሲመጣ የተመለሱ እየመሰለን ተሸፋፍነው የሚያልፉ መሰረታዊ ችግር ስላሉ ነው፣እነዚህ ችግር ካልተፈቱ ደቡብን ስታስደስት አማራውን ታስኮርፋለኽ።

እኔ እየሞገትኳችሁ ያለሁት በራሳችሁ ሀሳብ ነው።ሁሉምን ሃሳቦች ፖለቲከኞቻችን፣ሙህራኖቻችን፣አርቲስቶቻችን የዘፈናችሁለትን፣ፊልም የሰራችሁለትን፣ግጥም፣ቅኔ የተቀኛችሁለትን ሀሳብ ነው እያስታወስኳችሁ ያለሁት።

ስትታገሉ ለመሰረታዊ ችግሮች መፍትሄ ሳታገኙ ሌላ የትግል አቅጣጫ አትቀበሉ።እባካችሁ ለወሬ አታጨብጭቡ፣ምራቃችሁን ዋጥ አድርጉ።ሰርቶ ሲያሳይ ስራወን አይተህ፣እንዴት ፣ለምን አላማ፣ እንደሰራው፣በማን እውቅና እንደሰራው ሳታረጋግጥ አታጨብጭብ።

በዲስኩር ስንት ዘመን ታጨበጭባለኽ፣እያሳተፈህ የተግባር ስራ ሰርቶ እስከሚሳይህ ለማንም አታጨብጭብ።

ዲሞክራሲያዊ ምርጫ አካሂዳለሁ ሲለህ ሆ ሆ ሆ ብለህ አትጨሁ።ምክንያቱም ነፃ የምርጫ ቦርድ መስርቶ ሊያሳ ይገባል።ፍትህ አመጣለሁ ሲልህ ለምን አጨበጨብክ ፍትሃዊ ተቋማት ሳይኖሩ፣ ስለዚህ ማንም ይምጣ ቅድሚያ መሰራት የሚገባቸውን ስራ ሳይሰራ አታጨብጭቡ።ይህን የምልህ የሚተገብርበት ተቋም የለውም።

የማንም ደጋፊ አትሁኑ እያልኩ አይደለም።የተለያዩ ሀሳቦችን አትደግፉ እያልኩ አይደለም።የደገፍካቸውን ሃሳቦች የሚተገብር ተቋም የለንም።ለምሳሌ የአሜሪካ ህዝብ ማንም ለምርጫ ቢወዳደር ለተመቸው ሀሳብ ድጋፍና ቅስቀሳ፣ማጨብጨብ ይችላል።

ድጋፍ የሰጠው መሪ ስልጣን ላይ ወጥቶ ህዝብ ድጋፍ የሰጠበትን ሃሳቡን ቢክድ የሚጠይቁበት ስርአት አላቸው።ወንጀል ቢሰሩ/ቢጠረጠሩ የሚጠይቁበት ስርአት አላቸው።እኛ አገር ግን ጀኖሳይድ ተፈፅሟል፣ አልተፈፀም ክርክር ላይ ነን።ይህን ድርጊት፣የህዝብን በደል የሚፈትሽ ስርአት የለንም።መንግስት የሚሰጥኽን መግለጫ ብቻ ትቀበላለህ።

ስለዚህ እንደ አፍሪካ፣እንደ ኢትዮጵያ እየኖርን እንደ አሜሪካ ንፅፅራዊ ከሆነ ፖለቲካ እንውጣ።ፑቲን ፈረስ ይጋልባል፣አብይ ብሽክሊሊት ቢነዳ ምን አለበት አትበል ይቺ አገር ሩሲያ አይደለችም።መብቱ ነው ነገር ግር ወቅታዊ ሁኔታን ማገናዘብ ያስፈልጋል።

ስለዚህ የሰውን ልጅን ሚኒመም ሪኳየርመንት፣ቤዚክ ኒድ  የሆነውን በሁሉም ክልል የመኖር መብት አረጋግጡል።ከዚህ ውጭ የሆነ ግሩፕን ብቻ ነው ይዘህ የምትጓዘው።

አባቶቻችን ታሪክ የሰሩት እንደራሳቸው እንጂ እንደ ነጮቹ በመሆን አይደለም።የኢትዮጵያ ንጉሳውያን ክብር ያገኙት እንደ ኢትዮጵያ ንጉስነታቸው እንጂ እንደ እንግሊዛውያን ንጉሳውያን አስተሳሰብ አይደለም።በግሎባላይዘሽን አለም የምናውቀው ሁሉ በእኛ አይሰራም።የሚሰራልችሁም አላችሁ።አንድ ሀብታም እንደ ሆሊውድ ሰለብሪቲ ለመኖር ከምትሞክር ወግንህን ብታየው ጥሩ ነው።የሆሊውድን ኑሮ ስታይ፣በመዝናኛው ስታቀርብ፣የፍልፍሉንም ክራብስ አብረህ አሳይልን።ደግሞ እቤቱ እንዳትሄድ የሰራውን ቀልድ ነው ያልኩህ።ለማኝኛው ይመቻችሁ።

ሌላው ማለት የምፈልገው ሀሳብ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በህዝብ የሚመረጥበት መንገድ ቢመቻች ጥሩ ነው።በፕሬዝዳንት መመራት እያልኩ ሳይሆን፣ሀሳቤ ለምሳሌ መጭውን ምርጫ ብልፅግና ቢያሸንፍ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገና ነው የሚመረጠው።ስለዚህ አሸናፊው ፓርቲ ቀጥታ የጠቅላይ ሚኒንስተር እጩዎችን  ለህዝብ ቀርበው የህዝብ ድምፅ የሚካተትበት ስርአት ቢኖር።ከወከሏቸው በተጨማሪ የህዝብን ተሳትፎ ቢሰፋ፣ወጭ ሊጨምር እንዲሚችል አውቃለሁ። ነፃ ኤስ ኤም ኤስ፣ሌሎች ፕሮግራሞችን ብትሰሩ፣ወይም የምርጫ ስርአቱን ለህዝብ በይፋ በቲቪ ብታስተላልፉት። ይህን ያልኩት የህዝብ ተሳትፎን ለማስፋት ነው።ምክርቤታችሁ በብዛት የመረጣቸውን ህዝብ ውክልና ትቶ የመንግስት ስራ አስፈፃሚ ስለሚሆን ነው።በፕሬዝዳንት እንደ አሜሪካ መመራት የሚሉትም ሀሳባቸውን ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ቢጠና።ይህን ሁሉ ለማድረግ ደግሞ የዘረኝነት ቀንበር ሲሰበር ነው። በሰማይ በዙ መንገድ አለ ተብሏል።ሰማያዊውን ከያዝክ በምድር ብዙ መንገድ አለ።እባካችሁ ሁሉንም መርምሩልን።ሁላችንም ኃጥያተኞች ነን።ምንም ኃጥያት ያልሰራ ካለ ወንድሙምን በድንጋይ ይውገረው በድጋሜ።

ዛሬ 28/02/2013 ዓ.ም ነው፣ምንም የመፃፍ ሀሳብ ሳይኖረኝ፣እንደፅፍ የሚያስገድዱኝ ልምድ አለን የሚሉት ፖለቲከኞች ናቸው።I am a zero days politicians.

የኢትዮ 360 ዎቹ ፖለቲኮ-ጆርናሊስቶች የታወጀውን ጦርነት ሲተነትኑ በብዛት ጦርነቱን ሊያብራሩ የሚሞክሩት ከአማራ ህዝብ ጥቅም አንፃር እንጂ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚያመጣው ችግር ብዙም አያሳስባቸውም።በትግራይ ክልል አማራው ተወስደውብናል ስለሚሉት መሬት እንጂ ስለሚፈሰው ደም ፣ስለሚፃፈው ታሪክ ብዙም ችግር የለባቸውም።

የአማራ ህዝብ ሆይ ታሪክ እራሱን እየደገመ ነው።ወንድምህን ለመዋጋት መጥረብያ ሳይቀር ይዘህ ክተት ብለህ

ዘምተሃል።መጥረብያውን ምን ልትቆርጥበትነው? የያዝከው፣ታሪክህን ደገምከው።በግልፅ ልንገርህ በምንሊክ የመስፋፋት ዘመቻም

ክተት ስትባል ለምን ሳትል ልክ እንደዚሁ ነበር የዘመትከው ወንድምህ ላይ።

የአጫሉ ሁንዴሳን ጥያቄ ሳትመልስ መጥረብያ ይዘህ ትዘምታለህ።አሁንም አንተ ጅግና አይደለህም ነፈጠ ነህ።የጎንደርን ታሪክ

አታበላሽ፣የመይሰው ካሳን ታሪክ አታበላሽ ከእንግሊዝ ጋር ሲዋጋ ነው እራሱን የሰዋው በእንዳንተ አይነቱ ባንዳ ተከድቶ።

ከገባህ በትግራይ ህዝብ ላይ ሌላ አኖሌ ልትገነባ እየተጣደፍክ ነው።ወሬ የሚያወቁ መሪዎች የሚሉትን ዲስኩር ብቻ ሰምተህ ሆ

ሆ ሆ እያልክ የመይሰው ካሳ ዘር እያልክ መጥረብያና ሜንጫህን ይዘህ ትዘምታለህ።

ጎንደር እኮ የህይማኖት ሀገር ናት።እንዴት እምነትህ ፈቀደልህ።

ሌላው ሊገባህ የሚገባው ትግራይ የኢትዮጵያ ማህፀን ናት፣ትግራይ የኢትዮጵያ ሞትር ናት ብሎ ጦርነት ያዘመተህ መሪ እቅዱን

ምንድን ነው የሚለውን ማወቅ አለብህ።

የኢትዮጵያን ማህፀን፣ሞተሯን ሊያወርድ በሚሯሯጥ መሪ ተመርተህ ለጦርነት ወጣህ።ለማንኛውም በሰማይም

በምድርም፣የተወገዛችሁ ናችሁ።

እውነተኞቹ ኢትዮጵያውን ልታወግዙት ይገባል።

መንግስት ጦርነት ካወጅ እራሱ ሀጥያቱን ሊወርስ  ይገባል፣የራሱን መከላከያ ሰራዊት አሳምኖ መጠቀም ይችላል ኪዘህ ውጭ

የልጅ ልጅህ የሚወርሰው ቀፋፊ ታሪክ እየሰራህ ነው።ትግራይን አሸንፈህ ስትጨፍር ታየኝ፣እግዝያብሄር ይፍረድ።ጀግና ተብለህ አብይ

ሲያመሰግነህ ታየኝ። ፅዮን ማርያም ከማን ጋር እንደቆመች ስለማታውቅ አትሮክር።

ሀብታሙ አያሌው የ 6 ወር ፖለቲከኛ እኔን ሊያሳምነኝ አይችልም ትላለህ።መቼ ፖለቲካ አንተ ታውቃለህ መጀመሪያ።እኔ

ለፖለቲካ ዜሮ ቀን ነው ሪከርዴ። ግን አንተ ጋር ምንም እውነት የለም።በማንኛውም መንገድ ልክ የህይማኖት አባቶች እንዳወገዙት

ነው ማውገዝ ያለባችሁ።

የአማራ ብልፅግና ምን ያህል ለአማራ መብት ታግሏል፣በሁለት አመት ውስጥ ምን ያህል የንፁህ አማራውያን ደም ፈሷል፣ችግሩን ያልመለሰለትን መሪ ደግሞ ወንደሙ ላይ መጥረብያ ይዞ ሲዘምት ለምን አልተቃወምክም።ስለዚህ ነፍጠኛ የሚለው ስምህን እያደስክ ነው።የምንሊክ ጠባሳን ሳታክም ሌላ አሻራ ሊያስቀምጡ ሲሄዱ ለምን አልተቃወምክም።

የፖለቲካ እውቀትህ ገደል ይግባ።ደግሞ ሴራ ለመተንተን፣ብዙ ሴራወችን ስላወቅህ አንተ ፖለቲከኛ ልትሆን አትችልም።

መጀመሪያ አከባቢ ስለአንተ የሚሰማኛ ምን እንደነበረ ታውቃለህ ሲሳይ አጌና በአብይ የጎረሰውን፣አንተም በደመቀ መኮንን እንደጎረስክ ይሰማኝ ነበር።

እንዳውም ኢትዮ 360 የኢሳት ታክቲካል ዲቭዥን እንደሆነ ነበር የሚሰማኝ።ገብቶሃል የስራው ባህሪ።ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ አይደለህም፣ህብታሙ አያሌው ነፈጠ ብየህ አለሁ።

ኤርምያስ ለገሰም ጥንቃቄ አድርግ።ኢትዮጵያዊነትን የምታይበት አድማስህን አስፋ፣ለምሳሌ ህወሃት ያደረገችውን ብአዴን አድርጎት ቢሆን የትግል አቅጣጫህ ሌላ ሊሆን እንደሚችል እወቅ።

ብአዴን አልደመርም ብሎ.የራሱን ምርጫ ቢያካሂድ፣አቋማችሁ ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።ገብቶሃል።የአማራውን ህዝብ የምታሰድቡት፣እናንተ መሰልና መሪዎቹ ናቸው ከጥንተ ጀምሮ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ይህንን ጦርነት ልታወግዙ ይገባል።አይ ጦርነቱን ያስጀመሩት እነሱ ናቸው፣የሚል መልስ የምትሰጡ ባለሞያዎች፣ማረጋገጫ እፈልጋለሁ።ከዛውጭ የመንግስታት ሴራ አልገባህም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ትግራይን ሊወጉ የዘመቱት አማራ ነን የሚሉ ነፍጠኞች አማራን እንደማይወክሉ ልገልፅላችሁ እወዳለሁ።እነዚህ ደቡብ ጋር ቢሆን ጭግሩ፣ሶማልያ፣አፋር፣ወዘተ ጋር ቢሆንም ችግሩ መጥረብያ ይዞ ለመዝመት የሚነሱ የነፈጡ ናቸው።

ስለዚህ እኔ በአማራ ህዝብ ስም የትግራይንም፣የኢትዮጵያውያን ህዘብ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

የወልቃይት፣የዳንሻ ህዝብ ሆይ ችግርህን በሰላም እዲፈታልህ ነው መታገል ያለብህ።በጦርነት የሚመጣ ድል ያው ደም ነው።

ሌላው ኢሳት አጌናዎች፣ጦርነቱን የምትመሩት ኮማንደሮች ለመሆን እየሞከራችሁ ነው።

ለማንኛውም አቶ ግዛው ከጦርነቱ በኃላ አብረን የምንኖር ህዝብ ነን ትላለህ።እርግጠኛ ነህ።ተገደን አብረን ልንኖር እንችላለን።ልክ የኦሮም ህዝብ ለረጅም ግዜ አብሮ እንደኖረው፣ግን ግዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ ፈንጅ ነው።እርግጠኛ ሁኜ ልንገርህ፣ትልቅ ጠባሳ እንዳለው አትዘንጋ።ሲመቻቸው ግዜ ጠብቀው ባለመጥረቢያውን ህውልት ያቆሙለታል። በአዕምሮአቸው ውስጥ ግን አሁንም ህውልቱን ሰርተዋል።

የህገ መንግስትና የአገርን ሉአላዊትንት ለማስከበር ነው ትላላችሁ።የማንን ህገ መንግስት ነው የሚያስከብሩት፣የማንን ሉአላዊት ነው የምታስከብሩት፣ሁልህም ጨዋታውን ወደ ምትፈልግበት አስተሳሰብ ትዘውረው አለህ።

በቃ ጦርነቱን የወለደው የትግራይ መንግስት ለአብይ የመደመር አስተሳሰብ ስላልተበረከከ፣ስላልተገዛ፣እራሱን በራሱ የማስተዳደር የመሳሰሉት አላማዎች፣ ለፌደራል መንግስቱ ንግስናውን ያለማሳካት የፈጠረበት ስሜት ነው።ስለዚህ የምትሰጡት አስተያየት ለትግራይ ህዝብ ያላችሁን የጥላቻ ጥግ ነው የሚያሳየው።

ማረጋገጫህን አሳየኝ የትግርራይ ህዝብና ህወሃት አንድ አለመሆናቸውን።ከመደመርና ከህወሃት የሚሻላቸውን እነሱ መርጠዋል።አመራሮቹ ወንጀለኞች ናቸው ካልክ ደግሞ የሰይጣን ፍትህ አንፈልግም።

ሌላው ለመከላከያው ሰራዊት ስንቅ፣ደም ለግሱ፣ሲቆስል ህክምና፣ሲሰዋ ቅበሩት እያልክ የምታናፋው አጌናዊ መከላከያ ሰራዊቱን አለላስፈላጊ መስዋት እንዲሆን ጥሪ ታስተላልፋልህ፣ነዳጅህን ብትቀዳ ይሻልሃል።ዩቲዩብ ስንቱን አዋቂ አደረገው፣ከሽንት ቤት አጣቢነት እየተነሳ ሁሉን ጋዜጠኛና አክትቪስት አደረገው። ይቅርታ የተከበራችሁ ዲያስፖራ ኢትዮጵያዊና በፅዳት ሞያ ላይ የተሰማራችሁ ኢትዮጵያውያን።እኔም የፅዳት ሰራተኛ ነኝ።አስተያየቴ በቀጥታ እሱን ነው የሚመለከተው።

አይዞአችሁ መሬትን ስታፀዱ የእግዚያብሄር የእግሩ መረገጫ ታህታይ ምድርን እንዳፀደቃችሁ ቁጠሩት።ስለዚህ የእግሩ መረገጫን ማንም ሲያቆሽሽ እናንተ እያፀዳችሁ መሆንን እወቁ።የሁሉንም ስራ አከብራለሁ።

ለማንኛው ጦርነት መንግስት ሊያስነሳብህ ከፈለገ ምክንያቱንም እራሱ ፈጥሮ ሊሰጥህ እንደሚችል ማወቅ አለብህ።ስለዚህ ምእራብ ወለጋ ላይ የራሱን ጨዋታ በመጫወት ንፁሃን ዜጎችን እንዲጨፈጨፉ አስደርጎ፣ህወሃትና ሸኔ በመተባበር ያደረጉት ነው የሚል ጨዋታ አጫውቶህ፣ዳንሻ አከባቢ በራሱ ሰዎች ጦርነት ቀስቅሶ ዞር በማለት።

ጧት ላይ ህወሃት ናት ጠላትህ በማለት ጦርነት በማወጅ የተለየዩየ ምክንያቶች ጨምሮልህ፣መጥረብያ ሊያሽክም ይችላል።ስለዚህ ሁለት ግዜ አስብ ወንደሜ፣ መንግስተ ሰማያት እንዳታመልጥህ።

ኢትዮጵያውያን ነን የምትሉ በሙሉ ትግራይ የመገንጠል መሰረቷን እያኖራቸሁ እንደሆነ ሊገባችሁ ይገባል።ኢትዮጵያን የምትወዷት ከሆነ ለማዳን ግዜው አሁን ነው።

አብይ በዲሞክራሲ እንጂ ህወሃትን ማሸነፍ ያለብህ በሴራ አይደለም።ወንጀለኛ የምትለው የህወሃት አመራር ካለ መጀመሪያ የትግራይ ህዝብ አብይ አህመድ ንጉሴ ብሎ እንዲቀበልህ አድርግና ጠላቱ ናቸው የምትላቸውን ለፍርድ አቅርብለት።

ከዚህ ውጭ አብይ አህመድ አሊ አዔ በጉልበቱ ነህ።

ሌላው የህወሀት አመራር እነ ደብረፅዮን እንደጋዳፊ  ሲጎተቱ ማየት የተመኘህ፣ሙብረቅ ከሰማይ እንዲወርድባቸው የተመኘህ በኦርቶዶክስ ሀይማኖት መምህርነት ጭብል የተሸፈንክ ተኩላ ነህ።

የእስልምና ተከታይ አባቶችና አማኞች ይፍረዱ፣የጋዳፊ ሀጥያት ምንም ምንም ይሁን አሟሟቱ ልክ ነው፣ ብለህ ጠይቃቸው። በአላህ ሀራም ነው፣ሀራም ነው፣ሀራም እያለ ነው በግፍ የገደሉት።ስለዚህ ይህ አይነቱ አገዳደል ለፍትህ ቢሆንም በሃይማኖትም፣በሰባዊነትም ሀራም ነው።ስለዚህ ሀራም አትናገር። አንተን ሀራም ነህ ብየህ አለሁ።

የኦርቶዶክስ ሀይማኖትን የሚጠብቃት መንፈስ ቅዱስ እንጂ አንተ አይደለህም።መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድልን ፀልይ እንጂ ቤተክርስትያን ብቀላ አትፈልግም፣አስተምሮቷም አይደለም።አሁንም ጆሮውን ሲቆርጡት ጆሮውን ያዳነ አምላክ እንጂ ጴጥሮስ ብራቮ ያለ አይደለም አማኑኤል የድንግል ልጅ።

ጴጥሮስ የራሱን ሳያውቅ ጌታውን ለማስደሰት ጆሮ ቆረጠ።እሱ ግን ዶሮ ሶስት ግዜ ሳይጮህ፣3 ግዜ ከድቶታል።ስለዚህ ራስክን መርምር።ፍቅርህ ሊያስትህም እንደሚችልም እወቅ፣እያልኩህ ያለሁት ወንደሜ  ጴጥሮስ ጌታውን ስለሚወድ ነው አግዞለት ጆሮ የቆረጠው።የእግዘብሄር ፍቃድ ግን ጆሮውን  ማዳን ሆነ።

አሁንም ፍቅሩ ከኋላ እንዲከተል ሲያደርገው፣አማኑኤል እኮ ጴጥሮስን እየተከተለው ነበር።ፍቅሩ ነው እንዲከተል ያደረገው፣በመጨረሻም ጴጥሮስ 3 ግዜ ከዳው።የማይሳሳተው ቃሉ ተፈፀመ።በጴጥሮስ እኛን አስተማረን።ፀልዮ ፈተና እንዳይበዛችሁ በአላቸው ግዜ አለመፀለይ ለፈተና ይዳርጋልና።ቃሉ ህያው ነው።

ሌላው የቤተክርስትያን ጠበቃ ክርስቶስ ነው።እሱን ተማለድ እንጂ አንተ የአህያ ባል እንደሚባለው እንዳትሆን።

ቤተክርስትያኔን በአንተ እገነባለሁ ብሎ ጴጥሮስ በሚባል አለት ነው የገነባው።ይህን አለት ማንም አይነካውም ቃሉ እውነት፣ህያው ነው።

ስትገነቡ በትክክለኛው አለት ገንቡ።ቅዱስ ጴጥሮስ በሚባል አለት ገንቡት።ከዚህ ውጭ ይፈራራርሳል ጅብ የጮኸ እለት።

ስለዚህ አንተ የደብረ ፅዮን አስከሬን መንተት ስትፈርድ የክርስቶስ ፍቃድን ግን አታውቅምና የምታወራውን በሰማይም በምድርም ዝም ብለህ አታስመዝግብ።ሰማይም ምድርም መዝግበውልሃል። ራስህን መርምር ወንድሜ።

በፖለቲካ ሀይማኖተኛ እንዲሳተፍ ስታስተምር ሰምቼአለሁ ጥሩ። ነገርግን እንደ አንተ ሀራም ሊናገርና ሊሰራ ግን አይደለም።አፍህን ዝጋና የሃይማኖት አባቶች የሰጡትን መግለጫ ስማ።ከለምንም ቅድመ ሁኔታ ጦርነቱን እንዲቆም ነው ያስጠነቀቁት፣አምላክን መፍራት እንደዚህ ነው።

በመማር ባለመማር አላምን ነበር ያለመማር ችግርን በአንተ አየሁ፣አለማዊ እውቀትም፣መንፈሳዊ እውቀትም የለህም፣ደፋርና ፈጣጣ ግን ነህ።ማን እንደሚናገርህ አታውቀውም ስለዚህ የሚያናግርህን መርምር።

ከባህታዊ ገ/መስቀል የወረስከውን ርኩስ መንፈስ የተፋታኸው አልመሰለኝም። ራስህን መርምር፣አስመርምር።ይህቺ በህዝብ የመሰማት፣ገንዘብ የማስወጣት፣ በሰው ዘንድ ታማኝ መስሎ መታየትን፣ ሀይማኖተኛ መምሰልን፣ድፍረትና ፈጣጣነትን ያወረሱህ ባህታዊ ገብረ መስቀል ከቆሪጣቸው አንዱን፣ሁለቱን፣ከዝያም በላይ የሆነ ቆሪጦቻቸውን ስላወረሱህ ነው።

የኢትዮጵያ ትንሳኤ አብሳሪ ናቸው እየተባሉ ህዝቡን እያንጓለለ ሲያጫውቱ ዋና ደቀ መዝሙራቸው ነበርክ፣ ያወረሱህም ርኩስ መንፈስ ነበር፣ምክንያቱም ሊጠቀሙብህ ስለፈለጉ።ገንዘብ ለመሰብሰብና የእሱን ተሰሚነት ለመጨመር አስመላኪ ነው የነበርከው፣የተወሰኑ እርኩስ መንፈሳቸውን እንደገጩህ እርግጠኛ ሁኚ ልንገርህ።

አፍህን እየከፈትክባቸው ዝም ብለው የሚሰሙህ ለምን ይመስልሃል።ስለዚህ ባህታዊ ገ/መስቀል ማለት የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ሴቷ ስንዱ ማለት ነው ከገባችሁ፣ስለዚህ መስቀሉን እያሳየ፣የእቤታችን ስእል አድኖ እያሳየ የስንዱ ደቀ መዝሙር የነበረው ማለት ነው።

አውቃለሁ በንሰሃ ፀድተህ ሊሆን ይችላል፣ነገር ግን የወረስካቸውን ርኩስ መንፈሶች እንደተፋታችሁት እርግጠኛ መሆን አለብህ።ከዚህ ውጭ አሪወስ ነህ።

ሌሎቻችሁም የባህታዊ ገ/መስቀል አስመላኪ የነበራችሁ ሰዎች ንስሀ ብቻ ገብቶ ዝም ማለት ሳይሆን መንሶቹን በእግዚያብሄር ሀይል እንዳሸነፋችሁ እርግጠኛ መሆን አለባችሁ።

በታዋቂነት ደረጃ ያላችሁ የሳቸው ደቀ መዝሙሮችም አላችሁ፣የእሳቸውን መንፈስ እስከአሁን ተዋርሳችሁ ራሳችሁን ፕሮሞት ያደረጋችሁ ብዙ አላችሁ ስለዚህ ራሳችሁን መርምሩ።በአሁኑ ሰአትም እሳቸው መሰል ተረኞችን የምትከተሉ ብትጠነቀቁ ጥሩ ነው።

አንገትህ ላይ ያለውን መስቀል ሁልግዜ እያሳየህ ትመፃደቃለህ አማኝ እንደሆንክ፣ጥያቄ ልጠይቅህ መስቀሉ የተሰራበት እንጨት ምንድን ነው? ወገኖቼ ይህን እየጠየቁት ያለሁት በመስቀል ስማላምን አይደለም።ማወቅ ያለባቸሁ መስቀልን በግራው  የተሰቀለበትም እንዳ እወቁ።እንኳን አገትህ ላይ ማድረግን ብትሰቀልበትም ላትፀድቅ ትችላለህ።ከአንደበትህም የሚወጣው ይወስነዋል።

ከዚያ በፊትም ወንጀለኞች ነበሩ በመስቀል የተሰቀሉ <u>ስለዚህ መስቀልን የቀደሰው ክርስቶስ ነው እንጂ መስቀል አይደለም ክርስቶስን የቀደሰው</u>።

ስለዚህ መስቀልህ የማን እንደሆነ እወቅ።

ሌላው የረከሱ ደብተራዎች፣ርኩስ መንፈስ ሳቢዎች የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ እንጨቶች/ዛፎች አሉ፣ ሳይቆረጡ ድግምት ደግመውባቸው፣ከተቆረጡም በኋላም በመድገም መቁጠሪያ፣መስቀል፣ወዘተ በመስራት እራሳቸውን በሰይጣን የሚያስመልኩ አሉ።

ስለዚህ መስቀልህ የማን ነው? ገብቶአችኋል ምእመናን፣አባቶችን ጠይቁ ለበለጠ መረጃ።ስለዚህ የመምህር ግርማ መቁጠሪያዎች ሁሉም ባይሆኑ በውስጥ የተወሰኑት በእንደዚህ አይነት መንገድ ተሰርተው የተቀላቀሉበት ስለሚሆኑ መርምሩ።

በነዚህ የተሰሩ መቁጠርያዎች ተፅኖውን በዚህ መንገድ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ እወቁ።መስቀሉንም በአንገታቸው በማሰር፣አባት ነን እያሉ መስቀሉን በማሳለም ተፅኖ ሊፈጥሩብን እንደሚችሉ ማወቅ ያስፈልጋል።

መቁጠርያውን ከሌላ ነው የገዛነው የምትሉ መንፈሱ በመቁጠርያ ብቻ ሳይሆን  በሌላም መንገድ መኖሩን እወቁ፣

ሌላው ልታነሱት የምትችሉት ጥያቄ ሰይጣን የመስቀል ቅርፅን ይፈራል አይደለም እንዴ? ሊሆን ይችላል።መልሱን አባቶችን እና ወንጌላውያን ጠይቁ።

ለእኔ ግን መስቀልህ የማን ነው የሚል ጥያቄ አለኝ።እናንተ ደግሞ ሰይጣን መስቀል አይዘም ልትሉኝ ትላላችሁ።እኔ ግን ሰው ተመስሎ፣በሰው በማደር ሊሸከም ይችላል እላለሁ።እንደዛ ባይሆንማ መስቀል አንገትህ ላይ እያለ እርኩስ መንፈስ ባላሰቃየህ ነበር።

እምነትህ ነው የሚያድነህ። መስቀሉ የሀይማኖትህ መግለጫ ነው።ጠንካራ እምነት ካለህ ደግሞ መስቀልህ ሀይል ነው፣አሸናፊ ነው፣መድህን ክርስቶስ በውስጥህ ካደረ።አባቶች እኔም የእናንተን ትምህርት እሻለሁ።አለማወቄን በእውቀታችሁ ምሯት።

በረኸኖቹ አባቶቼ ማን ያውቃል የኢትዮጵያን ትንሳኤ አንተ ብትሆንስ የምታበስረው ብለውኛል ስትል ሰምቼ አለሁ፣እንደቸርነቱ ነው። ነገር ግን ራስህን መርምር፣ጋዜጠኛ ሁነህ ነው የምታበስረን ወይስ ንጉስ? ለማንኛው እግዚያብሄር ቸር ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የኢትዮጵያንም፣የአለምንም ትንሳኤ የሚያበስረው ሰው ሳይሆን የድንግል ማርያም ልጅ አማኑኤል ነው።ንጉስ ቶ፣ቴ እያልክ ፊደል አትቁጠር።ትንሳኤአችን ከስላሴ ነው፣ከመድህን ክርስቶስ ነው፣ከእናታችን ከድንግል ማርያም ነው፣ከእልፍ አላፋት ቅዱስ መላእክት ነው። እንጂ ከምድራዊ ሰው አትጠብቁ።በሰው ላይ አምላክ እንደሚገለፅ አውቃለሁ።ስለዚህ ሓያሉ የድንግል

ማርያም ልጅ ስለሆነ የሁሉም ሚስጥር ምስጋና ሁሉ ለእሱ ስጥ።ዘለህ ንጉስ ላይ አትንጠላጠል።ታቦት ልትቀርፅለት አትቸኩል።እዚህ ላይ ቅዱሳን አባቶችን እየተቃወምኩ አይደለም።ቃልኪዳኑን አምናለሁ።

የአፄ ሚኒሊክ ጉዳይ ሲነሳ አብዛኛዎች ተከራካሪዎች ኦርቶዶክሳውያን ናችሁ።ማወቅ ያለባችሁ ሀያሉ ሚኒሊክ ሳይሆን እግዝብሄር ነው፣ሀያሏ ቤተክርስትያን ነበረች፣ታቦት ይዛ የዘመተችው፣ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዎርጊስ ነበር አርበኛችን፣በስአቱ የነበሩ የሀይማኖት አበቶች ነበሩ ጀግኞቹ።

ስለዚህ የሚኒሊክ የአገር ውስጥ ችግሩ ሲነሳ አትንጫጩ።ሚሊሊክና ኦርቶዶክስ አንድ አይደሉም።አንድ የእምነቱ ተከታይ እንጂ ሌላ ፃድቃን አይደለም/ቅዱስ ንጉስ አይደለም። ቤተክርስትያን አስገንብቷል ጥሩ፣ነገር ግን የንፁሀንንም ደም  አፍሷሷል።የማሸነፍና የመሸነፍ ፖለቲካ ውስጥ ከገባችሁ መብታችሁ ነው።

የሰው ልጂ ሲወለድ ክርስትያል ክሊር ነው፣ምንም ያለተፃፈበት፣ምንም እንኳን ፍራተርናልና ማተርናል ኢፌክት ቢኖርበትም በሳይንስ አረዳዳድ።

በዚህ የሳይንስ እውቀት ሰው የሚባለው ማንነቱ የሚገነባው ከአባቱ ከእናቱ በሚወስደው ክሮሞዞሞች ነው 23/23 ከእናትና አባቱ፣ማንኛውንም የዘር ተፅኖ ከዚህ ነው የሚጀመርው።በፅንስ ህይወት ውስጥም እያለ የእናቲቱ የአኗኗር ዘይቤዋ በልጁ ለይ ተፅኖ እንደሚያሳድሩ ጥኖቶች ያረጋግጣሉ።

ስለዚህ አንድ ህፃን ልጅ ሲወለድ ፕሪ ስቶርድ/ ፕሪ ድተርማይንድ የሆነ እውቀት ቢኖረወም፣ክርስትያል ክሊር ነው/ነጭ ወረቀት ነው።

ስለዚህ ይህንን፣ነጭ ወረቀት፣ማን ነው የሚፅፍበት የሚለው ይወስነዋል፣በዚህ መሰረት ወላጅ፣አከባቢ፣መምህራን፣በአጠቃላ አገር፣የግሎባላይዜሽን ብእሮች ሁሉ በነጩ ወረቀት ላይ ያርፋሉ።

እሰከ ተወሰነ አመትድረስ ትክክለኛው እድሜውን ለባለሞያወችን ትቼው አለሁ፣እኔ ሃሳብ ነው የምሰጣችሁ ምክንቱም ሰፊ ጥናት ነው።

ስለዚህ እስከተወሰነ አመት ድረስ የልጆች አዕምሮ ራም ማለትም ራንደም አክሰስ ሚሞሪ ነው። ይህ ሚሞሪ የፈለከውን ፅፈህበት ልጣጠፋው ትችላለሁ ሁሉንም፣በከፊል አጥፍተህም ስህተቱን ልታስተካክለው ትችላለህ።በአጠቃላይ መጥፎና የማይፈለገውን ለማጥፋትና ለማስተካከል ላፒሳቸው መሆን ተችላላችሁ።

ከተወሰነ ግዜ በኃላ ይህ ኢዲት የሚደረግ እውቀት ወደ ቋሚ እውቀትነት ይቀይሩታል።ይህ ማለት ሮም ማለትም ነው።

ሮም ማለት ሪድ ኦንሊ እውቀት ይቀይራል፣ስለዚህ ዝም ብለህ መጥተህ ኢዲት ማድረግ አትችልም።ምክንያቱም ወደ ፐርማነት እውቀት ተቀይሯል።

ብትከራከረው መልስ የሚሰጥህ ፐርማነት እውቀቱን እየመረመረ ነው።ያንተ እውቀት ሊያርመው/ኢዲት ሊያደርገው አይችልም።

ስለዚህ ራይት ፕሮቴክትድ የሆነው እውቀቴን ለማረመረ ዘለህ ኮሞከርክ ትጣላኝ አለሁ።አብሬ የፃፍኳቸው ህጎችም አሉኝ።ስለዚህ ይህን ቋሚ እውቀቴን ለማስቀየር አቅም ካለህ መንገዶች አይጠፉም እና መንገዶቹን ከእኔ ጋር በመደራደር መፈለግ ተችላለህ።ከዚህ ውጭ ትራንስፎርም አድርጌአለሁ።ከራም ወደ ሮም ተሸጋግሪ አለሁ።ከቻይልድ ሁድ ወደ አደልት ሁድ ተሸጋግሬ አለሁ።

ፖለቲካችንም፣እምነታችንም የዚህ ውጤት ነው፣ስለዚህ አንተ ነባሩ ፖለቲካኛ ነፈጠ ገብቶኃል ግጭት እንዴት እንደሚፈታ እየጠቀምኩህ ነው።

ሌላው የሃማኖት አባቶች እርግማን፣ሀጥያት፣ደም ማፍሰስ፣ሰይጣን፣ወዘተ ነገሮች በዘር ይተላለፋል የሚሏችሁ አንዱ መንገድ ይህ ነው።እነዚህ ሀጥያቶች በአባትና በእናት ካሉ፣በእያራሳቸው 23 ክሮሞዞሞች ላይ በፈለጉት ዲኤንኤ sequence randomly or by any means ይፃፉሉ።ግልፅ እንዲሆንላችሁ በውንዱ ስፐርምና በሴቷ እንቁላል ላይ ስላሉ ሊቪንግ ሴል ነው የማወራችሁ።የወንዱና የሴቱ ሲዋሃዱ የየራሳቸውን ትሬት ይዘው ነው የሚሃዱት።ከዛ በእርግዝና ግዜ ያሉ እምነቶች ተጨምረውበት፣ከተወለደ በኃላ ያሉ እምነቶች ይቀጥላሉ በአጭሩ።እያለኩህ ያለሁት እንዲገባችህ ጥናት አድርጉ፣ባለሞያቸውን ጠይቁ ከባህሩ በጭልፋ ነው ላሳያችሁ እሞክራለሁ።ገና በእንቁላሉ ብልህ የተረተትከው ለዘዚህ ነው።

አብዛኛዎቻችሁ ምሁራን የእውቀት ችግር እንደሌለባችሁ አውቃለሁ።እውቀታችሁን ስትሞግቱበት ጎበዞች ናችሁ።ምሳሌ፣ምሳሌ በማን ልስጥ ራንደም ሰለክሽን ዋው አገኘሁሽ፣ መምህርና ጦማሪ መስከረም አበራ ጎብዝ ጦማሪ፣መምህርና ለጠቅላይ ሚንስትርነት ሁሉ የሚመኙሽ አክትቪስት ነሽ።ሀሳብሽን አላመሽን የምትገልጭበት ሀሳብ/የስነጥበብ እውቀት አለሽ፣ ችግርሽ ግን፣You are still in your own uterus, you are still your own zygote minded activist.

እያልኩሽ ያለሁት ገብቶሻል የምትኖሪው በዘር የወረስሽውንና በእናትሽ ማህፀን እያለሽ በአንብላይካል ኮርድ/በእትብት የወሰድሽውን፣በእንሽቴ ውሃ ወደ አፍሽሽ ወስደሽ፣መልሰሽ ሽንተሽው፣እንደ ገና የወሰድሽውን፣ሳንባሽን ሞልቶት የነበረው ሽንትሽን አሰውጥተሽ መተንፈስ ስትጀምሪ ማንነትሽ በእነዚህ ሁሉ የተመሰረተ ነው።

የአስተዳደግሽ፣የሀገርሽ፣የመምህሮችሽ፣የፍላጎትሽሽ ወዘተ ውጤት ነሽ።አዎ ሁላችንም የዚህ ውጤት ነን።እንዴት ከተወለድንበትና ከተፀኖአችን ማህፀን ውጭ ማየት አቃተን።

የማናግርሽ እኔ አጫሉ ሁንዴሳ ነኝ።ምን ያክል እኔን ተረድተሽኝ ነበር፣ መልሽልኝ? ስለእናቴ አዘንሽ አይደል፣እወጋሽኝ ለእናቴ አትዘኝ፣እኔ የእናቴ ውጤት ነኝ።

ሌላው ጎፃን ነው ያለከው የ 46 አመት ልጅ ከነፈጠነትህ ውጣና ዳኘኝ።ጥያቀዎች ነበሩኝ አያትህም፣አንተም ልጅህም ሳያሳምነኝ በሃጥያትና በግፍ ተገድያለሁ።

ስለዚህ የኦሮሞ ህዝብ ሆይ የእኔን ደም መካስ ከፈለክ ደም በማፍሰስ ሳይሆን በደለኝ የምትለውን ህዝብ ላይ ሳላማዊ ትግል አድርገኽ በይቅርታ ጉልበትህ ላይ ስትጥልን ነው።

ከዚህ ውጭ ነፍሴ ትጠይቅህ አለች ለእኔ ብለህ የምታፈሰው ደም ነፍሴን እያስጠየቀኝ ነው። የሌላው ብሄር አባለትም ጥያቄየን ሳትመልስ ስሜን እንዳታነሳ።አጫሉ ሁንዴሳ በእኔ ላይ አድሮ ከተናገረው በጥቂቱ።

ስለዚህ አንቺም፣አንቺም፣አንተም፣አንተም ለኢትዮጵያ መፍትሄዎች አይደላችሁም።ይህን እየፃፍኩ እያለሁ ኢትዮ 360 ብለን/ተናግረን ነበር እያሉ ትንቢታቸውን መልሰው እያሳዩ ነበር።የሸናውን የጠጣ ብቻ። መንግስታዊ ተጠያቂነት እያሉ ነው ፣የዛሬ ቢል መክፈያና በርገራቸው እንደሚያሳየው።

ከስንት ግዜ በኃላ ስማቸውንም አየሁት ደህና ነህ ለመሆኑ፣እግዝብሄር ከአንተ ጋር ይሁን ንግግርህ ምንም ይሁን ምን ሴረኛ ግን አትመስለኝም።

ሌላው ማወቅ የምፈልገው ስንቶቻችሁን ናችሁ፣ ሀይማኖታችሁን መርምራችሁ ያመናችሁ።አብዛኞቻችን ከቤተሰባችን የወረስነው ነው። በነጩ ወረቀት በተፃፈልን ልክ ነን።ይህን ነው እኛ መርምረን ፣ከራሳችን እምነት ጋር መርምረን የምኖረው።በዚህ ዙርያ ብዙም ማለት አልፈልግም።ቢያንስ ትክክለኝነትህን የሚመሰክርልህ የፈጠረህ መሆኑን በማወቅ የእኔ ሃይማኖት ልክ ነው፣ እያልክ አትከራከር።ሀይማኖትህም ውረስ ነው።ስለዚህ የውረስከውን ሁልህም መርምር፣እውነቱን ተረዳ።የራስህን ውረስ መረዳት ሲያቅትህ የእኔን አትንካ።

በማወቅና ባማወቅ የተናገርሁት፣አባቶቼ ንሰሀየ ነውና ይፍቱኝ።

የጥበብ መጀመሪያ እግዝያብሄርን መፍራት ነው!

በዚህ አለም ምንም አዲስ ነገር የለም!

ትውልድ ሁሉ ብዕት ይሉሻል!

ትውልድ ሁሉ ጫማሽ ስር ይወድቃሉ!

የቄሰርን ለቄሳር የእግዝያብሄርንም ለእግዝያብሄር ስጡ።

አሜን ወ አሜን

ስብአት ለአብ፣ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን

ክብር ምስጋና ስግደት ለድንግል ማርያም

ኢትዮጵያ(ጰ) ነኝ

ጥቅምት **16/2013** ዓ.ም

ሁሉም ቀን ለእኔ ኪዳነ ምህረት ናት!! ድል አለ በስምህ!! ማዕበል ሲመታኝ ሞገዱ!!